## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
## የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት




# በኢትዮጵያ ማሪታይም ባለሥልጣን
# የሞጆ ሎጅስቲክስ ማዕከል ፕሮጀክት አፈፃፀምን
# በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

ግንቦት 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ማውጫ

የክዋኔ ኦዲቱ ዋና ዋና ግኝቶች (Executive Summery) .......... i
ክፍል አንድ .......... 1
መግቢያ .......... 1
የንግድ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ዓላማዎች፣ ተልዕኮ፣ ራዕይ እና ዕሴቶች .......... 3
የፕሮጀክቱ ዓላማ .......... 3
ራዕይ .......... 3
ተልዕኮ .......... 3
ዕሴቶች .......... 3
የማሪታይም ባለስልጣን ሥልጣንና ተግባር፡- .......... 4
የፕሮጀክት ፅ/ቤቱን በበላይነት የሚመራ የስቲሪንግ ኮሚቴው ሥልጣንና ተግባር .......... 4
በማሪታይም ባለስልጣን የንግድ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክት ጽ/ቤት (ሞጆ አረንጓዴ ሎጂስቲክስ ማዕከል) ዋና ዋና ተግባራት .......... 5
የባለስልጣን መ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል .......... 6
በማሪታይም ባለስልጣን የንግድ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክት ጽ/ቤት የሰው ሀይል አደረጃጀት .......... 6
የባለስልጣን መ/ቤቱ የሰው ሃይል .......... 6
የኢትዮጵያ ማሪታይም ባለስልጣን የፋይናንስ ምንጭ፡- .......... 7
የኦዲቱ ዓላማ .......... 9
የኦዲቱ አካባቢ (Audit Area) .......... 9
የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች (audit issue) .......... 9
የክዋኔ ኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ .......... 10
የክዋኔ ኦዲቱ መመዘኛ መስፈርቶች እና የተዘጋጀባቸው ማስረጃዎች .......... 10
የንግድ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክት ጽ/ቤት የአሰራር ስርዓት መገለጫ / system Discription/ .......... 11
Fund Flow and Report Chart .......... i
ክፍል ሁለት .......... 13
የኦዲት ግኝቶች .......... 13
I. በማሪታይም ባለስልጣን የንግድ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ሞጆ አረንጓዴ ሎጂስቲክስ ማዕከል ግንባታ ፕሮጀክቶች በዓለም ባንክ እና በፌዴራል መንግስት ፕሮጀክቶች አዘገጃጀት መመሪያ መሰረት የተከተለ መሆኑን ማረጋገጥ .......... 13

የሞጆ አረንጓዴ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክት በጥናት ላይ የተመሰረተ የዲዛይንና የግንባታ ውል አስተዳደር በተመለከተ ........ 13
ባለስልጣን መ/ቤቱ የሞጆ አረንጓዴ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክትን ዲዛይን መንደፉን በተመለከተ:: ........ 15
ባለስልጠን መ/ቤቱ በጨረታ ተወዳዳሪዎች ቅድመ-ብቃት ምዘና ማድረጉን በተመለከተ:: ........ 16
ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ተቋራጭ እና አማካሪው በውሉ መሰረት ስራቸውን በወቅቱ መጀመራቸውን በተመለከተ ........ 17
በጨረታ ያሸነፈው ተቋራጭ የግንባታ ግብዓቶች አቅርቦትን በተመለከተ ........ 18
ባለስልጣን መ/ቤቱ የፕሮጀክት አስተዳደር ማኑዋል ማዘጋጀቱንና ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ ........ 19
II. በማሪታይም ባለስልጣን የንግድ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ሞጆ አረንጓዴ ሎጂስቲክስ ማዕከል ግንባታ ፕሮጀክቶች በታቀደለት ጊዜና በጀት እንዲሁም በአካባቢ እና የማህበራዊ ደህንነት ተፅዕኖ ግምገማ መሰረት እየተከናወነ መሆኑን መገምገም:: 20
የሞጆ አረንጓዴ ሎጂስቲክስ ማዕከል ግንባታ ፕሮጀክት በዕቅድ በተያዘለት ዋጋ(በጀት) መጠናቀቁን በተመለከተ:: ........ 20
የሞጆ አረንጓዴ ሎጂስቲክስ ማዕከል ግንባታ ፕሮጀክቶች በዕቅድ በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ መሰራቱን በተመለከተ ........ 24
የሞጆ ሎጂስቲክስ ግንባታ ፕሮጀክት ትግበራ ሴቶች እና አካል ጉዳተኞችን ማካተቱን በተመለከተ፡፡ ........ 27
III. ባለስልጣን መ/ቤቱ ተቋራጭም ሆነ አማካሪ ድርጅት በገቡት የኮንትራት ውል እና ውሉን መሰረት አድርጎ በተዘጋጀው ቴክኒካዊ የሥራ ዝርዝር ውል መሰረት ግዴታቸውን መወጣታቸውን በቅድመ-ትግበራ፣ በሥራ ሂደት ትግበራ እና ድህረ ትግበራ ወቅት ውጤታማ ክትትልና ቁጥጥር ማድረጉን በተመለከተ፡፡ ........ 28
በጨረታ ወቅት ለውድድር የሚቀርቡ የቴክኒካል አፈፃፀምን በተመለከተ ........ 28
የፕሮጀክት ስትሪንግ ኮሚቴን በተመለከተ ........ 30
የዳኝነት ቦርድ ማቋቋሙን በተመለከተ ........ 31
ባለስልጣን መ/ቤቱ የፕሮጀክት አስተዳደር አቅምን ማሳደጉን በተመለከተ ........ 32
የሞጆ አረንጓዴ ሎጂስቲክስ ማዕከል ግንባታ ፕሮጀክት መረጃ አያያዝን በተመለከተ ........ 34
IV. የኢትዮጵያ ማሪታይም ባለሥልጣን በሞጆ አረንጓዴ ሎጂስቲክስ ማዕከል ግንባታ ፕሮጀክት ለልማት ተነሽዎች በወቅቱ የካሳ ክፍያ መከፈሉን ማረጋገጥ፡፡ ........ 35
ካሳ ክፍያ እና በመልሶ ማቋቋምን በተመለከተ:: ........ 35
ክፍል ሶስት ........ 39

የኦዲቱ መደምደሚያ ሃሳቦች (audit conclusion)......39
ክፍል አራት......43
የማሻሻያ ሃሳቦች......43
አባሪ 1......i
አባሪ 2......x
አባሪ 3......xi
አባሪ 4......xii
አባሪ-5......xiv
አባሪ-6......xvii
አባሪ-7......xix
አባሪ-8......79

# የክዋኔ ኦዲቱ ዋና ዋና ግኝቶች (Executive Summery)

በማሪታይም ባለስልጣን ሥር የሚተዳደረው የሞጆ ደረቅ ወደብና ተርሚናል ከአገሪቱ የገቢ ንግድ ከ90% በላይ የሚሆነዉን የወደብ አገልግሎት የሚሰጥ ቢሆንም ያለው መሰረተ ልማትና የአገልግሎት አሰጣጥ ከገቢ ንግድ መጠንና ከሀገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገት ጋር የተመጣጠነ ባለመሆኑ ባለፉት ዓመታት በኢትዮ-ጂቡቲ የንግድ ኮሪደር ሲፈጠር ለነበረዉ የተንተተ የሎጂስቲክስ ትራንዚት አፈጻጸም ምክንያት ሆኖ ቆይቷል፡፡ ይህንንም በመረዳት የሞጆ ደረቅ ወደብን ሁለንተናዊ የሎጂስቲክስ አቅምና አፈጻጸም ማሳደግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ እና ችግሩን ለመቅረፍ እንዲቻል መንግስት ከዓለም ባንክ ጋር ለፕሮጀክቱ ማስፈፀሚያ የሚውል 150,000,000 (አንድ መቶ ሃምሳ ሚሊዮን) የአሜሪካ ዶላር የብድር ስምምነት መጋቢት 29/2009 ዓ.ም (April-07/2017) ተፈርሞ በ3 ዋና ዋና ተግባራት ማለትም በሞጆ ያለውን መሰረተ-ልማት ማሻሻል፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስርዓቶችን በማጠንከር የተቀናጀ አሰራር እንዲኖር ማድረግ እና የአስተዳደራዊ እና ተቋማዊ (አቅም ግንባታ) ድጋፍ ላይ ትኩረት አድርጎ ፕሮጀክቱ በመተግበር ላይ ይገኛል፡፡

የክዋኔ ኦዲቱ የተከናወነው በአለም አቀፍ የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (International Standards For supreme Audit Institutions -ISSAI) እና የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 982/2008 ዓ.ም በተሰጠው ስልጣን መሰረት ሲሆን፤ የክዋኔ ኦዲቱ የሚሸፍነው ከመጋቢት 29/2009 ዓ.ም (April-07/2017) እስከ ታህሳስ 30/2016 ዓ.ም ባለው ጊዜ የሞጆ ሎጅስቲክስ ማዕከል ፕሮጀክት አፈፃፀምን የተመለከተ የሥራ ክንውኖች ላይ ሲሆን ለኦዲቱ አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎችን በማሰባሰብ፣ በመተንተን እና የተለያዩ የኦዲት ዘዴዎችን በመከተል ተከናውኗል፡፡

የክዋኔ ኦዲቱ አላማ የሞጆ ሎጅስቲክስ ማዕከል ግንባታ ፕሮጀክት የመሰረተ-ልማት ማሻሻል፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስርዓት እና የአስተዳደራዊ እና ተቋማዊ (አቅም ግንባታና ድጋፍ ሥራዎች) ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆናቸውን መገምገም ሲሆን፣ በዚህ ዙሪያ የሚታዩ የአሰራር ክፍተቶች ካሉ በመለየት ችግሮቹን ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሀሳብ ለማቅረብና ተጠያቂነትን ለማጠናከር ነው፡፡

በመሆኑም በክዋኔ ኦዲቱ የታዩ ዋና ዋና ግኝቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡-

- ☞ እ.ኤ.አ በ2019 የተሰራው የፕሮጀክቱ የመጀመሪያው አርክቴክቸር ዲዛይን የግንባታ ሳይቱን አጠቃላይ ገጽታ፣ የሎጀስቲክስ ግንባታ ቦታ እና በዙርያው ያሉ ነገሮችን በፍጥነት ለመረዳት የሚያስችለው የድሮዊንግ ርዕስ (drawing Title) የጎደለው መሆኑ፡፡

- ☞ በሎጂስቲክስ  መሰረተ ልማት አፈፃፀም የዲዛይንና የግንባታ ፕሮጀክቶች ኮንትራት አስተዳደር ችግር መኖሩ እንዲሁም አብዛኞቹ የግንባታ ውል ሥዕሎች( contract drawings) ያልተሟሉ እና ግልፅ ያልሆኑ መሆናቸው፤
- ☞ የፕሮጀክቱ የግምገማ ሰነድ ሲዘጋጅ የጨረታ ቅድመ ብቃት እና ድህረ ብቃት የማወዳደርያ ዘዴዎች እንዳስፈላጊነቱ መጠቀም በሚያስችል መልኩ እቅድ ላይ ሳይካተት የጸደቀ መሆኑ፣
- ☞ በውል ስምምነቱ መሰረት አሸናፊው ተቋራጭ ለግንባታ የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን በማቅረብ ግንባታውን ማከናወን ያለበት ቢሆንም ተቋራጩ በተደጋጋሚ የሲሚንቶ ግብዓት እጥረትን ለፕሮጀክት መጓተት እንደ ዋና ምክንያት እየተጠቀመበት ያለ መሆኑ፤
- ☞ በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ቀድሞ ተግባራዊ የሆነው የፕሮጀክት አስተዳደር ማኑዋል/Project Administrative Manual/ ከ6 አመት በላይ የቆየ እና ወቅቱን ያላገናዘበ ሲሆን በእ.ኤ.አ መጋቢት 2021 ተከልሶ የቀረበው የፕሮጀክት አስተዳደር ማኑዋል /Project Administrative Manual/ ያለ ቢሆንም በሚመለከተው አካል ጸድቆ ወደ ሥራ ያልገባ መሆኑ እንዲሁም በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ተሻሽሎ የቀረበውም ቢሆን ለሚመለከተው አካል ቀርቦ ያልጸደቀ መሆኑ፤
- ☞ ፕሮጀክቱን ለማከናወን በ2013 በጀት ዓመት በዕቅድ የተያዘ 51,597,147.0 የአሜሪካ ዶላር (ሃምሳ አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ዘጠና ሰባት ሺ አንድ መቶ አርባ ሰባት የአሜሪካ ዶላር) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ለፕሮጀክት ሥራ የተከፈለው ክፍያ 7,118,397.5 (ሰባት ሚሊዮን አንድ መቶ አስራ ስምንት ሺ ሶስት መቶ ዘጠና ሰባት ከ50/100) (13.8%) በመሆን ከዕቅድ አንጻር የፋይናንስ አፈፃጸሙ ዝቅተኛ መሆኑ፤
- ☞ በ2014 በጀት ዓመት በዕቅድ የተያዘ 44,253,280.0 የአሜሪካ ዶላር (አርባ አራት ሚሊዮን ሁለት መቶ አምሳ ሶስት ሺ ሁለት መቶ ሰማንያ የአሜሪካ ዶላር) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ለፕሮጀክት ሥራ የተከፈለው ክፍያ 24,779,769.64 (ሃያ አራት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሰባ ሰባት ሺ ሰባት መቶ ስልሳ ዘጠኝ ከ65/100 የአሜሪካ ዶላር) (56%) በመሆን ከዕቅድ አንጻር የፋይናንስ አፈፃጸሙ ዝቅተኛ መሆኑ፤
- ☞ በ2015 በጀት ዓመት የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስርዓትን በማጠንከር የተቀናጀ አሰራር ለመፍጠር የሚያስችል 6,140,137.89 (ስድስት ሚሊዮን አንድ መቶ አርባ ሺ አንድ መቶ ሠላሳ ሰባት ከ89/100) የአሜሪካ ዶላር ዓመታዊ በጀት ዕቅድ የተያዘ ቢሆንም ከዚህ ውስጥ ስራ ላይ የዋለው የዕቅዱ (0.85%) 51,955.35 (አምሳ አንድ

ሺ ዘጠኝ መቶ አምሳ አምስት ከ35/100) የአሜሪካ  ዶላር ሲሆን ከዕቅድ አንጻር የፋይናንስ አፈፃጸሙ ዝቅተኛ መሆኑ፤

- ☞ የሞጆ አረንጓዴ ሎጂስቲክስ ማዕከል ግንባታ ማስፋፍያ ፕሮጀክት እየተከናወነ የሚገኘው ከአለም ባንክ በተገኘ ብድር  ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የፕሮጀክቱ ስራዎች ሲከናወኑ ውጤታማ፣ ወጪ ቆጣቢ መሆን ሲገባው የመኪና ግዥ በሚመለከት ለሲቪል ሥራ በተቀመጠው ውል Bill of Quantity በ Item 01500.5 a,b ላይ እንደተቀመጠው 4(ታይፕ)አይነት A እና 7(ታይፕ)አይነት B መኪናዎች በድምሩ 11 መኪናዎች መገዛት እንዳለበት እና ከተገዙት 4ታይፕ/አይነት A ሁለት ለአሰሪው ተቋም ሁለት ለአማካሪው መሆን እንዳለበት በውሉ የተመላከተ ቢሆንም ነገር ግን 4ታይፕ/አይነት A መኪናዎችን ሁሉንም አሰሪው መ/ቤት የወሰደ መሆኑ፣ በተጨማሪ ታይፕ/አይነት B 2 አዲስ ፒክአፕ መኪናዎችን አሰሪው ተቋም በመውሰድ አማካሪው ሁለት  መኪናዎችን በኪራይ እንዲጠቀም መደረጉ፣
- ☞ ፕሮጀክቱ እ.ኤ.አ ሐምሌ 2017 ተጀምሮ ሐምሌ 2023 ይጠናቀቃል ተብሎ የታቀደ ቢሆንም በይፋ ስራ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ እስከ 2016 ዓ.ም. ሩብ በጀት ዓመት ድረስ  ወይም እ.ኤ.አ (2024) ጠቅላላ የፕሮጀክቱ አፈጻጸም 61.51% ብቻ በመሆኑ ከዕቅድ አንፃር  ሲታይ ፕሮጀክቱ የዘገየ መሆኑ፤
- ☞ የመሰረተ-ልማት ማሻሻያ ስራው በ2013 በጀት ዓመት መጨረሻ ከደረሰበት 30.92% የክንውን አፈፃፀም በበጀት ዓመቱ 15.82% በማከናወን አጠቃላይ ስራውን 46.74% ለማድረስ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም  በበጀት አመቱ  2.31% ብቻ የተከናወነ መሆኑ፤
- ☞ በ2014 በጀት ዓመት የሲቪል ግንባታ የጨረታ ሂደት ተጠናቆና ውል ተፈርሞ የግንባታ ስራው  በበጀት ዓመቱ 18.21% ይደርሳል ተብሎ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም 3% ብቻ የተከናወነ መሆኑ፤
- ☞ የአይ.ሲ.ቲ. መሰረተ-ልማት ለማስፋፋት የተለያዩ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስራዎችን በማከናወን በዘርፉ ያለውን ቅንጅታዊ አሰራር ለማሻሻል ስራው በ2014 በጀት ዓመት ከደረሰበት 42.04% በ2015 በጀት ዓመት 23.24% በማከናወን  65.28% ለማድረስ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም በበጀት ዓመቱ 2.09% ብቻ ተከናውኖ አጠቃላይ አፈጻጸሙ ዝቅተኛ መሆኑ፤
- ☞ የTerminal Operating System (TOS)፣ Gate Operating System (GOS) እና የPort Community System (PCS) በ2014 በጀት ዓመት 4.62 ለማከናወን ታቅዶ አመታዊ አፈፃፀሙ ዜሮ መሆኑ፣

- ☞ በ2015 በጀት ዓመት የሲቪል ግንባታ ስራ ከነበረነት 2.5% በበጀት ዓመቱ ውስጥ 33.72% በማከናወን 36.22% ለማድረስ ታቅዶ 23.80% ብቻ የተከናወነ በመሆኑ አፈፃፀሙን ዝቅተኛ መሆኑ፤
- ☞ ፕሮጀክቱ ሲቀረፅ በፕሮጀክት ጥናት ጀምሮ በፕሮጀክት ትግበራና አፈፃፀም ወቅት በእያንዳንዱ የሥራ ሂደት ሴቶች እና ድጋፍ የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎችን አካትቶ ተግባራዊ ለማድረግ በዕቅድ ያላከተተ መሆኑ እና በአፈፃፀሙ ወቅትም ከዚህ አንፃር ስለመገምገሙ ማስረጃው ለኦዲት ያልቀረበ መሆኑ፤
- ☞ የፕሮጀክት ስትሪንግ ኮሚቴ በሚፈለገው መጠን የፕሮጀክቱን እንቅስቃሴ በመስክ ላይ በመገኘት የፕሮጀክቱ ተግባራት ያሉበትን ደረጃ ገምግሞ አቅጣጫዎችን የማስቀመጥና የውሳኔ ሃሳብ ያልሰጠ መሆኑ፤
- ☞ አማካሪው ለአራት ወራት ያህል ዘግይቶ በመግባቱ የግንባታ ስራው እንዲዘገይና የግንባታ ቁጥጥር ስራውም ታቅዶ ካልተከናወኑት ተግባራት ውስጥ እንዲሆን ያደረገው መሆኑ፤
- ☞ የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሰው ሃይል ያልተሟላ እና ለፕሮጀክቱ አስፈላጊ የሆኑ ባለሙያዎች የሚቀጠሩበት መንገድ  ብቁ ተወዳዳሪዎችን አካታች ባደረገ መልኩ እና በውድድር አለመሆኑ፣
- ☞ የግንባታ ፕሮጀክቱን ዝግጅት እና አተገባበርን በተመለከተ በብሮሸር፣ፍላየር(በበራሪ-ወረቀት)ወ.ዘ.ተ በመሳሰሉ የማስተዋወቅያ ዘዴዎችን በመጠቀም በስፋት ፕሮጀክቱን የማስተዋወቅ ስራ አለመስራቱ እንዲሁም ዘመናዊ የመረጃ ቴክኖሎጂ በመጠቀም መረጃን በሚገባው መጠን ተደራሽ ያልተደረገ መሆኑ፤

ከላይ ለተገለፁት ግኝቶች የተሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ☞ የኢትዮጵያ ማሪታይም ባለስልጣን የሞጆ ሎጂስቲክስ ማዕከል ፕሮጀክትን ለመተግበር ስራውን ሲጀመር የቅድመ አዋጭነት እና የአዋጭነት ጥናት በማስጠናት፣ የፕሮጀክት ግምገማ ሰነድ እና የፕሮጅክት ትግበራዎች በቅድም ተከተል በማከናወን በጥልቅ በተጠና ዲዛይን ሥራውን መስራት በሀገር ውስጥ ለሚተገበሩ ማናቸውም የግንባታ ፕሮጀክቶች ውጤታማ እንዲሆኑ ስለሚያስችል፣ የሞጆ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክትም ሆነ ወደ ፊት በብድር እና በመንግስት ፋይናንስ የሚሰሩ ትላልቅ ሀገራዊ ፕሮጀክቶች በጥናት ላይ የተመሰረተ የዲዛይንና የግንባታ ኮንትራት አስተዳደር ስርዓት ሊኖራቸው ይገባል፡፡

- ☞ የግንባታ ፕሮጀክቶች ስራን ለመተግበር የተሟላ የዲዛይን ንድፍ መንደፍ ወጪን ለመቀነስ፣ በጊዜ ለመጨረስ፣ አጠቃላይ ጥራትን ለማሻሻል እና የግንባታው ሂደቱን የበለጠ ውጤታማ መሆኑን ለማረጋገጥ እንዲሁም ሥራ ተቋራጭ እና አማካሪ ተቋም ስራቸውን በብቃት እንዲሰሩና የግንባታ ፕሮጀክቱ እንዴት እንደሚሠራ በቀላሉ እንዲረዱ የሚያግዝ በመሆኑ የሞጆ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክትም ሆነ ወደ ፊት በብድር እና በመንግስት ፋይናንስ የሚሰሩ ትላልቅ ሀገራዊ ፕሮጀክቶች ሲቀርፅ የፕሮጀክቱን ገፅታ በተገቢው መንገድ የሚሳይ ግልጽ እና የተሟላ ዲዛይን መነደፍ ይኖርበታል፡፡
- ☞ ባለስልጣን መ/ቤቱ የሞጆ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክትም ሆነ ወደ ፊት በብድር እና በመንግስት ፋይናንስ የሚሰሩ ትላልቅ ሀገራዊ ፕሮጀክቶች ግዥ በሚፈፅምበት ወቅት የቀድሞ የግንባታ ልምድን መስረት በማድረግ ስለግንባታ አፈፃፀማቸው ከሰሩበት ሀገር ከሚገኙ አሰሪ ተቋማት ይሁን እራሱ ከሰጣቸው ፕሮጀክቶች የሥራ አፈፃፀም ምስክርነት እንዲያቀርቡ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ☞ አንድ የግንባታ ፕሮጀክት ውጤታማ ነው ለመባል በተመደበለት የጊዜ እቅድ እና በተያዘለት በጀት ማለቅ ሲችል በመሆኑ ይህ ትልቅ ሀገራዊ ፕሮጀክት ከአለም ባንክ በተገኘ ብድር የሚሰራ ፕሮጀክት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ፕሮጀክቱ በተያዘለት ጊዜና በጀት ስራዎችን በተገቢው መንገድ ማከናወን ይኖርበታል፡፡ ስለሆነም የፕሮጀክቱ ስራዎች ሲከናወኑ ውጤታማ፣ ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ ሲተገበሩ አመርቂ ውጤት ስለሚያስገኝ ባለስልጠን መ/ቤቱ የሞጆ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክትም ሆነ ወደ ፊት በብድር እና በመንግስት ፋይናንስ የሚሰሩ ትላልቅ ሀገራዊ ፕሮጀክቶችን ሲቀርፅ ፕሮጀክቶች በተገባው የኮንትራት ውል መሰረት በታቀደው የጊዜ እና ዋጋ (በጀት) እንዲጠናቀቁ የሚያስችሉ ሥራዎችን ሊሰራ ይገባል፡፡

# ክፍል አንድ
## መግቢያ

1. ኢትዮጵያ ከዘመናት በፊት በቀይ ባህር የንግድ ልውውጥ ታደርግ እንደነበረ መረጃዎች ያሳያሉ:: ይህ የባህር ንግድ የሚካሄደው በአነስተኛ ጀልባዎች ሲሆን ሥርዓት ያለው ቁጥጥር የማይደረግበትና በማዕከል የማይመራ ነበር። በሀገራችን የባህር ትራንስፖርት ለሀገር ዕድገት ጠቃሚነቱና ዘመናዊ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ መሆኑን ግንዛቤ ያገኘው ከኢጣሊያን ወረራ በኋላ ነው።
2. ከዚህም የተነሳ የአሰብና የምጽዋ ወደቦችን በበላይነት የሚያስተዳድር በ1945 ዓ.ም የማሪታይም አስተዳደር በሚል ስያሜ ተቋቋመ። ይኸው የማሪታይም አስተዳደር በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ ደረጃዎች የነበሩት ሲሆን፣ በ1971 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 139/71 መሠረት የማሪታይም ትራንስፖርት ባለሥልጣን (Maritime Transport Authority) በሚል ስያሜ ተጠሪነቱ ለትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስትር ሆኖ ራሱን የቻለ ባለሥልጣን መ/ቤት (Autonomous Public Authority) በመሆን እንደገና ተቋቋመ። ይህ የባለሥልጣን መ/ቤት በተለይም የአሰብና የምጽዋ ወደቦችን ከማስተዳደር በተጨማሪ በወደቦቹ የመርከቦች መነሻ /Stevedoring/ እና የባህር ዳርቻ አጠቃቀም /shore handling/ አገልግሎቶችና የወደብ የዕቃ መገልገያ መሣሪያዎች የማከራየት አገልግሎት ይሰጥ ነበር።
3. በ1983 ዓ.ም በአገራችን በተፈጠረው የፖለቲካ ለውጥ ይህ መ/ቤት በዋናነት ተልዕኮው በወደብ ላይ ያተኮረ ስለነበር አስፈላጊነቱ ስላልታመነበት እንዲፈርስ ተደረገ። ሆኖም የማሪታይም አስተዳደርን በተመለከተ የማሪታይም መምሪያ በትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር ስር በመምሪያ ደረጃና በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ስር በመምሪያ ደረጃ ተዋቅሮ የወደብና የትራንዚት ጉዳዮችን የሚከታተል የወደብ ጉዳዮች መምሪያ በመባል ተቋቋመ። በዚህ መልኩ እስከ 1999 ዓ.ም ድረስ ሲሰራ ቆይቶ፣ ዘርፉ በተበታተነ መልኩ መመራቱ ብቻ ሳይሆን ባለቤት እንደሌለው ታይቶ የማሪታይም ዘርፍ ወጥ የመንግስት አካል የመኖር አስፈላጊነት ስለታመነበት በማሪታይም ዘርፍ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 549/99 መሠረት ነሐሴ 29 ቀን 1999 ዓ.ም የማሪታይም ጉዳይ ባለሥልጣን በትራንስፖርት እና መገናኛ ሚኒስቴር ሥር እንደገና እንዲቋቋም ተደረገ።
4. በርካታ ሀገሮች የሎጂስቲክስ አፈጻጸምን ለማሻሻል የሚያስችሉ ስትራቴጂዎችና ስልቶችን ለመቀየስ በመነሻነት የሚጠቀሙት ጥናትና ሪፖርት በየሁለት ዓመቱ በዓለም ባንክ የሚዘጋጀው የሎጅስቲክስ አፈጻጸም መለኪያ ሪፖርት መሰረት ነው:: በዚህ

ሪፖርት መሰረት እ.ኤ.አ በ2010 የኢትዮጵያ የሎጅስቲክስ አፈጻጸም (LPI) ኢትዮጵያ 104ኛ ደረጃ የነበረች ሲሆን፣ የ2016 ዕቅድ ዘመኑ ሲጠናቀቅ 57ኛ ደረጃ ትደርሳለች ተብሎ ቢታቀድም በ2016 እ.ኤ.አ በዓለም ባንክ የሎጅስቲክስ አፈጻጸም ኢንዴክስ (LPI) መሰረት ከ160 ሀገራት 126ኛ ላይ ትገኛለች፡፡

5. የሞጆ ደረቅ ወደብና ተርሚናል ከአገሪቱ የገቢ ንግድ ከ90% በላይ የሚሆነዉን የወደብ አገልግሎት የሚሰጥ ቢሆንም ያለው መሰረተ ልማትና የአገልግሎት አሰጣጥ ከገቢ ንግድ መጠንና ከሀገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገት ጋር የተመጣጠነ ባለመሆኑ በአለፉት ዓመታት በኢትዮ-ጂቡቲ የንግድ ኮሪደር ሲፈጠር ለነበረዉ የተንተተ የሎጂስቲክስ ትራንዚት አፈጻጸም ምክንያት ሆኖ ቆይቷል፡፡ ይህንንም በመረዳት የሞጆ ደረቅ ወደብን ሁለንተናዊ የሎጂስቲክስ አቅምና አፈጻጸም ማሳደግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ እና ችግሩን ለመቅረፍ እንዲቻል መንግስት ከዓለም ባንክ ጋር ለፕሮጀክቱ ማስፈፀሚያ የሚውል 150,000,000 (አንድ መቶ ሃምሳ ሚሊዮን) የአሜሪካ ዶላር የብድር ስምምነት መጋቢት 29/2009 ዓ.ም (April-07/2017) ተፈርሞ በ3 ዋና ዋና ተግባራት ማለትም በሞጆ ያለውን መሰረተ-ልማት ማሻሻል፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስርዓቶችን በማጠንከር የተቀናጀ አሰራር እንዲኖር ማድረግ እና የአስተዳደራዊ እና ተቋማዊ (አቅም ግንባታ) ድጋፍ ላይ ትኩረት አድርጎ ፕሮጀክቱ በመተግበር ላይ ይገኛል፡፡
6. የሎጂስቲክስ መሠረተ-ልማትን ከማስፋፋት አኳያ ዘመናዊ እና ቀልጣፋ የሎጂስቲክስ ማዕከላትን ለመፍጠር እንዲያስችል በዕቅድ ዘመኑ በርካታ ኘሮጀክቶች እንዲከናወኑ ከተቀመጡት ውስጥ አንዱ የሞጆ የሎጂስቲክስ ማዕከል ግንባታ ኘሮጀክት አፈፃፀሙ 49% ደርሷል፡፡
7. በሎጂስቲክስ ዘርፍ የነበሩ ክፍተቶች የሎጅስቲክስ ጊዜና ወጪ ከዓለም አቀፍ ስታንዳርድ ጋር ሲነፃፀር ወጪው በእጅጉ ከፍተኛ ነው፡፡ የዕቃዎቹ የወደብ ላይ ቆይታ የሀገራችን ከዓለም አቀፍ ስታንደርድ /አማካይ 3 ቀናት/ አንፃር ከ10 እጥፍ በላይ ነው፡፡ ስለሆነም ውጤታማና ፈጣን የሎጅስቲክስ ሥርዓት ከመዘርጋት አኳያ የንግድና የፋይናንስ ትራንስፖርት ሎጅስቲክስ ሥርዓቱ አንዱ ክፍተት መሆኑ ታይቷል፡፡
8. የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የተቋቋመው የንግድ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክትን ዓላማና በተያዘለት ዕቅድ መሰረት ለማስፈጸም በሎጅስቲክስ ዘርፉ የሚታዩትን መጓተቶችና ተያያዥ ችግሮች ለመቅረፍና በዘርፉ ሊገኙ የሚችሉ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳዎችን ለማሳደግ እንዲቻል ሆኖ የሞጆ ደረቅ ወደብን በአገልግሎት አይነትና ቁጥር ለማሳደግና ለማስፋፋት በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ለማዘመንና የአቅም ግንባታ ስራዎችን መስራትና አሰራሮችን መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የኢትዮጵያ ማሪታም ጉዳይ ባለስልጣን

ስር የፕሮጀክት ጽ/ቤት ተቋቁሞ አራት ዓመታትን አስቆጥሯል፡፡ የፕሮጀክት ጽ/ቤቱን ስራዎች በበላይነት የሚመራ፣ የሚከታተልና የሚገመግም፣የተለያዩ ወሳኝ ውሳኔዎችን የሚወስንና የወደፊት አቅጣጫዎችን የሚያስቀምጥ የፕሮጀክት ስትሪንግ ኮሚቴ/Project Steering Committee-PSC/ ተቋቁሞ በስራ ላይ ይገኛል፡፡

## የንግድ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ዓላማዎች፣ ተልዕኮ፣ ራዕይ እና ዕሴቶች

### የፕሮጀክቱ ዓላማ

9. የፕሮጀክቱ አጠቃላይ ዓላማ የሞጆ ደረቅ ወደብ የማስተናገድ አቅም፣ ቅልጥፍና እና ተዛማጅ የሎጂስቲክስ አገልግሎቶችን ደረጃ ከመሰረቱ መቀየር እና የኢትዮ-ጂቡቲን የንግድ ኮሪደር /መተላለፊ/ አቅም የአገሪቱ የኢኮኖሚያዊ ዕድገት በደረሰበት ደረጃ መሸከም እንዲችል ማብቃት ነዉ፡፡

### ራዕይ

10.በ2016 ዓ.ም መጨረሻ የሞጆ ደረቅ ወደብና ተርሚናልን አቅም በማሳደግ በገቢና ወጭ ንግድ አገልግሎት ዘርፍ ከአፍሪካ ቀዳሚ ሆኖ ማየት፡፡

### ተልዕኮ

11.የማስፈጸም አቅምን በማሳደግ፣ በዘርፉ ቁልፍ ሚና ያላቸውን ተቋማት በመገንባት፣ በማስፋፋት እና የዘርፉን አሰራር ለማዘመን የሚያስችሉ አሰራሮችን ለማስፈን የሚያስችል የኢንፎርማሽን ቴክኖሎጅ ስራዎችን በማስፋፋት የሞጆ ደረቅ ወደብ በገቢና ወጭ ንግዱ ላይ ያለውን አሰራር ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ወጭ ቆጣቢ እንዲሆን በማስቻል ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ አስተዋጽዖ ማበርከት ነው፡፡

### ዕሴቶች

- ✓ በቡድን የመስራት መንፈስ
- ✓ ቅንጅታዊ አሰራር
- ✓ ግልፀኝነት
- ✓ ታማኝነት
- ✓ ቅድሚያ ለደህንነት
- ✓ ውጤታማነት

## የማሪታይም ባለስልጣን ሥልጣንና ተግባር፡-

12.ባለስልጣኑ በአዋጅ ቁጥር 549/1999 የተሰጡትን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ የሚከተ ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡-

- በገቢና ወጪ ንግድ ኮሪደሮች የሚካሄደውን የአገሪቷን የገቢና ወጪ ዕቃዎች እንቅስቃሴ ኢኮኖሚያዊነትና ቀልጣፋነት ማረጋገጥ፤ መቆጣጠር፤ ማስተባበርና ለችግሮች አፋጣኝ መፍትሔ መስጠት፤
- በባህር ወደቦች የራሱ የመርከብ መጠጊያ እንዲኖረው መጣር፣ የደረቅ ወደብ ግንባታና አገልግሎት ማስፋፋት፣ የገቢና ወጪ ዕቃዎች የትራንዚት፣ የመርከብና ሌሎች ጭነቶች ዋጋ ለመደራደር የሚያስችል ክህሎት ማዳበር፣
- ማናቸውንም የደረቅ ወደብ አገልግሎት መስጫ መሳሪያዎች ወይም መገልገያዎች መመርመርና መፍቀድ፣ የደረቅ ወደብ አገልግሎት፣ የሃገር ውስጥ ጉምሩክ ማስተላለፊያ ቦታዎችን አገልግሎቶች መቆጣጠር፣
- የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴርን በማስፈቀድ ዓለም አቀፍ የማሪታይምና ትራንዚት አገልግሎት ስምምነቶች መደራደር፣ ደንቦች እንዲወጡ ወይም እንዲተገበሩ ማድረግ አፈጻጸማቸውን መከታተል፣
- የደረቅ ወደቦችንና ሌሎችንም የውሃ ትራንስፖርት ነክ ጉዳዮችና ተግባሮች በማጥናት ፕላንና ፕሮግራም ማዘጋጀት፣ በሚፈቀደው ፕሮግራም መሰረት ደረቅ ወደቦችና ሌሎችንም የሐመር (በውሀ ላይ ለመጓጓዝ የሚያገለግል ማንኛውም አይነት መርከብ፣ጀልባ፣ታንኳ ወይም ሳንቡቃ) መገልገያዎች ማቋቋም፣ ማሻሻልና መጠገን፤
- በዚህ አዋጅ መሰረት የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ረቂቅ መመሪያዎችን ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ሁሉ በግልጽ እንዲያውቁት ማድረግ፤
- ውል መግባት፣ መክሰስና መከሰስ፣ ክርክሮችን በግልግል መጨረስና ለስራው እንደሚያስፈልገው ማንኛውንም ዓይነት ንብረት መግዛት፣ መሸጥ፣ ባለቤት መሆን፣ መከራየት ወይም ማከራየት፤

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

## የፕሮጀክት ፅ/ቤቱን በበላይነት የሚመራ የስቲሪንግ ኮሚቴው ሥልጣንና ተግባር

13.የፕሮጀክት ጽ/ቤቱን ስራዎች በበላይነት የሚመራ፣ የሚከታተልና የሚገመግም፣ የተለያዩ ወሳኝ ውሳኔዎችን የሚወስንና የወደፊት አቅጣጫዎችን የሚያስቀምጥ የፕሮጀክት ስትሪንግ ኮሚቴ /Project Steering Committee-PSC/ ተቋቁሟል፡፡ የፕሮጀክት ስትሪንግ ኮሚቴው በትራንስፖርትና ሎጀስቲክ ሚኒስትር ሰብሳቢነት ከገንዘብ ሚኒስቴር፣ ከንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ ከግብርና ሚኒስቴር፣ ከገቢዎች

ሚኒስቴር፣ ከኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ፣ ከኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅትና ከፕሮጀክቱ ባለቤት ከኢትዮጵያ ማሪታይም ባለስልጣን የተውጣጣና የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ አስተባባሪ አባልና ሴክሬታሪያት የሚገኙበት ኮሚቴ ነው። ስትሪንግ ኮሚቴው የሚከተሉት ዋና ዋና ስልጣንና ሃላፊነቶች አሉት፡-

- የፕሮጀክቱን አፈፃፀም በበላይ ሆኖ ይከታተላል፤ ይገመግማል፣
- ለፕሮጀክቱ አፈፃፀም የሚረዱ የፖሊሲ አቅጣጫዎችን ያመላክታል፣
- ለፕሮጀክቱ ጠቀሜታ ሲባል ከተለያዩ አካላት ጋር የትብብር ግንኙነቶች እንዲኖሩ ያደርጋል፣
- ሪፖርቶችን፣ እቅዶችንና በጀት ገምግሞ ያፀድቃል።

በተጨማሪም እንደ ትግበራው ሁኔታና እንዳስፈላጊነቱ አፈጻጸሙን በቅርበት የሚከታተልና ዕገዛ የሚያደርግ በማሪታይም ባለስልጣን ደረጃ በዋና ዳይሬክተሩ የሚመራ ኮሚቴም አለው።

## በማሪታይም ባለስልጣን የንግድ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክት ጽ/ቤት (ሞጆ አረንጓዴ ሎጂስቲክስ ማዕከል) ዋና ዋና ተግባራት

- የፕሮጀክቱን በጀት ዓመት እቅድ እና የድርጊት መርሃ-ግብር ማዘጋጀት፣
- በበጀት ዓመቱ ውስጥ ሳምንታዊ የእቅድ አፈፃፀምን የሚያሳዩ ሪፖርቶች እና የበጀት ዓመቱ የ1ኛው፣ የ2ኛው፣ የ3ኛውና 4ኛው ሩብ ዓመቶች ሪፖርቶች በማዘጋጀት ለሚመለከተው ይልካል፣
- የፕሮጀክቱ ተግባራት ያሉበትን ደረጃ ለመገምገም የሚያስችሉ የተግባራት ግምገማ በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ እና ከዓለም ባንክ ባለሞያዎችና ሃላፊዎች ጋር የተለያዩ ውይይቶች /technical session Meeting/ እና የትግበራ ድጋፍ የተልኮ ግምገማዎች (Implementation Support Missions) ያካሂዳል። በተደረጉት ውይይቶችም የፕሮጀክቱ አፈጻጸሞች ላይ ማለትም በሲቪል ግንባታ ስራው፣ በአማካሪ ቅጥሩ፣ በፖርት ማሽነሪ፣ በTOS (Terminal Operating System) GOS (Gate Operating System) እና በPCS (Port Community System) አፈፃፀሞችና ላጋጠሙ ችግሮችም መፍትሄዎች ያስቀምጣል፣
- ፕሮጀክቱ ወደፊት ሊያጋጥሙት የሚችሉ ችግሮችን ለመቅረፍ የሚያስችል የፕሮጀክት ስጋት ማቅለያ እቅድ /Project Risk Mitigation Plan/ ለማዘጋጀት የሚያስችል እቅድ በማዘጋጀት ከሁሉም የፕሮጀክቱ ባለሙያዎች የወደፊት ስጋቶች በማሰባሰብ በተገኙት መረጃዎች መሰረት የፕሮጀክት የስጋት ማቅለያ እቅድ በመከለስ ይተገብራል፡

- የሞጆ ደረቅ ወደብን አሰራር በቴክኖሎጅ ከመደገፍ አንፃር ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የተለያዩ ጥረቶችን ማድረግ፣ የደረቅ ወደቡን Terminal Operating System እና Gate Operating System(TOS-GOS) ለማዘመንና የሃገሪቱን የገቢና ወጭ አሰራር-Port Community System (PCS) ዲጅታላይዝ ማድረግ፣ ሥራዎችን በዋናነት ይተገብራል፡፡

## የባለስልጣን መ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል

14.የማሪታይም ባለስልጣን ተጠሪነቱ ለትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ሚኒስትር ሆኖ በአንድ ዋና ዳይሬክተር የሚመራ ሲሆን በስሩ አንድ ምክትል ዋና ዳይሬክተር፣ ሦስት ጽ/ቤት፣ አንድ የኳሊት ማኔጅመንት ቡድን እና የሥራ አመራር ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሲኖረው በምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ስር የማሪታይም አስተዳደር መሪ ሥራ አስፈፃሚ፣ የዓለም አቀፍ ማሪታይም ህግ እና ትብብር መሪ ሥራ አስፈፃሚ፣ የሎጅስቲክስ አስተዳደር መሪ ሥራ አስፈፃሚ እና የባህር ወደብ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ይገኛሉ፡፡ የባለስልጣን መ/ቤቱን ድርጅታዊ መዋቅር የሚያሳይ መረጃ በአባሪ 3 ተያይዟል፡፡

## በማሪታይም ባለስልጣን የንግድ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክት ጽ/ቤት የሰው ሀይል አደረጃጀት

15.የንግድ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክት ጽ/ቤት (ሞጆ አረንጓዴ ሎጂስቲክስ ማዕከል) በስትሪንግ ኮሚቴው የሚመራ ሲሆን በስሩ አንድ የፕሮጀክት አስተባባሪ እና የፕሮጀክት ምህንድስና አማካሪ፣ 1 ውል አስተዳደር አማካሪ፣ 1 ግዥ አማካሪ፣ 1 የአይ.ሲ.ቲ. አማካሪ፣ 2 የፋይናንስ አማካሪዎች፣ 1 የሴፍጋርድ አማካሪ፣ 1 የክትትልና ግምገማ አማካሪ፣ 1 ረዳት የቢሮ አስተዳደር፣ 1 የንብረት አስተዳደር ሰራተኛና 2 ሹፌሮች በድምሩ 12 ሰራተኞች ይገኛሉ፡፡

## የባለስልጣን መ/ቤቱ የሰው ሃይል

16.ባለስልጣን መ/ቤቱ እስከ ጥር 2016 ዓ.ም 109 ቋሚ እና 3 ኮንትራት በድምሩ 109 ሰራተኞች ያሉት ሲሆን ከዚህ ውስጥ 45 ሴት እና 61 ወንድ ሰራተኞች ናቸው፡፡ እንዲሁም በንግድ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክት ጽ/ቤት እና በሎጂስቲክስ ትራንስፎርሜሽን ጽ/ቤት 26 የኮንትራት ሰራተኞች ያሉ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 6 ሴት እና 20 ወንድ ሰራተኞች ናቸው፡፡

ዝርዝሩም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

| ተ.ቁ | የኢትዮጵያ ማሪታይም ባለስልጣን | በመዋቅር የተፈቀደው የሰው ሃይል | በሥራ ላይ ያለ ቋሚ የሰው ሃይል | | | በሰው ሃይል ያልተሸፈነ ብዛት | በሥራ ላይ ያለ ኮንትራት የሰው ሃይል | | | ምርመራ/ ጠቅላላ የሰራተኛ ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ሴት | ወንድ | ድምር | | ሴት | ወንድ | ድምር | |
| 1 | በኢትዮጵያ ማሪታይም ባለስልጣን መ/ቤት የተመደበ የሰው ሃይል ብዛት | 185 | 45 | 61 | 106 | 84 | - | 3 | 3 | 109 |
| 2 | በማሪታይም ባለስልጣን<br>የንግድ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክት ጽ/ቤት የተመደበ የሰው ሃይል ብዛት | 26 | - | - | - | 13 | 3 | 10 | | 13 |
| | በማሪታይም ባለስልጣን የሎጂስቲክስ ትራንስፎርሜሽን ጽ/ቤት የተመደበ የሰው ሃይል ብዛት | 11 | - | - | - | 11 | 2 | 9 | 11 | 11 |

**የኢትዮጵያ ማሪታይም ባለስልጣን የፋይናንስ ምንጭ፡-**

17.ባለስልጣን መ/ቤቱ የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣትና በእቅድ የያዛቸውን ሥራዎች ለማስፈፀም የሚያስፈልገውን ገንዘብ በየዓመቱ ከመንግስት መደበኛና ካፒታል በጀት እንዲሁም ከብድር የሚያገኝ ሲሆን ከ2014 እስከ ጥር 2016 በጀት ዓመት ድረስ የተመደበለት መደበኛና ካፒታል በጀት፣ እና የብድር ውጪ በሚከተለው ሰንጠረዥ

ተመላክቷል፡፡

| የበጀት ዓ.ም | የበጀት ዓይነት | የፀደቀና የተስተካከለ በጀት (ብር) | ሥራ ላይ የዋለ (ብር) | አፈፃፀም በመቶኛ % |
|---|---|---|---|---|
| 2014 | መደበኛ | 56,185,000 | 53,292,329.41 | 94.85% |
| | ካፒታል | 1,532,490,201 | 858,210,299 | 56% |
| | ከብድር | ------- | ------- | ------- |
| | ጠቅላላ ድምር | **1,588,675,201** | **811,502,628.41** | 57.37% |
| 2015 | መደበኛ | 75,470,433.83 | 67,617,732.89 | 89.6% |
| | ካፒታል | 3,634,445,728.66 | 869,944,745 | 23.9% |
| | ከብድር | ------- | ------- | -------- |
| | ጠቅላላ ድምር | **3,709,916,162,49** | **937,562,477.89** | 25.27% |
| 2016 | መደበኛ | 101,452,000 | 35,606,819.80 | 35% |
| | ካፒታል | 4,401,681,800 | 490,761,990 | 11.14% |
| | ከብድር | ------- | ------- | ------- |
| | ጠቅላላ ድምር | **4,503,133,800** | **526,368,809.8** | 11,7% |

18. የሞጆ ሎጅስቲክስ ማዕከል ፕሮጀክት በ3 ዋና ዋና ተግባራት ማለትም በሞጆ ያለውን መሰረተ-ልማት ማሻሻል፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስርዓቶችን በማጠናከር የተቀናጀ አሰራር እንዲኖር ማድረግ እና የአስተዳደራዊ እና ተቋማዊ (አቅም ግንባታ) ድጋፍ ላይ ትኩረት አድርጎ የሚተገብር ሲሆን የፋይናንስ ምንጩ መንግስት ከዓለም ባንክ ጋር ለፕሮጀክቱ ማስፈፀሚያ የሚውል USD150,000,000 (መቶ ሃምሳ ሚሊዮን) የአሜሪካን ዶላር የብድር ስምምነት መጋቢት 29/2009 ዓ.ም (April-07/2017) ተፈርሟል፡፡
19. ፕሮጀክቱን ለማስፈፀም ከዓለም ባንክ የተገኘው ብድር የሶስቱ የፕሮጀክቱ ክፍሎች በጀት ከዚህ በታች በተቀመጠው ሰንጠረዥ ዝርዝር መሠረት ለተለያዩ ተግባራት የሚውል ይሆናል፡፡

የካፒታል በጀት ዕቅድ ክንውን (በአሜሪካ ዶላር) እስከ 2016 በጀት ዓመት 6 ወር መጨረሻ ድረስ

| ተ.ቁ | ዋና ዋና ተግባራት(ኮምፖነንቶች) | በየካቲት 2009 ተጠንቶ የተመደበ ጠቅላላ ገንዘብ በአሜሪካን ዶላር | ክንውን | |
|---|---|---|---|---|
| | | | ፕሮጀክቱ ከተጀመረ ጀምሮ በዶላር | በመቶኛ |
| 1 | በሞጆ ያለውን መሰረተ-ልማት ማሻሻል (Improvement of infrastructure at Modjo) | 120,000,000 | 67,064,372.95 | 55.89% |
| 2 | የኢንፎርሜሽንቴክኖሎጂስርዓቶችንበማጠንከርየተቀናጀአሰራርእንዲኖር ማድረግ (Enhancing coordination through investments in information technology systems) | 15,000,000 | 425,358.10 | 2.06% |
| 3 | የአስተዳደራዊናተቋማዊ (አቅም ግንባታ) ድጋፍ (Regulatory and Institutional Capacity Buliding) | 15,000,000 | 6,694,449.30 | 44.63% |
| | ድምር | 150,000,000 | 74,184,180.35 | 49.46 |

## የኦዲቱ ዓላማ

20.ባለስልጣን መ/ቤቱ የሚያከናውነው የሞጆ ሎጅስቲክስ ማዕከል ግንባታ ፕሮጀክት በተገባው ውል መሰረት ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ እየተከናወነ ስለመሆኑ፤ ውል የገቡ አማካሪ ድርጅቶች እና ተቋራጮች በገቡት ውል መሰረት እየፈጸሙ ስለመሆኑ እና በሎጅስቲክስ ግንባታ ምክንያት የሚነሱ ንብረቶች ለካሳ ክፍያ አፈፃፀም በወጡ አዋጅ እና ደንብ መሰረት የተፈፀሙ መሆኑን ማረጋገጥ ሲሆን ከዚህ ጋር በተያያዘ የአሰራር ችግሮች ካሉ በመለየት የማሻሻያ ሀሳቦችን በማቅረብ የፕሮጀክት ፅ/ቤቱ የተቋቋመበትን ዓላማ እንዲያሳካ የሚያግዝ ምክረ ሃሳብ ለማቅረብ እና ተጠያቂነትን ለማጠናከር ነው፡፡

## የኦዲቱ አካባቢ (Audit Area)

21.ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ በኢትዮጵያ ማሪታይም ባለሥልጣን የሞጆ ሎጅስቲክስ ማዕከል ፕሮጀክት ግንባታ አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን መገምገም የሚል ነው፡፡

## የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች (audit issue)

22.በተመረጠው የኦዲት አካባቢ (Potential Audit Area) ሥር 4 (አራት) የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issue) ተዘጋጅተዋል፡፡ እነርሱም፦

1. በማሪታይም ባለስልጣን የንግድ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ሞጆ አረንጓዴ ሎጂስቲክስ ማዕከል ግንባታ ፕሮጀክቶች በዓለም ባንክ እና በፌዴራል መንግስት ፕሮጀክቶች አዘገጃጀት መመሪያ መሰረት የተከተለ ማረጋገጥ፤
2. በማሪታይም ባለስልጣን የንግድ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ሞጆ አረንጓዴ ሎጂስቲክስ ማዕከል ግንባታ ፕሮጀክቶች በታቀደለት ጊዜና በጀት መጠናቀቁን እንዲሁም በአካባቢ እና የማህበራዊ ደህንነት ተፅዕኖ ግምገማ መሰረት እየተከናወነ መሆኑን መገምገም፤
3. ባለስልጣን መ/ቤቱ ተቋራጭም ሆነ አማካሪ ድርጅት በገቡት የኮንትራት ውል እና ውሉን መሰረት አድርጎ በተዘጋጀው ቴክኒካዊ የሥራ ዝርዝር ውል መሰረት ግዴታቸውን መወጣታቸውን በቅድመ-ትግበራ፣ በሥራ ሂደት ትግበራ እና ድህረ ትግበራ ወቅት ውጤታማ ክትትልና ቁጥጥር ማድረጉን መገምገም፤
4. የኢትዮጵያ ማሪታይም ባለሥልጣን በሞጆ አረንጓዴ ሎጂስቲክስ ማዕከል ግንባታ ፕሮጀክት ለልማት ተነሽዎች በወቅቱ የካሳ ክፍያ መከፈሉን ማረጋገጥ፤ የሚሉት ናቸው፡፡


## የክዋኔ ኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ

23.የክዋኔ ኦዲቱ የሚሸፍነው ከመጋቢት 29/2009 ዓ.ም (April-07/2017) እስከ ታህሣስ 30/2016 ዓ.ም ባለው ጊዜ የሞጆ ሎጅስቲክስ ማዕከል ፕሮጀክት አፈፃፀምን የተመለከተ ሥራዎችን ነው፡፡ የክዋኔ ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በኢትዮጵያ ማሪታይም ባለሥልጣን መ/ቤት ሆኖ በስሩ የሞጆ ሎጅስቲክስ ማዕከል ፕሮጀክት በሚከናወንበት የንግድ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክት ጽ/ቤት (ሞጆ አረንጓዴ ሎጂስቲክስ ማዕከል) ነው፡፡ በዚህም መሰረት ከባለስልጣን መ/ቤቱ እና ከተመረጠው የሞጆ ሎጅስቲክስ ማዕከል ፕሮጀክት አፈፃፀም ጋር ተያያዥ የሆኑ እና አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች በመከለስ፣ በአካል በመገኘት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ጋር ቃለ-መጠይቅ በማድረግ እና መረጃዎችን መተንተን፣ ዋና ዋናዎቹ የኦዲቱ ስልቶች/ዘዴዎች/ በመጠቀም የክዋኔ ኦዲቱ ተከናውኗል፡፡


## የክዋኔ ኦዲቱ መመዘኛ መስፈርቶች እና የተዘጋጀባቸው ማስረጃዎች


24.በኦዲት ቡድኑ ለተመረጡት አራት ዋና ዋና የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎችን ለመመዘን የሚረዱ 33 (ሠላሳ ሦስት) የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች የተዘጋጁ ሲሆን ዝርዝሩ በአባሪ 1 ተያይዟል፡፡ በመመዘኛ መስፈርቶቹ ላይ የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት የበላይ ኃላፊዎች አስተያየት እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶችን (Evaluative Criteria) ለማዘጋጀት የተከለሱ ሰነዶች/መረጃዎች በአባሪ 2 ተያይዟል፡፡

**የንግድ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክት ጽ/ቤት የአሰራር ስርዓት መገለጫ / system Discription/**



Fund Flow and Report Chart



# ክፍል ሁለት
# የኦዲት ግኝቶች

## I. በማሪታይም ባለስልጣን የንግድ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ሞጆ አረንጓዴ ሎጂስቲክስ ማዕከል ግንባታ ፕሮጀክቶች በዓለም ባንክ እና በፌዴራል መንግስት ፕሮጀክቶች አዘገጃጀት መመሪያ መሰረት የተከተለ መሆኑን ማረጋገጥ

**የሞጆ አረንጓዴ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክት በጥናት ላይ የተመሰረተ የዲዛይንና የግንባታ ውል አስተዳደር በተመለከተ**

25.የሞጆ አረንጓዴ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክት በጥናት ላይ የተመሰረተ የዲዛይንና የግንባታ ውል አስተዳደር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

26.ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች እንደተገኘው ባለስልጣን መ/ቤቱ የሞጆ አረንጓዴ ሎጂስቲክስ ማዕከል ፕሮጀክት ግንባታ ላይ በተደረገ የአማካሪዎች ጨረታ ሴሌሆርን-ኤችፒሲ ጄ.ቪ. / Sellehorn-HPC JV/ አሸናፊ ሲሆን፤ የፍላጎት ትንተና፤ ማስተር ፕላን፤ ዝርዝር ዲዛይን እና የጨረታ ሰነድ አዘጋጅቶ በስድስት ወራት አጠናቆ ለማስረከብ ውል የፈረመ ቢሆንም በውሉ መሰረት ያላከናወነ መሆኑ፤- ለማሳያ ያህል የሚከተሉት ችግሮች ተስተውለዋል፡፡

- (በሴሌሆርን-ኤችፒሲ ጄ.ቪ.) Sellehorn-HPC JV የተሰራ የሎጂስቲክስ መሰረተ ልማት የምህንድስና ዝርዝር ዲዛይን፣ የግንባታ ቁጥጥር እና የውል አስተዳደር አገልግሎቶችን ያላሟላ፤ እንዲሁም ፕሮጀክቱ መጀመሪያ ዓመት ላይ በውሉ መሠረት የተሟላ ዲዛይን ሰርቶ ማስረከብ ያልቻለ መሆኑ፣
- ሴሌሆርን-ኤችፒሲ ጄ.ቪ. /Sellehorn-HPC JV/ ውሉን አቋርጦ ከወጣ በኂላ ዲዛይኑን እንዲሰሩ በመ/ቤቱ በኩል የተወከሉ ባለሙያዎች የሰሩት ዲዛይን ኮንትራክተሩ ሥራውን ለመስራት ወደ ሳይት በገባበት ወቅት ሊያሰራው ያልቻለ መሆኑ፣ ለማሳያ ያህል የመንገድ የሌቭሊንግ ችግር፣ የድሬኔጅ ችግር፣ የፋየርፋይቲንግ እና የእስትራክቸር ችግር እንዲሁም የአካባቢው አፈር የመሰነጣጠቅ እና ወደ ውስጥ የመንሸራተት ባህሪ የነበረበት መሆኑ መገለፁ፣
- ሴሌሆርን-ኤችፒሲ ጄ.ቪ. /Sellehorn-HPC JV/ በሞጆ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክት ከንድፍ ጋር የተያያዙ ችግሮች መኖራቸው ለማሳያ ኦርጂናል የተሳለው ዲዛይን እና ማስተር ፕላኑ የተሟላና ግልጽ አለመሆኑን ነሐሴ 2014 በቀረበው የሂደት ሪፖርት(progress report) የተመላከተ መሆኑ፣

☞ የፕሮጀክቱ የመጀመሪያው አርክቴክቸር ዲዛይን የግንባታ ሳይቱን አጠቃላይ ገጽታ፣ የሎጀስቲክስ ግንባታ ቦታ እና በዙርያው ያሉ ነገሮችን በፍጥነት ለመረዳት የሚያስችለው የድሮዊንግ ርዕስ (drawing Title) የጎደለው መሆኑ፤

☞ በሎጂስቲክስ  መሰረተ ልማት አፈፃፀም የዲዛይንና የግንባታ ፕሮጀክቶች ኮንትራት አስተዳደር ችግር መኖሩ በማሪታይም እና ሎጂስቲክስ ዘርፍ የአምስት ዓመት ስትራቴጅክ ዕቅድ ላይ የተመላከተ መሆኑ፣

☞ አብዛኞቹ የግንባታ ውል ሥዕሎች( contract drawings) የተሟሉ እና ግልፅ ያልሆኑ መሆናቸው፤ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ የሰነድ ማስረጃዎች እና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች ለማወቅ ተችሏል፡፡

27. ስለጉዳዩ የፕሮጀክቱ አማካሪ ድርጅት ኢፕቲሳ ሰርቪስዮስ ዲ ኢንጂነርያ (EPTISA Servicios de Ingeniería, S.L.) ከኦዲት ቡድኑ በቀረበው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ኢፕቲሳ (አማካሪው) ፕሮጀክቱ ከተጀምረ በኋላ ለወራት ዘግይቶ ወደ ሥራ ሲገባ ዲዛይኑ የመንገድ የሌቭሊንግ ችግር፣ የድሬኔጅ ችግር፣ የፋየርፋይቲንግ እና የእስትራክቸር ችግር እንዲሁም የአከባቢው አፈር የመሰነጣጠቅ እና ወደ ውስጥ የመንሸራተት ባህሪ የነበረበት በመሆኑ ሥራውን ሊያስቀጥለን ባለመቻሉ፣ ሥራውን አስቁመን ዲዛይኑ እንደ አዲስ በማስተር ፕላን ተካቶ እንዲሰራ እንዲሁም ጥልቅ የአፈፍር ጥናት ተደርጎ ችግሩን በመቅረፍ ለአሰሪው መ/ቤት ተልኮ ተገምግሞ ይሁንታ ካገኘ በኋላ ነው ወደ ሥራ የተገባው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

28. ስለጉዳዩ ለቻይና ሲቭል ኢንጂነሪንግ ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን (CCECC) የስራ ኃላፊዎች ከኦዲት ቡድኑ በቀረበው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የጀርመኑ ካምፓኒ የሰራቸው ስራዎች የተሟላ እና ወጥነት ያልነበረው እንዲሁም የፕሮጀክት ዲዛይኑ በተለያዩ አካላት መሰራቱ ራሱን የቻለ ችግር ሲሆን፣ በአጠቃላይ ጉድለቶችን በጋራ ሆኖ ገምግሞ እና አርሞ የተሟላ ዲዛይን ተይዞ ወደስራ መግባት ላይ ውስንነት ነበረበት በማለት ገልጸዋል፡፡

29. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የባለስልጣን መ/ቤቱ እና የፕሮጀክቱ ጽ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (fact sheet) እና በኦዲት ቡድኑ በቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ፡-

- በተደረገ የአማካሪዎች ጨረታ ሴሌሆርን-ኤችፒሲ ጄ.ቪ. / Sellehorn-HPC JV/ የበላይ በመሆኑ ውል የተፈራረመ ሲሆን የተሠጡት ዋና ዋና ሥራዎች የሎጂስቲክስ ፍላጎት ትንተና/Demand Analysis/፤የሎጂስቲክስ ማዕከል መዋቅራዊ ንድፍ /Master Plan/፤ዝርዝር የዲዛይን ጥናት /Detailed Engineering Design/፣

የጨረታ ሰነድ ዝግጅት /Tender Document Preparation/ እና የግንባታ ቁጥጥር እና ኮንትራት አስተዳደር ሲሆኑ በስድስት ወራት ለማጠናቀቅ ውል የፈረመ ቢሆንም በ18 ወራት ድረስ ያላጠናቀቀ እና በውሉ መሠረት ዲዛይን ሰርቶ ማስረከብ ያልቻለ መሆኑ፤ እንዲሁም የተከናወነው ስራ በውሉ መሠረት የምህንድስና ዝርዝር ዲዛይን እና የጨረታ ሰነድ ዝግጅት ዝርዝር ጉዱለት የተገኘበት በመሆኑ ተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያ ሲሰጠው ከቆየ በኋላ ውሉ እንዲቋረጥ ተደርጓል፡፡ ላላጠናቀቃቸው ስራዎች የተመደቡ ክፍያዎች ተቀንሰው ለቀሪ ስራዎች ማጠናቀቂያ እንዲውል ተደረጓል፡፡

- ከላይ የተጠቀሱት ጉድለቶች ቢኖሩም አማካሪው በሰራቸው ሥራዎች መሰረት ስራ ተቋራጩ  ወደ ሳይት ሲገባ ስራውን ለመጀመር ችሏል፡፡ ለምሳሌ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ካምፕ፤ ቤተ ሙከራ፤ የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ፤ የግንባታ ቁሳቁሶች ማምረቻ፤ የነዳጅ ማደያ እና የመሳሰሉ ሥራዎችን አከናውኗል እንዲሁም የተዘጋጀው ድሮዊንግ የተሟላና ግልጽ ነው ሲሉ በሰጡት ምላሽ ላይ ገልጸዋል፡፡

30. ባለስልጣን መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎቹ ይህንን መልስ ቢሰጡም የተዘጋጀው ድሮዊንግ የተሟላና ግልጽ አለመሆኑ በ FINAL INCEPTION REPORT July 2022 Page I 62) በግልፅ የተጠቀሰ በመሆኑ የተሰጠው መልስ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡
31. ፕሮጀክቱ መጀመሪያ ዓመት ላይ ውል ያሰረው አማካሪ በውሉ መሠረት ዲዛይን ሰርቶ ማስረከብ አለመቻሉ ስራው በውሉ መሰረት እንዳይከናወን፣ የምህንድስና ዝርዝር ዲዛይን እና የጨረታ ሰነድ ዝግጅት ጉዱለት እንዲታይበት እንዲሁም የፕሮጀክቱ ስራዎች በተጠና ጥልቅ ዲዛይን እና በታቀደለት ጊዜ እንዳይጠናቀቅ አድርጓል፡፡

**ባለስልጣን መ/ቤቱ የሞጆ አረንጓዴ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክትን ዲዛይን መንደፉን በተመለከተ**::

32. ባለስልጣን መ/ቤቱ የሞጆ አረንጓዴ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክትን ሲቀርጽ የፕሮጀክቱን ገፅታ በተገቢው መንገድ የሚሳይ ግልጽ እና የተሟላ ዲዛይን በመንደፍ ስራዎችን ሊያከናውን ይገባል፡፡
33. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ የሰነድ ማስረጃዎች እና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች መሰረት፡-

- ☞ ፕሮጀክቱ ሲቀረፅ የተፈረመው ስምምነት የባቡር ሐዲድ መስመር ዝርጋታ ስራን ያላካተተ መሆኑ፣
- ☞ በሴሌሆርን-ኤችፒሲ ጄ.ቪ. የተሰራዉ ዲዛይን የተፈጥሮ እና የሰው ሰራሽ ገፅታዎች የወንዝ ጅረት እና ጉድጓዶች  የመሳሰሉት በማስተር ፕላኑ ላይ ያላካተተ መሆኑ፣

☞ በወደቡ ውቅር ንድፍ /ማስር ፕላን/ ተንተርሶ ይሰራ የነበረው የአይሲቲ ጥናት የዘገየ መሆኑን፣ ለማወቅ ተችሏል፡፡

34. ስለጉዳዩ ለቻይና ሲቪል ኢንጂነሪንግ ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን (CCECC) የስራ ኃላፊዎች ከኦዲት ቡድኑ በቀረበው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ኮንተራክተሩ መጀመርያ ወደ ሥራ ሲገባ አማካሪ እንዳልነበረው ነገር ግን በአሰሪው መ/ቤት ተወክለው የማማከር ሥራ የሚሰሩ ኢንጂነሮች ነበሩ ሆኖም ግን በመጀመርያም የዲዛይን ችግር በመኖሩ ምክንያት ስራችንን በተፈለገው ደረጃ ሊያሰራን አልቻለም ነበር፤ አሁን ያለው አማካሪ በመ/ቤቱ ከተወከሉት ኢንጂነር ተቀብሎ ወደ ሥራ በገባበት ጊዜ ያሉ ችግሮችን በመቅረፍ እኛም ወደ ሥራ እንድንገባ አድርገናል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

35. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የባለስልጣን መ/ቤቱ እና የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (fact sheet) እና በኦዲት ቡድኑ በቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ፕሮጀክቱ ሲቀረጽ በአማካሪ የተጠና እስከ 2043 ድረስ የሚያገለግል ማስተርፕላን ያለን ሲሆን ነገር ግን የሥራ ተቋራጭ ውል ጋር የተካተቱት የሥራ ዝርዝሮች በበጀት እጥረት ምክንያት የተወሰኑት ብቻ በመሆናቸው ወደ ሥራ ከተገባ በኋላ እንዳስፈላጊነቱ የሚጨመርም ሆነ የሚቀነስ ሥራ በየትኛውም የግንባታ ሥራ ላይ ይኖራል፣ ነገር ግን የወንዝ ጅረት ተከትሎ ያለውን ጎርፍ ለመከላከል በአሁኑ ወቅት የሃይድሮሎጅ ዝርዝር ጥናት እንዲሰራ ተደርጓል በማለት ገልጸዋል፡፡

36. የሞጆ አረንጓዴ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክት ሲቀርጽ የፕሮጀክቱን ገፅታ በተገቢው መንገድ የሚሳይ ግልጽ እና የተሟላ ዲዛይን አለመነደፉ የፕሮጀክቱ ዝርዝር ስራዎች በተቀመጠላቸው የጊዜ ሰሌዳ እንዳይከናወኑ፣ ተጨማሪ ሥራዎችና ወጪዎችን ከማስከተሉ በተጨማሪ በታቀደለት ጊዜ አገልግሎት መስጠት እንዳይችል ያደርገዋል፡፡

**ባለስልጠን መ/ቤቱ በጨረታ ተወዳዳሪዎች ቅድመ-ብቃት ምዘና ማድረጉን በተመለከተ**::

37. ባለስልጣን መ/ቤቱ በጨረታ ተወዳዳሪዎች ላይ ቅድመ-ብቃት /Pre-qualification/ ምዘና ማድረግ ይኖርበታል፡፡

38. ይሁን እንጂ ጉዳዩን አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ ባካሄዳቸው የሰነድ ክለሳዎች መሰረት የሚከተሉት ክፍተቶች ተለይተዋል፡፡

- የፕሮጀክቱ የግምገማ ሰነድ ሲዘጋጅ የጨረታ ቅድመ ብቃት እና ድህረ ብቃት የማወዳደርያ ዘዴዎች እንዳስፈላጊነቱ መጠቀም በሚያስችል መልኩ እቅድ ላይ ሳይካተት የጸደቀ መሆኑ፣

- በሞጆ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክት የTOS/GOS የጨረታ ሂደት በድህረ ብቃት ምዘና /Post Qualification/ መሰረት ጨረታው የተደረገ ቢሆንም ፕሮጀክቱ አሁን ላይ ስራ የጀመረ ቢሆንም መጀመር ከነበረበት ጊዜ በላይ የዘገየ መሆኑ፣ለማወቅ ተችሏል፡፡

39.ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የባለስልጣን መ/ቤቱ እና የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (fact sheet) እና በኦዲት ቡድኑ በቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ በባንኩ የግዥ መርህ መሰረት ቅድመ ብቃት ምዘና /Prequalification/ የተባለ ሁለት እርከን ጨረታ ሂደት (Two stage two envelop) ሲሆን ተመራጭነቱም እጅግ ውስብስብና ገዥው ፍላጎቱን በተሟላ ይዘትና የጨረታ ሃሳብ ተንትኖ መግለጽ በማይችል ጊዜ የተጫራቾችን ግብአት በሁለተኛው የጨረታ እርከን አካትቶ ወደ ጨረታ ሂደት መግባት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የሚተገበር የጨረታ አማራጭ ነው በዚህም መሰረት ሁሉም የፕሮጀክት ግንባታና እቃ ግዥዎች በድህረ ብቃት ምዘና /Post Qualification/ የአንድ እርከን አንድ ፖስታ ( Single stage one envelope) ስርአትን በመከተል ነው የሚፈፀመው በማለት ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም በረቂቅ ሪፖርት መልሳቸው ላይ በግዥ እቅድ ወቅት የተወሰነው ሁሉም ግዥዎች በድህረ ብቃት መዘና እንዲከናወን ሲሆን በቀጣይ ዕቅዶች ሲዘጋጁ ውስብስብ ፕሮጀክቶች ቅድመ ምዘና እንዲካተት ይደረጋል በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

40.የባለስልጣን መ/ቤቱ የስራ ሀላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ በጨረታ ሂደት ወቅት ቅድመ ብቃት ምዘናም ሆነ ድህረ ብቃት ምዘና እንደየ ጨረታው አይነት መጠቀም የሚያስችል በመሆኑ፤ እስካሁን በተደረጉት ጨረታዎች የድህረ ብቃት ምዘና እንጂ በቅድመ ብቃት ምዘና ሂደት ተደርጎ የማይታወቅ በመሆኑ በተለይም የአይቲ ስራዎች ላይ የተደረገው የድህረ ብቃት ምዘና ሲሆን በኦዲቱ ማጠናቀቂ ወቅት የአይቲ ስራው የተጀመረ ቢሆንም እጅግ እንዲዘገይ ያደረገ በመሆኑ እና ስራውም በባህሪው ውስብስብ በመሆኑ የቅድመ ብቃት ምዘና ቢደረግ የተሸለ ውጤት ስለሚያስገኝ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

41.ባለስልጣን መ/ቤቱ ባካሄዳቸው የግዥ ሂደቶች ላይ ድህረ-ብቃት ግምገማ /Post-qualification/ ብቻ መጠቀሙ እና የቅድመ-ብቃት /Pre-qualification/ ምዘና የሚያስፈልጋቸውን የግዥ አይነቶች ለይቶ ተግባራዊ አለማድረጉ የTOS-GOS አይቲ ስራዎችን በጊዜ እንዳይከናወኑ ያደርጋል፡፡

## ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ተቋራጭ እና አማካሪው በውሉ መሰረት ስራቸውን በወቅቱ መጀመራቸውን በተመለከተ

42.ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ተቋራጭ እና አማካሪ ተቋም በውሉ መሰረት ስራቸውን በተቀመጠው

ግዜ መጀመራቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

43. ባለስልጣን መ/ቤቱ በዚሁ መሰረት በውል ስምምነት ልዩ ሁኔታዎች (Particular Condition) ሥራ መጀመሩን የተከታተለ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ፡- የምህንድስና አማካሪው ኢፕቲሳ ሰርቪሲዮስ ዲ ኢንጂነርያ ለአራት ወራት ያህል ዘግይቶ በመግባቱ የግንባታ ስራው እንዲዘገይና የግንባታ ቁጥጥር ስራውም በእቅዱ መሰረት ካልተከናወኑት ተግባራት ውስጥ እንዲሆን ያደረገው መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ የሰነድ ማስረጃዎች እና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፍዎች ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች ለማወቅ ተችሏል፡፡

44. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የባለስልጣን መ/ቤቱ እና የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (fact sheet) እና በረቂቅ ሪፖርት ምላሽ ላይ በሰጡት መልስ በፕሮጀክት ግዥ አተገባበር ተያያዥና ተጣማሪ ስራዎችን በአንድ የትግበራ ሰሌዳ ለማምጣት የትኛው ግዥ መቼ ይጀመር የትኛው ግዥ መቼ ይከተል የሚለው ታስቦበት በግዥ እቅድ ተይዞና ጸድቆ ወደ ግዥ ሂደት ይገባል፡፡ የተደረገውም ይሄው ነው፡፡ ሆኖም ሴሌሆርን ኤች ፒ ሲ ጄቪ ከጥናት ውል በተጨማሪ የግንባታ ወቅት ክትትል ለማድረግ ሁለተኛ ውል ፈርሞ ነበር፡፡ ነገር ግን የመጀመሪያውን ውል ያልሰራ አማካሪ ማስቀጠል ስለማያስፈልግ ሁለተኛው ውል ሳይጀመር እንዲመክን ተደረጓል፡፡ ቀጥሎም የግዥ ዕቀድ በአለም ባንክ ጸድቆ፤ ቢጋር ተዘጋጅቶ ለአማካዎች የፍላጎት መግለጫ ማስታወቂያ ከወጣ በኋላ ለተመረጡ ስድስት ተጫራቾች የፕሮፖዛል ማቅረቢያ ሠነድ ተልኮላቸው ፕሮፖዛላቸው ከተገመገመ በኋላ አማካሪው ከሥራ ተቋራጩ 4 ወር ዘግይቶ ሊቀጠር ችሏል በማለት ገልጸዋል፡፡

45. የሞጆ ሎጀስቲክ የግንባታ ፕሮጀክት በተፈረመው ውል መሰረት አማካሪው ተቋም ስራውን በጊዜ ባለመጀመሩ የሲቭል የግንባታ ስራው እንዲጓተት እንዲሁም አማካሪው በወቅቱ ባለመቀጠሩ ተቋራጩ በሚሰራው ስራዎች ላይ የተጠናከረ ክትትል እንዳይኖር አድርጓል፡፡

**በጨረታ ያሸነፈው ተቋራጭ የግንባታ ግብዓቶች አቅርቦትን በተመለከተ**

46. ባለስልጣን መ/ቤቱ በጨረታ ያሸነፈው ተቋራጭ ለግንባታ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች መፈብረኪያ አቅርቦት ባለቤት መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

47. ይሁን እንጅ በውል ስምምነቱ መሰረት አሸናፊው ተቋራጭ ለግንባታ የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን በማቅረብ ግንባታውን ማከናወን ያለበት ቢሆንም ተቋራጩ የፕሮጀክቱ መዘግየት ምክንያትነት በተደጋጋሚ የሲሚንቶ ግብዓት እጥረትን እንደ ዋና ምክንያት እየተጠቀመበት ያለ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ የሰነድ ማስረጃዎች እና ጉዳዩ

ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች ለማወቅ ተችሏል፡፡

48.ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የባለስልጣን መ/ቤቱ እና የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (fact sheet) እና በኦዲት ቡድኑ በቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ሲሚንቶ ማቅረብ የሥራ ተቋራጩ ኃላፊነት ነው፡፡ ነገር ግን በሃገሪቱ የተከሰተውን የሲሚንቶ እጥረት በመረዳት ሥራ ተቋራጩ ሲሚንቶ እንዲያገኝ አስፈላጊ ጥረት ተደርጓል ፡፡ ስራ ተቋራጩ በውሉ መሰረት ባለማቅረቡ መዘግየት አጋጥሟል፡፡ በዚሁም መሰረት ሲሚንቶ ማቅረብ የሥራ ተቋራጩ ኃላፊነት መሆኑን በማስገንዘብ ለእያንዳንዱ መዘግየት በውሉ ጠቅላላ ሁኔታ አንቀጽ 20 መሠረት የአሰሪው የይገባኛል ማመልከቻ /Employer's Claim/ ለአማካሪው ቀርቧል በማለት በሰጡት መልስ ላይ ገልጸዋል፡፡ የባላስልጣኑ ኃላፊዎች ይህን ቢሉም በውሉ መሰረት ቀርቧል የተባለው የይገባኛል ማመልከቻ ምን እንደደረሰ ማስረጃውን ለኦዲቱ አላቀረቡም፡፡

49.ስራ ተቋራጩ በውሉ መሰረት ለግንባታ የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን በማቅረብ በዕቅድ መሰረት ሥራውን ባለመስራቱ እንዲሁም ባለስልጣን መ/ቤቱ ግብዓት ስለሚያገኝበት ሁኔታ በወቅቱ ችግሮቹ እንዲፈቱ ባለመደረጉ ስራዎቹን ለማጠናቀቅ ከታቀደው ጊዜ አንፃር ሲታይ የደረቅ ወደብ ማስፋፍያ ፕሮጀክቱ እንዲዘገይ አድርጓታል፡፡

**ባለስልጣን መ/ቤቱ የፕሮጀክት አስተዳደር ማኑዋል ማዘጋጀቱንና ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ**

50.ባለስልጣን መ/ቤቱ የፕሮጀክት አስተዳደር ማኑዋል/Project Administrative Manual/ በማዘጋጀት እና በሚመለከተው አካል በማፀደቅ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

51.ይሁን እንጅ በኦዲቱ ወቅት፡-

- በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ቀድሞ ተግባራዊ የሆነው የፕሮጀክት አስተዳደር ማኑዋል/Project Administrative Manual/ ከ6 አመት በላይ የቆየ እና ወቅቱን ያላገናዘበ ሲሆን በእ.ኤ.አ መጋቢት 2021 ተከልሶ የቀረበው ረቂቅ የፕሮጀክት አስተዳደር ማኑዋል /Project Administrative Manual/ ያለ ቢሆንም በሚመለከተው አካል ጸድቆ ወደ ሥራ ያልገባ መሆኑ እንዲሁም በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ተሻሽሎ የቀረበውም ቢሆን ለሚመለከተው አካል ቀርቦ ያልጸደቀ መሆኑ፣
- ስራ ተቋራጩ ሊያቀርብ የሚገባው ማንዋል American Society for Testing Materials (ASTM) Standards, Deutsches Institut for Normung e.V. (DIN) Standards, British Standard (BS), American Concrete Institute(ACI) Standards, ባለመቅረቡ ቴክኒካል ስራዎችን አዛምዶ ማረጋገጥ ያልቻለ መሆኑ፣

በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ የሰነድ ማስረጃዎች እና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች ለማወቅ ተችሏል፡፡

52. ስለጉዳዩ ኢፐቲሳ ሰርቪስዮስ ዲ ኢንጂነርያ (EPTISA Servicios de Ingeniería, S.L.) የፕሮጀክቱ አማካሪ ድርጅት ከኦዲት ቡድኑ በቀረበው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ተሻሽሎም ሆነ ወቅቱን ባገናዘበ መልኩ ተከልሶ የቀረበ የፕሮጀክት አስተዳደር ማኑዋል /Project Administrative Manual/ ባይኖርም ነገር ግን እኛ በራሳችን በሱፐርቪዥን ማንዋል ሥራችንን በመስራት ላይ እንገኛለን ሲሉ ገልጸዋል፡፡
53. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የባለስልጣን መ/ቤቱ እና የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (fact sheet) እና በረቂቅ ሪፖርት ምላሽ መሰረት በፕሮጀክት የመተግበሪያ አመታት ተዘጋጅቶ ወደ ስራ የተገባ ቢሆንም በጊዜያት ሂደት ከሰራተኞች አስተዳደር አዋጅ በማይጣረስ ሁኔታ አሁን ባሉት ባለሙያዎች ለማሻሻል ተደጋጋሚ ጥረቶች ተደርገዋል፣ ሆኖም የከፍተኛ ማኔጅመንት አካላትን ምልከታና አስተያየት ለማስገኘት በየደረጃው የሚደረጉ ግምገማዎች ሳይጠናቀቁ የበላይ ሃላፊዎች በሹመት በተደጋጋሚ የሚቀያየሩ በመሆኑ እንደ አዲስ ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራው ከፍጥነት አንጻር ተግዳሮት ሆኖ ቆይቷል፤ ሆኖም ግን ለቀሪው የፕሮጀክት ጊዜም ቢሆን ስራ ላይ ለማዋል ረቂቁን አሁን ላለው አመራር በማቅረብ ለማጸደቅ ጥረት ይደረጋል በማለት ገልጸዋል፡፡
54. ባለስልጣን መ/ቤቱ የፕሮጀክት አስተዳደር ማኑዋሉን /Project Administrative Manual/ በማዘጋጀት እና በሚመለከተው አካል በማፀደቅ ተግባራዊ ባለመደረጉ የፕሮጀክቶቹ ሥራዎችን በመመሪያና በጥንቃቄ መስራት ላይ ክፍተት እንዲኖር ከማድረጉም በላይ ቴክኒካል ስራዎችን አዛምዶ ለማረጋገጥም ሆነ ለመከታተል አዳጋች ይሆናል፡፡

## II. በማሪታይም ባለስልጣን የንግድ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ሞጆ አረንጓዴ ሎጂስቲክስ ማዕከል ግንባታ ፕሮጀክቶች በታቀደለት ጊዜና በጀት እንዲሁም በአካባቢ እና የማህበራዊ ደህንነት ተፅዕኖ ግምገማ መሰረት እየተከናወነ መሆኑን መገምገም::

**የሞጆ አረንጓዴ ሎጂስቲክስ ማዕከል ግንባታ ፕሮጀክት በዕቅድ በተያዘለት ዋጋ(በጀት) መጠናቀቁን በተመለከተ::**

55. የሞጆ አረንጓዴ ሎጂስቲክስ ማዕከል ግንባታ ፕሮጀክቶት በተገባው የኮንትራት ውል መሰርት በዕቅድ በተያዘለት ዋጋ (በጀት) ሊጠናቀቅ ይገባል፡፡
56. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ጉዳዩን አስመልክቶ በተካሄደ የማስረጃ ክለሳ የሚከተሉት

ክፍተቶች ተለይተዋል፡፡

- ፕሮጀክቱን ለማከናወን በ2013 በጀት ዓመት በዕቅድ የተያዘ 51,597,147.0 የአሜሪካ ዶላር (ሃምሳ አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ዘጠና ሰባት ሺ አንድ መቶ አርባ ሰባት የአሜሪካ ዶላር) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ለፕሮጀክት ሥራ የተከፈለው ክፍያ 7,118,397.5 (ሰባት ሚሊዮን አንድ መቶ አስራ ስምንት ሺ ሶስት መቶ ዘጠና ሰባት ከ50/100) (13.8%) በመሆን ከዕቅድ አንጻር የፋይናንስ አፈፃጸሙ ዝቅተኛ መሆኑ፤
- በ2014 በጀት ዓመት በዕቅድ የተያዘ 44,253,280.0 የአሜሪካ ዶላር (አርባ አራት ሚሊዮን ሁለት መቶ አምሳ ሶስት ሺ ሁለት መቶ ሰማንያ የአሜሪካ ዶላር) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ለፕሮጀክት ሥራ የተከፈለው ክፍያ 24,779,769.64 (ሃያ አራት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሰባ ሰባት ሺ ሰባት መቶ ስልሳ ዘጠኝ ከ65/100 የአሜሪካ ዶላር) (56%) በመሆን ከዕቅድ አንጻር የፋይናንስ አፈፃጸሙ ዝቅተኛ መሆኑ፤
- በ2015 በጀት ዓመት የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስርዓትን በማጠንከር የተቀናጀ አሰራር ለመፍጠር የሚያስችል 6,140,137.89 (ስድስት ሚሊዮን አንድ መቶ አርባ ሺ አንድ መቶ ሠላሳ ሰባት ከ89/100) የአሜሪካ ዶላር ዓመታዊ በጀት ዕቅድ የተያዘ ቢሆንም ከዚህ ውስጥ ስራ ላይ የዋለው የዕቅዱ (0.85%) 51,955.35 (አምሳ አንድ ሺ ዘጠኝ መቶ አምሳ አምስት ከ35/100) የአሜሪካ ዶላር ሲሆን ከዕቅድ አንጻር የፋይናንስ አፈፃጸሙ ዝቅተኛ መሆኑ፤
- በ2015 በጀት ዓመት ለመሰረተ ልማት ስራው የሚሆን ዓመታዊ የበጀት ዕቅድ 59,008,602.83 (አምሳ ዘጠኝ ሚሊዮን ስምንት ሺ ስድስት መቶ ሁለት ከሰማንያ ሶስት) የአሜሪካ ዶላር ሲሆን ከዚህ ውስጥ ስራ ላይ የዋለው የዕቅዱ (26.26%) 15,495,455.73 (አስራ አምስት ሚሊዮን አራት መቶ ዘጠና አምስት ሺ አራት መቶ አምሳ አምስት ከሰባ ሶስት) የአሜሪካ ዶላር በመሆን አፈፃፀሙ ዝቅተኛ መሆኑ፣
- በ2015 በጀት ዓመት የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስርዓትን በማጠንከር የተቀናጀ አሰራር ለመፍጠር የሚያስችል 6,140,137.89 (ስድስት ሚሊዮን አንድ መቶ አርባ ሺ አንድ መቶ ሠላሳ ሰባት ከሰማንያ ዘጠኝ) የአሜሪካ ዶላር ዓመታዊ በጀት ዕቅድ የተያዘ ቢሆንም ከዚህ ውስጥ ስራ ላይ የዋለው የዕቅዱ (0.85%) 51,955.35 (አምሳ አንድ ሺ ዘጠኝ መቶ አምሳ አምስት ከሰላሳ አምስት) የአሜሪካ ዶላር በአጠቃላይ ፕሮጀክቱ የፋይናንስ አጠቃቀሙ ከእቅድ በታች መሆኑ በኦዲቱ ታይቷል፡፡

57. ይህ እንዳለ ሆኖ ፕሮጀክቱ የተሽከርካሪ አጠቃቀም ሲገመገም የሚከተሉት ክፍተቶች ታይተዋል፡-

🙇 የሞጆ አረንጓዴ ሎጂስቲክስ ማዕከል ግንባታ ማስፋፍያ ፕሮጀክት እየተከናወነ የሚገኘው ከአለም ባንክ በተገኘ ብድር ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የፕሮጀክቱ ስራዎች ሲከናወኑ ውጤታማ፣ ወጪ ቆጣቢ መሆን ሲገባው የመኪና ግዥ በሚመለከት ለሲቪል ሥራ በተቀመጠው ውል Bill of Quantity በ Item 01500.5 a,b ላይ እንደተቀመጠው 4ታይፕ A እና 7 ታይፕ B መኪናዎች በድምሩ 11 መኪናዎች መገዛት እንዳለበት እና ከተገዙት 4ታይፕ A መኪናዎች ሁለት ለአሰሪው ተቋም፤ ሁለት ለአማካሪው መሆን እንዳለበት በውሉ የተመላከተ ቢሆንም 4ታይፕ A መኪናዎችን ሁሉንም አሰሪው መ/ቤት የወሰደ መሆኑ፤ በተጨማሪ ታይፕ B 2 አዲስ ፒክአፕ መኪናዎችን አሰሪው ተቋም የወሰደው በመሆኑ ለአማካሪው የሚያስፈልጉ ሁለቱን መኪናዎችን በኪራይ እንዲጠቀም መደረጉ፤ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ የሰነድ ማስረጃዎች እና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች ለማወቅ ተችሏል፡፡ **ዝርዝሩ በአባሪ 8 ተያይዟል፡፡**

**እስከ ሰኔ 30 2015 በጀት ዓመት የፕሮጀክቱ የገንዘብ አጠቃቀም በአሜሪካ ዶላር እና የ2015 በጀት ዓመት የፊዚካል ስራዎች እቅድ አፈፃፀም (በአባሪ 6) ተያይዟል፡፡**

58. ስለጉዳዩ ኢፕቲሳ ሰርቪስዮስ ዲ ኢንጂነርያ (EPTISA Servicios de Ingeniería, S.L.) የፕሮጀክቱ አማካሪ ድርጅት ከኦዲት ቡድኑ በቀረበው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የአማካሪ ምደባ (ቅጥር) መዘግየቱ፣ የአፈር ስራ ዋጋ ዝቅተኛ መሆኑ፣ እንዲሁም ሲሚንቶ በተፈለገው መጠን አለመገኘቱ የፋይናንስ አፈፃጸሙን ዝቅተኛ ያደረገው መሆኑ፤ የመኪና ግዥን በሚመለከት ለሲቪል ሥራ በተቀመጠው ውል Bill of Quantity በ Item 01500.5 a,b ላይ እንደተጠቀሳው 4(ታይፕ)አይነት A እና 7 (ታይፕ)አይነት B መኪናዎች በድምሩ 11 መኪናዎች መገዛት እንዳለበት እና ከተገዙት 4(ታይፕ)አይነት A ሁለት ለአሰሪው ተቋም ሁለት ለአማካሪው መሆን እንዳለበት በውሉ የተመላከተ ቢሆንም ነገር ግን አሰሪው መ/ቤት 4ቱንም (ታይፕ) አይነት A መኪናዎችን እና 2 ታይፕ/አይነት B አዲስ ፒክአፕ መኪናዎችን በድምሩ 6 መኪናዎች ሲወስድ አማካሪው በውል መሰረት 7 መኪናዎች የተፈቀዱለት በመሆኑ 2ቱን ቀሪ መኪናዎችን በኪራይ እንድንጠቀም ተደረጓል ሲሉ በሰጡት ምላሽ ላይ ገልጸዋል፡፡

59. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የባለስልጣን መ/ቤቱ እና የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (fact sheet) እና ለረቂቅ ሪፖርት ላይ በሰጡት መልስ፡-

☞ የአማካሪ ቅጥሩ ከታሰበው ጊዜ በላይ መውሰዱ፣ የማሽነሪዎች ግዥ በ6 ወሩ መጨረሻ ከነበረበት የ Rubber tyred gantry cranes (RTG ) እና rail mounted gantry (RMG እና RTG) የግዥ ሂደት ላይ በተነሳው ከብር ወደ ዶላር ምንዛሪ

ይቀየርልኝ ውይይት ከታሰበው ጊዜ በላይ ረጅም ጊዜ መውሰዱ፣የሲቪል ግንባታ የጨረታ ሂደት ባጋጠመው መዘግየት ወደ 42 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ገደማ ተጨማሪ ማሳየቱ፣ እንዲሁም ተጨማሪ ወጭ በገንዘቡ ልዩነት ዙሪያ በሚደርጉ ውይይቶችና ኮንትራክተሩ ከጨረታ ሰነዱና ካቀረበው ፕሮፖዛል በተለየ ባነሳው የምንዛሪ እና ሌሎች ጥያቄዎች ምክንያት ውል የመፈራረም ሂደቱ ረጅም ጊዜ መውሰዱ የፋይናንስ አፈፃፀሙንም ዝቅ እንዲል አድርጎታል፡፡

- በተጨማሪም የግብዓት ማምረቻ ቦታዎች (የጠጠርና ምርጥ አፈር) እንዲሁም የልል ትርፍ አፈር መድፊያ ስፍራዎች ለማግኘት ረጅም ጊዜ መውሰዱ፣ የኤሌክትሪክ፣ የባቡር፣ የስልክ እና የውሃ መስመሮችን ለማስነሳት ረጅም ጊዜ መጠየቁ፣ የግንባታ ቦታውን የይዞታ ካርታ ለማግኘት ጊዜ መውሰዱ፣ የተርሚናል ኦፕሬሽን ሲስተም/የጌት ኦፐሬቲንግ ሲስተም የጨረታ ሂደት በተደጋጋሚ መራዘሙ እና የ Port Community System (PCS) ስራው መጓተቱ እንዲሁም ከሲሚንቶ አቅርቦት ችግር ጋር በተገናኘ የግንባታ ስራው አፈፃፀም ዝቅተኛ መሆኑ እና የወደብ መሳሪያዎች (RTG-RMG) የክፍያ ጥያቄ በወቅቱ ተሟልቶ ባለመቅረቡ የፋይናንስ አፈፃፀሙንም ዝቅ እንዲል አድርጎታል፡፡
- ፕሮጀክት ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግባቸው መኪናዎች ብዛት እና አይነት በጨረታ ሠነድ ዝግጅት ወቅት የተወሰነ ሲሆን (4 ታይፕ/አይነት A እና 7ታይፕ/አይነት B-ፒካፕ)፣ በጨረታ ሠነድ ሲቀመጥም የሌሎች ፕሮጀክቶችን ልምድ ግምት ውስጥ ያስገባ መሆኑ እንዲሁም ፕሮጀክቱ ሲያልቅ ለመንግስት ሊሰጡ ከሚችሉት ጥቅም አንጻር ውሳኔው ተገቢ ነው ብለን እናምናለን ሲሉ በሰጡት መልስ ገልጸዋል፡፡

60.የባለስልጣን መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎቹ ይህንን መልስ ቢሰጡም፤

- ✓ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በተገቢው መልኩ የግንባታ ስራው በተያዘለት እቅድ እና በተሻለ የፋይናንስ አፈፃፀም እንዲጠናቀቅ የሚያስችል በቂ ስራዎችን ሰርቷል ለማለት የማይቻል በመሆኑ፣
- ✓ አሰሪው መ/ቤት ከውል ውጭ 4ታይፕ/አይነት A መኪና፣ 2 ታይፕ/ አይነት B አዲስ ፒክአፕ እና 1መኪና በኪራይ አጠቃላይ በቁጥር 7 መኪናዎች በፕሮጀክት ስም ከፕሮጀክቱ አላማ ውጭ የሚጠቀሙ መሆኑ አግባብነት የሌለው መሆኑ፤ የፕሮጀክቱ አላማ በፕሮጀክቱ ገንዘብ መኪና ገዝቶ ለመንግስት ማስተላለፍ ባለመሆኑ እና ይህም ከፕሮጀክቱ አላማ አንፃር ውሳኔው ተገቢ ነው መባሉ በኦዲቱ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

61.ፕሮጀክቱ የሚሰራው ከአለም ባንክ በተገኘ ብድር በመሆኑና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ

መተግበር ያለበት እና ፕሮጀክቱ የሚሰራው አንድ ቦታ/ሳይት/ ላይ እንደመሆኑ አላስፈላጊ ወጪ ማብዛት የተመደበው የፕሮጀክቱ ገንዘብ ለተባለለት አላማ በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዳይውል ከማድረጉም ሌላ ፕሮጀክቱ የተሻለ አፈፃፀም እንዳይኖር ያደርጋል፡፡

**የሞጆ አረንጓዴ ሎጂስቲክስ ማዕከል ግንባታ ፕሮጀክቶች በዕቅድ በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ መሰራቱን በተመለከተ**

62.የሞጆ አረንጓዴ ሎጂስቲክስ ማዕከል ግንባታ ፕሮጀክት በተገባው የኮንትራት ውል መሰረት በዕቅድ በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ ሊጠናቀቅ ይገባል፡፡

63.ይሁን እንጂ ጉዳዩን አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ ባካሄዳቸው የሰነድ ክለሳዎች መሰረት የሚከተሉት ክፍተቶች ተለይተዋል፡፡

- ፕሮጅክቱ እ.ኤ.አ መጋቢት 2017 ተጀምሮ ሐምሌ 2023 ይጠናቀቃል ተብሎ የታቀደ ቢሆንም በይፋ ስራ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ እስከ 2016 የሁለተኛው ሩብ በጀት ዓመት ድረስ ጠቅላላ የፕሮጀክቱ አፈጻጸም 61.51% ብቻ በመሆኑ ከዕቅድ አንፃር ሲታይ ፕሮጀክቱ የዘገየ መሆኑ፤
- የመሰረተ-ልማት ማሻሻያ ስራው በ2013 በጀት ዓመት መጨረሻ ከደረሰበት 30.92% የክንውን አፈፃፀም በበጀት ዓመቱ 15.82% በማከናወን አጠቃላይ ስራውን 46.74% ለማድረስ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም በበጀት አመቱ 2.31% ብቻ የተከናወነ መሆኑ፣
- በሞጆ ደረቅ ወደብ የሚከናወነው የመሰረተ ልማት ማስፋፊያ ስራ በ2014 በጀት ዓመት መጨረሻ ከደረሰበት 33.23% በ2015 በበጀት ዓመት 30.06% በማከናወን በበጀት ዓመቱ መጨረሻ 63.29% ለማድረስ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም በበጀት ዓመቱ 17.53% ብቻ ተከናውኖ አጠቃላይ አፈጻጸሙ ዝቅተኛ መሆኑ፣
- በሎጂስቲክስ መሰረተ ልማት አፈፃፀም የምህንድስና ግዥ ክፍተት መኖሩ፣ ለማሳያ፡- በ2013 በጀት ዓመት የሲቪል ግንባታ የግዥ ሂደት ተጠናቆ የግንባታ ስራው 8.3% ይጠናቀቃል ተብሎ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም የግዥ ሂደቱ በታሰበው ጊዜ ያልተጠናቀቀ መሆኑ እና የግንባታ ስራውም የዘገየ መሆኑ፣
- በ2014 በጀት ዓመት የሲቪል ግንባታ የጨረታ ሂደት ተጠናቆና ውል ተፈርሞ የግንባታ ስራው በበጀት ዓመቱ 18.21% ይደርሳል ተብሎ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም 3% ብቻ የተከናወነ መሆኑ፣
- በ2015 በጀት ዓመት የሲቪል ግንባታ ስራ ከነበረበት 2.5% በበጀት ዓመቱ ውስጥ 33.72% በማከናወን 36.22% ለማድረስ ታቅዶ 23.80% ብቻ የተከናወነ በመሆኑ አፈፃፀሙን ዝቅተኛ መሆኑ፣

- የአይ.ሲ.ቲ. መሰረተ-ልማት ማስፋፋትን በተመለከተ፡-
    - የተለያዩ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ ስራዎችን በማከናወን በዘርፉ ያለውን ቅንጅታዊ አሰራር ለማሻሻል ስራው በ2014 በጀት ዓመት ከደረሰበት 42.04% በ2015 በጀት ዓመት 23.24% በማከናወን 65.28% ለማድረስ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም በበጀት ዓመቱ 2.09% ብቻ ተከናውኖ አጠቃላይ አፈጻጸሙ ዝቅተኛ መሆኑ፡፡
    - የTerminal Operating System (TOS)፣ Gate Operating System (GOS) እና የPort Community System (PCS) በ2014 በጀት ዓመት 4.62 ለማከናወን ታቅዶ አመታዊ አፈፃፀሙ ዜሮ መሆኑ፣
    - የTOS-GOS ስራው እንዲሰጠው ከተደረገው JV CCECC, with Huadong Electron and CSI እ. አ .አ ጁላይ(ሐምሌ) 5 2023 የውል ስምምነት የተደረገ ቢሆንም ውሉ ተፈርሞ አምስት ወር ያለፈው ሲሆን ስራው ግን በአግባቡና በውሉ መሰረት እየተከናወነ አለመሆኑ እና ተገቢ ክትትል ያልተደረገበት መሆኑ፤
    - ከፕሮጀክቱ ሰራተኞች ወደ ተጫራጮች የTOS-GOS ሚስጥራዊ መረጃዎች ሾልከው በመውጣታቸው እስኪጣራ ድረስ በሚል ሰበብ የውል ስምምነት ከሚገባው በላይ መዘግየቱ በ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ ሪፖርት ላይ የተመላከተ መሆኑ፡፡
- የፕሮጀክቱን ግዥዎች ለማከናወን የተቀመጡ የግዥ ሂደቶች የሚወስዱት ጊዜ ከታሰበው በላይ የፕሮጀክቱን የትግበራ ጊዜ ማራዘሙ እና የግዥ ሂደቱ ሊወስድ የሚችለው ጊዜ ግንዛቤ ውስጥ አለመግባቱ በፕሮጀክቱ አፈፃፀም ላይ ተፅዕኖ የፈጠረ መሆኑ እንዲሁም የሎጂስቲክስ መሰረተ ልማት ግንባታ ፕሮጀክቶችን በውላቸው መሰረት ማጠናቀቅ አለመቻሉ በአስር አመቱ መሪ እቅድ እንደ ድክመት የተቀመጠ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ የሰነድ ማስረጃዎች እና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች ለማወቅ ተችሏል፡፡

64. ስለጉዳዩ ኢፕቲሳ ሰርቪስዮስ ዲ ኢንጂነርያ (EPTISA Servicios de Ingeniería, S.L.) የፕሮጀክቱ አማካሪ ድርጅት እና የቻይና ሲቭል ኢንጂነሪንግ ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን (CCECC) የስራ ኃላፊዎች ከኦዲት ቡድኑ በቀረበው ቃለ መጠይቅ ላይ በሰጡት መልስ የሲሚንቶ አቅርቦት ችግር፣ የዲዛይን ችግር፣ ከሚያዝያ ጀምሮ ሀይለኛ ዝናብ መኖር፤ የወሰን ማስከበር ችግር እንዲሁም አማካሪው ድርጅት ዘግይቶ ሥራ መጀመሩ ፕሮጀክቱ በተገባው የኮንትራት ውል መሰረት በታቀደለት የጊዜ ሰሌዳ እንዳይጠናቀቅ አድርጓታል

ሲሉ ገልጸዋል፡፡

65.ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የባለስልጣን መ/ቤቱ እና የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (fact sheet) እና በኦዲት ቡድኑ በቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ፡-ለፕሮጀክቱ መዘግየት የሚከተሉት ምክንያቶች ዋና ዋና ናቸው፡-

- በግንባታው የመጀመሪያ ወቅት አማካሪ መሃንዲስ የመቅጠር ሂደት እክል ስለገጠመው ሥራ በፍጥነት ለማስጀመር ባለመቻሉ፣ በገበያው ላይ የሲሚንቶ እጥረት በማጋጠሙ፤በሳይቱ ውስጥ የነበሩ የኃይል፤ የውሃ፤ የስልክ፤ የባቡር መሰረተ ልማቶች ማስነሳት የራሱ ጊዜ መውሰዱ፣ በካባ ድንጋይ ቦታዎች፤ በምርጥ አፈር ማምረቻ እና ትርፍ ልል አፈር መድፊያ ሥፍራዎች ላይ በተለያየ ጊዜ እንቅፋት የሚፈጥሩ አካላት በማጋጠማቸው እና ተጫራቾች ፕሮፖዛል ማስገቢያ ቀን እንዲራዘም በመጠይቁ፣ ውጤት ከተለጠፈ በኃላ ቅሬታ ሲቀርብ ቀሬታውን ለመፍታት ረዥም ጊዜ በመውሰዱ፣
- የዲዛይን ስራው ላይ በነበረው የአማካሪ አቅም ማነስ እና ስራውን በውሉ መሰረት ባለማጠናቀቁ ይህንን ለማስተካከል የወሰደው ጊዜ የተራዘመ መሆኑ፤
- የToS/GoS የጨረታ ሂደት በተደጋጋሚ መራዘሙ እና የ PCS ስራው መጓተቱ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚከሰቱ ጦርነቶች ምክንያት በተፈጠረ የዋጋ ንረት ምክንያት የመጣ የዋጋ ጭማሪ ያስከተለው የበጀት እጥረት፣ እንዲሁም የግንባታ ቦታው በግለሰቦች እጅ የነበረ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ቦታውን ለግንባታ ምቹ ለማድረግ የወሰደው ጊዜ መራዘሙና የሲሚንቶ እና የውጭ ምንዛሬ እጥረት እንዲሁም ሌሎች ዓለም ዐቀፍ ተለዋዋጭ ሁኔታዎች የተነሳ የዕቃዎች ዋጋ በመናሩ እና በአበዳሪው መስፈርት መሠረት ከ18 ወር በላይ ለሆነ ውል የዋጋ ማስተካከያ ስለሚደረግ የወጪ ጭማሪ በማሳየታቸው ምክንያት የፕሮጀክቱ ስራዎች በተቀመጠለት የጊዜ ሰሌዳ እንዳይጠናቀቅ እና ከመጠን በላይ እንዲዘገይ አድርጎታል ሲሉ በሰጡት ምላሽ ላይ ገልጸዋል፡፡

66.የባለስልጣኑ የስራ ሀላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ችግሮችን ለመፍታትና የተፋጠነ ምላሽ ለመስጠት የትኩረት ማነስ ችግር የሚታይበት በመሆኑ እንዲሁም ለሚደረጉ የጨረታ ፕሮግራሞች ብዙ ጊዜ እና ገንዘብ የወጣበት ቢሆንም ነገር ግን ያመጣው ለውጥ ባለመኖሩ የተሰጠውን ምላሽ በኦዲቱ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

67.በባለስልጠን መ/ቤቱ የሚገነባው የሞጆ ሎጀስቲክ ግንባታ ፕሮጀክት በዕቅድ በተያዘለት ጊዜ ተገንብቶ አለመጠናቀቁ በፕሮጀክቱ ሊሰሩ የታቀዱት ሥራዎች ተጠናቅቀው አገልግሎት እንዳይሰጡ በማድረግ ከሀገራችን በፍጥነት ማግኘት ያለባትን የኢኮኖሚ

እድገት እንዳታገኝ እና በወጪ እና ገቢ እቃዎች አገልግሎት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዲኖር ከማድረጉም ሌላ የመልካም አስተዳደር ችግር እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡

**የሞጆ ሎጂስቲክስ ግንባታ ፕሮጀክት ትግበራ ሴቶች እና አካል ጉዳተኞችን ማካተቱን በተመለከተ፡፡**

68.የሞጆ ሎጂስቲክስ ግንባታ ፕሮጀክት ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞችን እና ድጋፍ የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎችን አካታች ባደረገ መልኩ ሊተገብር ይገባል፡፡

69.ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በዚሁ መሰረት ስለ መፈፀሙ ኦዲት ሲደረግ፡-

- ፕሮጀክቱ ሲቀረፅ በፕሮጀክት ጥናት ጀምሮ በፕሮጀክት ትግበራና አፈፃፀም ወቅት በእያንዳንዱ የሥራ ሂደት ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞች እና ድጋፍ የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎችን አካትቶ ተግባራዊ ለማድረግ በዕቅድ ያልተካተተ መሆኑ እና በአፈፃፀሙ ወቅትም ከዚህ አንፃር ስለመገምገሙ ማስረጃው ለኦዲት ያልቀረበ መሆኑ፤ እንዲሁም በፕሮጀክቱ ውስጥ የሚቀጠሩ አማካሪና ተቋራጮች ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞች እና ድጋፍ የሚሹ የህብረተሰብ እንዲያካትቱ የሚያስገድድ አንቀፅ በውላቸው ውስጥ ያልተካተተ መሆኑ፤
- ፕሮጀክቱ በሚተገበርበት ቦታ በህዳር 16/2016 በስራ ተቋራጩ ያሉ አጠቃላይ የሰው ሀይል ሰራተኞች ቁጥር 764 ሲሆን አንድ ኪ-እስታፍ የአካል ጉዳተኛ እንዲሁም በቁጥር 33 የሴት ሰራተኞች ያሉ ቢሆንም በተፈለገዉ መጠን የሴቶችን እና የአካል ጉዳተኞች ተሳትፎ ከወንዶች ጋር ሲነፃፀር 4.3% እና 0.1% ሲሆን ቁጥራቸዉ ዝቅተኛ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ የሰነድ ማስረጃዎች እና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች ለማወቅ ተችሏል፡፡

70.ስለጉዳዩ ለቻይና ሲቭል ኢንጂነሪንግ ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን (CCECC) የስራ ኃላፊዎች ከኦዲት ቡድኑ በቀረበው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ በባለሙያ ደረጃ አንድ ኪ-እስታፍ የአካል ጉዳተኛ አለን እንዲሁም በቂ ሴት ባለሙያዎች አሉን ብለን እናምናለን ነገር ግን ቁጥራቸው ከወንዶች ጋር ሲነፃፀር ቁጥራቸው አነስተኛ ነው ይህ ደግሞ የሆነበት የስራው ባህሪ ለሴቶች ምቹ ባለመሆኑ ነው በማለት ገልጸዋል፡፡

71.ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የባለስልጣን መ/ቤቱ እና የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (fact sheet) እና በኦዲት ቡድኑ በቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የፕሮጀክቱ የስራ ባህሪ በጣም አድካሚ እና አሰልቺ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ምንም እንኳን በተፈለገዉ መጠን የሴቶችን እና የአካል ጉዳተኞች ተሳትፎ ከወንዶች ጋር ሲነፃፀር ዉስንነት ያለዉ እና ቁጥራቸዉ የተፈለገዉን ያህል ባይሆንም በቀጣይ የአካል ጉዳተኛች እና የሴቶች ስራተኞች ቁጥር ለማሻሻል ጥረት እናደርጋለን

በማለት ገልጸዋል።

72.የባለሥልጣኑ የሥራ ሃላፊዎች ይህን ቢሉም ሴቶችና አካል ጉዳተኞች በየትኛውም አድካሚና አሰልች የሥራ ባህሪ ውስጥ የመስራት ብቃት ያላቸው በመሆኑ እና የሥራ ቦታ ላይ ደህንነታቸው ተጠብቆ በብቃት እንዲሰሩ እድል እንዲመቻችላቸው አለመደረጉ የትኩረት ማነስ በመሆኑ የሰጡት መልስ ተገቢ ነው ለማለት አይቻልም።

73.በሞጆ ሎጂስቲክስ ግንባታ ፕሮጀክት ከፕሮጀክቱ አላማ ጋር ተያይዞ ሴቶችን፣ አካል ጉዳተኞን እና ድጋፍ የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎችን ባካተተና ተጠቃሚ መሆናቸውን የሚያረጋገጥ መልኩ ባለመሰራቱ የህብረተሰቡ ግማሽ አካል የሆኑትን ሴቶችን፣ አካል ጉዳተኞችንና ድጋፍ የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎችን ከፕሮጀክቱ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ከማድረጉም በላይ በብድር የሚሰራው ፕሮጀክት ከፋይ የሆኑትን የህብረተሰብ ክፍል አለማካተቱ ፍትሃዊነትና ተጠቃሚነታቸው እንዳይከበር፤ በፕሮጀክት ፅ/ቤት፣ በስራ ተቋራጩ እና በአማካሪ ድርጅቱ ሴቶች እና አካል ጉዳተኞች ልዩ ድጋፍ እንዳያገኙ በማድረግ መንግስት በቀጣይ የልማት ዕቅድ (SDG) የያዘውን የሴቶችና አካል ጉዳተኞች ተሳትፎ እንዳይሳካ አስተዋፅኦ ያደርጋል።

## III. ባለስልጣን መ/ቤቱ ተቋራጭም ሆነ አማካሪ ድርጅት በገቡት የኮንትራት ውል እና ውሉን መሰረት አድርጎ በተዘጋጀው ቴክኒካዊ የሥራ ዝርዝር ውል መሰረት ግዴታቸውን መወጣታቸውን በቅድመ-ትግበራ፣ በሥራ ሂደት ትግበራ እና ድህረ ትግበራ ወቅት ውጤታማ ክትትልና ቁጥጥር ማድረጉን በተመለከተ፡፡

### በጨረታ ወቅት ለውድድር የሚቀርቡ የቴክኒካል አፈፃፀምን በተመለከተ

74.ባለስልጣን መ/ቤቱ በቅድመ-ጨረታ ሂደት ወቅት ተጫራቶች ከሚያቀርቧቸው የመጫረቻ ሰነዶች በተጨማሪ ያለውን ቁልፍ የሰው ኃይል፣ የግንባታ ማቴሪያል የፋይናንስ አቅም እና ልምዳቸውን መሰረት በማድረግ የግንባታ አፈጻጸም ብቃታቸውን ቀደም ሲል ከሰሩባቸው ሀገራት አሰሪዎች ቅድመ-አፈጻጸም መረጃ በበቂ ሁኔታ በማሰባሰብ ሊገመግም እና ሊያረጋግጥ ይገባል::

75.ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

- ስራ ተቋራጩ የተወሰኑ ለመሬት ጥናት የሚያገለግሉ መሳሪያዎችን (Survey Equipment’s) ያቀረበ ቢሆንም በስምምነቱ እንደሚያስፈልገው መጠን ሙሉ ማቅረብ ያልቻለ መሆኑ፣

- በአሰሪው እና በስራ ተቋራጭ መካከል በተደረገው የውል ስምምነት ከፕሮጀክቱ መጠን አንፃር የአማካሪ ፋሲሊቲዎች ላይ ውስንነት ያለው መሆኑ ለምሳሌ በቂ ቢሮዎች የሌለው መሆኑ፣
- በስራ ተቋራጩ መቅረብ የነበረበት የፕሎተር(Plotter) ማሽን መቅረብ ከነበረበት ጊዜ በጣም ዘግይቶ የቀረበ መሆኑ፣
- ስራ ተቋራጩ ለግንባታ የሚያስፈልግ ሲሚንቶ በማቅረብ ሥራውን በዕቅዱ መሰረት እየሰራ አለመሆኑ፣
- ተጫራች ለውድድር ሂደቱ የሚያቀርቧቸውን ሰነዶች ብቻ በመመልከት ለውድድሩ ብቃት ያላቸው መሆኑን ከግንዛቤ ከመውሰድ ባሻገር ባቀረቧቸው ሰነዶች መሰረት ሥራውን ከሰሩባቸው ሀገራት ስለነበራቸው አፈፃፀም የማረጋገጥ ሥራ በተወሰኑ አቅራቢ ተጫራቾች ላይ የተሰራ ቢሆንም በፊት ስራ ላይ በነበሩ ሴሊሆርን እና አሁንም ስራ ላይ ባሉ ኢፕቲሳ በመሳሰሉ ተጫራቾች ላይ የማረጋገጥ ስራ አለመሰራቱ፣

በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ የሰነድ ማስረጃዎች እና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች ለማወቅ ተችሏል፡፡

76. ስለጉዳዩ ኢፕቲሳ ሰርቪስዮስ ዲ ኢንጂነርያ (EPTISA Servicios de Ingeniería, S.L.) የፕሮጀክቱ አማካሪ ድርጅት ከኦዲት ቡድኑ በቀረበው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የተወሰኑ ማሽኖች ዘግይተው ከመቅረባቸው ውጭ የስራ ተቋራጩ ቴክኒካልም ሆነ ፋይናንሻል አቅሙ ሥራውን ለመስራት ከሚያስችለው በላይ ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡
77. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የባለስልጣን መ/ቤቱ እና የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (fact sheet) እና በኦዲት ቡድኑ በቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ሥራ ተቋራጩ ያቀረባቸው የላብራቶሪ መሣሪያዎች በማጓጉዝ ሂደት በአንድ ዙር ተጠቃለው ያልገቡ ቢሆንም በሂደት ተሟልተዋል፡፡ የፕሎተር(Plotter) ማሽን እቃው አገር ውስጥ ባለመገኘቱ አቅርቦቱ ዘግይቷል፡፡ ሆኖም እስከዚያ ድረስ በሥራ ተቋራጩ ወጪ ገበያ ላይ ፕሪንት ሲደረግ ቆይቷል፡፡ አሁን ላይ ፕሎተሩ ተገዝቶ በስራ ላይ ይገኛል፡፡ ሲሚንቶን በተመለከተ ተቋራጩ ውል የገባባቸው የሲሚንቶ ፋብሪካዎች በውላቸው መሰረት ማቅረብ ባለመቻላቸው የሲሚንቶ እጥረቱ ሊያጋጥም ችሏል ሲሉ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡
78. ባለስልጣን መ/ቤቱ የሎጅስቲክ ግንባታ ፕሮጀክቶችን በጨረታ ሂደት በሚያወዳድርበት ወቅት ተጫራች ለውድድር ሂደቱ የሚያቀርቧቸውን ሰነዶች ብቻ በመመልከት ለውድድሩ ብቃት ያላቸው መሆኑን ከግንዛቤ ከመውሰድ ባሻገር ባቀረቧቸው ሰነዶች

መሰረት ሥራውን ከሰሩባቸው ሀገራት ስለነበራቸው አፈፃፀም የማረጋገጥ ሥራ የሚሰሩ ቢሆንም በፕሮጀክቱ ጅማሮ ወቅት በሴሌሆርን-ኤችፒሲ ጄ.ቪ.)Sellehorn-HPC JV እና በአሰሪው ተቋም ላይ በለመከናወኑ በአሰሪው ተቋምና በተጫራቾች መካከል ልዩነትን እና ቅሬታን ከማስከተሉ በላይ ውሉ እንዲቋረጥ አድርጓል፡፡ እንዲሁም ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች በወቅቱ ተጠናቀው አለመግባታቸው ፕሮጀክቱ በታቀደለት ጊዜ ላለመጠናቀቅ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡

## የፕሮጀክት ስትሪንግ ኮሚቴን በተመለከተ

79.የፕሮጀክት ስትሪንግ ኮሚቴው ለፕሮጀክቱ አፈፃፀም የሚረዱ የፖሊሲ አቅጣጫዎችን ሊያመላክት፣ ዕቅድ እና በጀትን ገምግሞ ሊያፀድቅ እንዲሁም የፕሮጀክቱን አፈፃፀም በበላይ ሆኖ ሊከታተል እና ሊገመግም ይገባል፡፡

80.ይሁን እንጂ ጉዳዩን አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ ባካሄዳቸው የሰነድ ክለሳዎች መሰረት የሚከተሉት ክፍተቶች ተለይተዋል፡-

- የፕሮጀክት ስትሪንግ ኮሚቴ የፕሮጀክቱን እንቅስቃሴ ላይ በተወሰነ መልኩ ክትትል ያደረጉ ቢሆንም ነገር ግን እቅድን መሰረት ባደረገና ወጥነት ባለው መልኩ በመስክ ላይ በመገኘት የፕሮጀክቱ ተግባራት ያሉበትን ደረጃ ገምግሞ አቅጣጫዎችን የማስቀመጥ እና የውሳኔ ሃሳብ መስጠት ላይ ክፍተት ያለበት መሆኑ፣
- ስትሪንግ ኮሚቴው ለፕሮጀክቱ ጠቀሜታ ሲባል ከተለያዩ አካላት ጋር ቋሚ የሆነ የትብብር ግንኙነቶች እንዲኖር ያላደረገ መሆኑ እና የፕሮጀክቱ ስራዎች በጊዜው እንዲከናወኑ የፖሊሲ አቅጣጫዎችን ያላስቀመጠ እንዲሁም የፕሮጀክቱን ባለድረሻ አካላት/stakeholders/ በተፈለገው ጊዜ በአንድ ላይ መገኘት አለመቻልና ፕሮጀክቱ ላይ ባጋጠሙ ችግሮችና መፍትዎቻቸው ዙሪያ በጋራ መወያየት ያልተቻለ መሆኑ፤
- የፕሮጀክት አስተባባሪ ኮሚቴው (PSC) የፕሮጀክቱን ስራዎች በበላይ ሆኖ ለመገምገም፣ ቁጥጥር እና ክትትል ለማድረግ እንዲሁም የዓመታዊ የሥራ ዕቅዶችን እና በጀትን ለማፅደቅ በመደበኛነት የማይሰበሰብ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ የሰነድ ማስረጃዎች እና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች ለማወቅ ተችሏል፡፡

81.ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የባለስልጣን መ/ቤቱ እና የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (fact sheet) እና በኦዲት ቡድኑ በቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የፕሮጀከት ስትሪንግ ኮሚቴ በሚኒስትሮች እና በከፍተኛ አመራሮች የተወከለ ከመሆኑ አንጻር የተፈለገውን ያክል በመደበኛነት መሰብሰብ ባይችሉም ስብሰባ ያደርጋሉ፡፡ የመስክ ጉብኝትም ያደርጋሉ፡፡ በሰሜኑ ጦርነት እና በኮቪድ 19 ምክንያት

በዚያ ወቅት መደበኛ ስብሰባ ማድረግ አስቸጋሪ ነበር፡፡ ነገር ግን በቨርቹዋል ተከናወኗል፡፡ አንዳንዴ ደግሞ የአመራር ለውጥ በሚኖር ጊዜ አዲስ አመራር እስከሚተካ ድረስ ስብሰባ ሊዘገይ ይችላል፡፡ የፖሊሲ አቅጣጫዎች ደግሞ እንደአስፈላጊነቱ የሚከናወኑ እንጂ በመደበኛነት የሚደረጉ አይደሉም በማለት ገልጸዋል፡፡

82.ስለጉዳዩ የባለስልጣን መ/ቤቱ እና የፕሮጀክት ጽ/ቤት ስራ ሀላፊዎች ይህን መልስ ቢሰጡም የፕሮጀክቱ ስትሪንግ ኮሚቴ ስራዎች በዋናነት በወቅቱ መደበኛ ሰበሰባ በማድረግ ስራዎችን በበላይ ሆኖ መገምገም ፣ቁጥጥር እና ክትትል ማድረግ እንዲሁም የዓመታዊ የሥራ ዕቅዶችን እና በጀትን ማፅደቅ በተጨማሪም የፖሊሲ አቅጣጫዎችን ማስቀመጠ በመሆናቸው እና እነዚህ ስራዎች ስለመሰራታቸው የሚያሳይ በቂ የተሟላ መረጃ ባለመቅረቡ የሰጡት መልስ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

83.የፕሮጀክት ስትሪንግ ኮሚቴው በተፈለገው ልክ የፕሮጀክት ጽ/ቤቱን ስራዎች በበላይነት ለመምራት በአንድ ላይ በመገኘት ባጋጠሙ ችግሮች ዙርያ ባለመወያየታቸው እንዲሁም የተለያዩ ወሳኝ ውሳኔዎችን በመወሰን የግንባታ ፕሮጅክት ስራዎች በወቅቱ እንዳይገመገሙ፣ ክፍተቶቹ ተለይቶ መስተካከል እንዳይችሉ እና ፕሮጀክቱ በተባለለት ጊዜ እንዳይጠናቀቅ ያደርጋል፡፡

**የዳኝነት ቦርድ ማቋቋሙን በተመለከተ**

84.በባለስልጣን መ/ቤቱ እና ኮንትራክተሩ የጋራ የሆነ ያለመግባባትን የሚፈታ/ የዳኝነት ቦርድ (Dispute Avoidance/Adjudication Board) ሊያቋቁሙ ይገባል፡፡

85.በዚሁ መሰረት የፈፀመ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ፡-

- በባለስልጣን መ/ቤቱ እና ኮንትራክተሩ የጋራ የሆነ ያለመግባባትን የሚፈታ /የዳኝነት ቦርድ ውሉ በተፈረመ በ42 ቀን ውስጥ መቋቋም ቢኖርበትም (Dispute Avoidance/Adjudication Board) ያልተቋቋመ መሆኑ፣
- በአሰሪው ተቋም እና በስራ ተቋራጩ የውል የሂሳብ ዝርዝር (Bill of Quantity) ላይ በአሰሪው ተቋም በኩል ለዳኝነት ቦርድ አባላት ተብሎ 3 ሚሊዮን ብር በጀት የተያዘ ቢሆንም ለታለመለት አላማ እየዋለ አለመሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ የሰነድ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

86.ስለጉዳዩ ለቻይና ሲቭል ኢንጂነሪንግ ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን (CCECC) የስራ ኃላፊዎች ከኦዲት ቡድኑ በቀረበው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ በኛ በኩል እንዲቋቋም ከአንዴም ሁለት ሦስት ጊዜ ጠይቀናል ነገር ግን በአሰሪው መ/ቤት በኩል እስከ አሁን መልስ አላገኘም በማለት ገልጸዋል፡፡

87.ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የባለስልጣን መ/ቤቱ እና የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች

በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (fact sheet) እና በኦዲት ቡድኑ በቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ በውሉ መሠረት ለማቋቋም እስከ መረጣ ድረስ መሄድ የተቻለ ቢሆንም፤ ፕሮጀክቱ በፍጥነት ስላልተጀመረና በወቅቱ አለመግባባት ስላልተከሰተ በየወሩ በቋሚነት ሳይቱ ሲገበኝ ከፍ ያለ ክፍያ በውጭ ምንዛሬ የሚጠይቁ በመሆናቸው እና ሥራ ተቋራጩ በውጭ ምንዛሬ ለመክፈል እንደሚቸገር በመግለጹ የማሪታይም እና የሥራ ተቋራጩ ሃላፊዎች በተገኙበት አስፈላጊ በሆነ ጊዜ መሰየም እንደሚቻል መግባባት ላይ በመደረሱ እንዲዘገይ ተደረገ እንጂ የተተወ ተግባር አይደለም ሲሉ ገልጸዋል።

88.የባለስልጣን መ/ቤቱ የሰራ ኃላፊዎቹ ይህንን መልስ ቢሰጡም እንዲሰየም የተፈለገው በመጀመሪያው የፕሮጀክቱ ምዕራፍ እንጂ ፕሮጀክቱ ከተጠናቀቀ በኂላ ባለመሆኑ፣ ለሥራ ተቋራጩ 33.4% በውጭ ምንዛሬ እንዲከፈለው በውል ውስጥ የተካተተና የተፈቀደ በመሆኑ፣ ለዚው ሥራ ተብሎ የተያዘ በጀት በመኖሩ እንዲሁም አስፈላጊ በሆነ ጊዜ መሰየም እንደሚቻል እና በውሉ መሰረት ተግባራዊ መደረግ ያለበት በመሆኑ የተሰጠው መልስ በኦዲቱ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም።

89.በባለስልጣን መ/ቤቱ እና ኮንትራክተሩ የጋራ የሆነ ያለመግባባትን የሚፈታ / የግልግል ዳኝነት ቦርድ አባላት (Dispute Avoidance/Adjudication Board) አለመቋቋሙ ግጭት እንዳይፈጠር አስቀድሞ ከመከላከል አንፃር መሰራት ያለባቸው ስራዎች በእቅድ ተካትተው እንዳይሰሩ በማድረግ አለም ባንክ ያስቀመጣቸው የውል ግዴታዎች እንዳይፈጸሙ አድርጓል።

**ባለስልጣን መ/ቤቱ የፕሮጀክት አስተዳደር አቅምን ማሳደጉን በተመለከተ**

90.ባለስልጣን መ/ቤቱ የፕሮጀክት አስተዳደር አቅምን ለማሳደግ የክትትል፣ ቁጥጥርና የማብቃት ስራዎችን ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል።

91.ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ባለስልጣን መ/ቤቱ በዚሁ መሰረት የፈፀመ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ፡-

- የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሰው ሃይል ያልተሟላ መሆኑ፤ ለማሳያ ያህል ከተፈቀደው 26 የሰው ሃይል እስከ ሕዳር 15/2016ዓ.ም መጨረሻ ድረስ 13 የሰው ሃይል በስራ ላይ የሌለ ሲሆን ለፕሮጀክት ጽ/ቤቱ አስፈላጊ የሆኑ የሰው ሃይሎች ማለትም የአካባቢያዊ ባለሙያ፤የስርአተ-ጾታ ባለሙያ፤የአይቲ ድጋፍ ቴክኒሻን፤ የውስጥ ኦዲተር፤ የሎጂስቲክስ ባለሙያ፤የኤሌክትሮ ሜካኒካል ኢንጂነር ሰራተኞችን ለመቅጠር በየአመቱ እቅድ የሚታቀድ ቢሆንም ኦዲቱ እስከተከናወነበት ጊዜ ድረስ ተፈጻሚ አለመሆኑ፣
- ለፕሮጀክቱ አስፈላጊ የሆኑ ባለሙያዎች የሚቀጠሩበት መንገድ ሁሉንም ብቁ ተወዳዳሪዎችን አካታች በሆነ መልኩ እና በውድድር አለመሆኑ፣ ለማሳያ የፕሮጀክት

ኢንጂነር ቅጥር የገበያ አማራጩን (Market Approach Limited) ውስን በማድረግ ቅጥር መፈፀሙ ትክክል አለመሆኑ፣

- እንዲሁም በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በየአመቱ የሚታቀድ ያልተሟላ ብዙ የሰው ሀይል ክፍተት እያለበት በፕሮጀክቱ በጀት ለባለስልጣን መ/ቤቱ የህግ ባለሙያ (Lawyer) መቀጠሩ በጀቱ ለታለመለት አላማ እየዋለ እንዳልሆነ የሚያሳይ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ የሰነድ ማስረጃዎች እና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች ለማወቅ ተችሏል፡፡

92.ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የባለስልጣን መ/ቤቱ እና የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (fact sheet) እና በኦዲት ቡድኑ በቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ፡-

- በፕሮጀክት የሚሟሉ የስራ መድቦች ቅጥር የሚከናወነው በግልጽ በተዘጋጀ መስፈርት እና በአለም ባንክ የግዥ መመሪያ መሰረት ሲሆን ውስን የጨረታ ሂደት ከጨረታ አማራጮች አንዱ ነው አተገባበሩም መደቡን ባጭር ጊዜና በአስቸኳይ ማሟላት ሲያስፈልግ የሚተገበር የግዥ አማራጭ ሲሆን ከ3 ያላነሱ ተወዳዳሪዎችን በመጋበዝ በውድድር የሚከናዎን ነው፡፡ በግዥ ኮሚቴ የውሳኔ ኃሳብ መሰረት ዋና ዳይሬክተሩ ሲያጸድቅ ተግባራዊ ይሆናል፡፡ የፕሮጅክት ኢንጅነር ቅጥር በዚህ አይነት የግዥ አማራጭ የተከናወነ ነው፡፡
- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ አስፈላጊ በሆኑ የስራ መደቦች ላይ ቀጥሮ እያሰራ ነው፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰው አንዳንድ የስራ መደቦች በተለያየ አማራጭ የተሸፈኑ ስለሆነ መቅጠር ባለማስፈለጉ ለጊዜው በእቅድ ብቻ እየተያዘ እንዲቆይ ሆኗል፡፡ የህግ አማካሪ የተቀጠረው ለንግድ ሎጅስቲክስ ፕሮጀክት ትራንስፎርሜሽን ጽ/ቤት ሲሆን በእቅድ የተያዘ ነው በማለት ገልጸዋል፡፡

93.የባለስልጣን መ/ቤቱ የሰራ ኃላፊዎቹ ይህንን መልስ ቢሰጡም የቅጥር ሂደቱ ውስን ጨረታ በማድረግ የተኬደበት አሰራር ፕሮጀክት አስተባባሪ (Project Coordinator) የፕሮጅክት ኢንጅነሩን ቦታ ከአመት በላይ ደርቦ ሲሰራ የነበረ በመሆኑ መደቡን ባጭር ጊዜና በአስቸኳይ ማሟላት ማስፈለጉ የሚለው ሀሳብ ከላይ በተቀመጠው ምክንያት ትክክል አለመሆኑ፣ የህግ ባለሙያ በሎጅስቲክስ ፕሮጀክት ትራንስፎርሜሽን ጽ/ቤት እቅድ ያልተካተተ በመሆኑ የተሰጠው መልስ በኦዲቱ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

**የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ እና የሎጅስቲክስ ፕሮጀክት ትራንስፎርሜሽን ጽ/ቤት የሰው ሀይል ዕቅድ በአባሪ 6 ተያይዟል፡፡**

94. ባለስልጣን መ/ቤቱ የፕሮጀክቱ አፈፃፀም ክትትልና ድጋፍ ለማሳደግ በተለያዩ የፕሮጀክት ክፍሎች ብቁ የሆነ የሰው ሃይል ሟሟላት የሚያስፈልግ በመሆኑ እና ቅጥር ሲፈፀም ግልፅና ተጠያቂነት በሰፈነበትና እኩል እድልን ለተሳታፊዎች በመስጠት የመንግስት የቅጥር ህግን እንዳያከብር እና የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሰው ሃይል ተሟልቶ በሙሉ ኃይል እንዳይሰራ አስተዋፆ አድርገዋል፡፡

**የሞጆ አረንጓዴ ሎጂስቲክስ ማዕከል ግንባታ ፕሮጀክት መረጃ አያያዝን በተመለከተ**

95. ባለስልጠን መ/ቤቱ የሞጆ አረንጓዴ ሎጂስቲክስ ማዕከል ግንባታ ፕሮጀክት ዝግጅት እና አተገባበርን በተመለከተ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ ማጠናቀር፣ መተንተን እና ማሰራጨት ይኖርበታል፡፡

- ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ባለስልጣን መ/ቤቱ በዚሁ መሰረት የፈፀመ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ፡- የግንባታ ፕሮጀክቱን ዝግጅት እና አተገባበርን በተመለከተ በብሮሸር፣ በበራሪ-ወረቀት(ፍላየር) ወ.ዘ.ተ በመሳሰሉ የማስተዋወቅያ ዘዴዎችን በመጠቀም በስፋት ፕሮጀክቱን የማስተዋወቅ ስራ አለመስራቱ እንዲሁም ዘመናዊ የመረጃ ቴክኖሎጂ በመጠቀም መረጃን በሚገባው መጠን ተደራሽ አለመደረጉን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ የሰነድ ማስረጃዎች እና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች ለማወቅ ተችሏል፡፡

96. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የባለስልጣን መ/ቤቱ እና የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (fact sheet) እና በኦዲት ቡድኑ በቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ስለፕሮጀክቱ በታወቁ ሚዲያዎች ለምሳሌ ዋልታ እና ኢቲቪ ማብራሪዎች ተሰጥተዋል፡፡ የሚመለከታቸው መንግሥታዊ አካላትም እየጎበኙት ይገኛሉ፡፡ በጉብኝት ወቅትም በሚዲዎች እና በማህበራዊ ድረ-ገጾቸ በመለጠፍ የማዳረስ እና የማስተዋወቅ ስራ ተሰርቷል፡፡ ነገር ግን ፍላየር ማዘጋጀት አንድ ጊዜ የተሰራ ቢሆንም ወቅቱን ጠብቆ እየተከለሰ አይደለም፡፡ በቅርብ በራሪ ወረቀት/ፍላየር እና ዶክመንታሪ ለመሥራት ዝግጅት እያደረግን ነው በማለት ገልጸዋል፡፡

97. የባለስልጣን መ/ቤቱ እና የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ድረስ ተሰርተዋል የተባሉ ሥራዎች ማስረጃዎቻቸውና ባለመቅረባቸው የቀረበውን መልስ በኦዲቱ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

98. በፕሮጀክት ጽ/ቤት ውስጥ የፕሮጀክት ሀሳቦችን፣ ሪፖርቶችን፣ ግምገማዎችን እና ህትመቶችን በተመለከተ የተደረጃ ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ስርዓት በሚፈለገው ደረጃ ባለመደራጀቱ፣ በብድር የተሰሩ ፕሮጀክቶች ዝርዝር ሁኔታ እና ፋይዳቸው ምን ደረጃ ላይ እንዳለ በቀላሉ ለመረዳት ካለማስቻሉም በላይ የሚፈለገውን መረጃ አቀናጅቶ

በሚፈገው ልክ ለሚፈልገው አካል ለመስጠት እንዳይቻል ያደርጋል፡፡


## IV. የኢትዮጵያ ማሪታይም ባለሥልጣን በሞጆ አረንጓዴ ሎጂስቲክስ ማዕከል ግንባታ ፕሮጀክት ለልማት ተነሽዎች በወቅቱ የካሳ ክፍያ መከፈሉን ማረጋገጥ፡፡

**ካሳ ክፍያ እና በመልሶ ማቋቋምን በተመለከተ::**

99.ባለስልጣን መ/ቤቱ ለልማት ተነሽዎች በወቅቱ የካሳ ክፍያ በመክፈል የግንባታ ቦታውን ለስራ ዝግጁ ሊያደርግ ይገባል፡፡

100. ይሁን እንጅ በኦዲቱ ወቅት ጉዳዩን አስመልክቶ በተካሄደ የማስረጃ ክለሳ የሚከተሉት ክፍተቶች ተለይተዋል፡፡

- ❖ ከሞጆ ወደብና ተርሚናል ፕሮጀክት ጋር በተያያዘ ለልማት ተነሺዎች በአካባቢው ማህበረሰብ እና በአርሶ አደሮች ዘንድ መልካም ስም እንዲኖረው እና የህብረተሰቡ አጋር እንደሆነ እንዲገነዘቡ በማለት በሞጆ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ እና ኢኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤት በኩል ተጨማሪ 9,632,750.00 (ዘጠኝ ሚሊዮን ስድስት መቶ ሰላሳ ሁለት ሺ ሰባት መቶ ሀምሳ ብር) ከመደበኛው ክፍያ በተጨማሪ እንዲከፈል የተደረገ መሆኑ፣
- ❖ ለልማት ተነሽዎች ምትክ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ የመስጠቱ እና የካሳ ክፍያ ስራዎች መዘግየታቸው እንዲሁም የመኪና ማቆሚያ ቦታ የባለቤትነት ይዞታ አለመጠናቀቁ በማሪታይም ባለስልጣን የንግድ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክት ጽ/ቤት በ2013 እና በ2014 በጀት ዓመት ዓመታዊ ሪፖርት የተመላከተ መሆኑ፣
- ❖ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ከህግ ውጭ ክፍያ (ጥቅም) የሚፈልጉ የተለያዩ ግለሰቦች በተመረጡ አፈር ማምረቻ(Borrow Site)፣ በማይጠቅም አፈር መድፍያ(Waste Disposal area) ቦታዎች ላይ በተደጋጋሚ የሚፈጠረውን የስራ ማወክ ድርጊት በጋራ ለማስቆም በቂ ክትትል ያላደረገ መሆኑ፣
- ❖ በሞጆ ወደብ ማስፋፍያ ፕሮጀክት የመልሶ ማቋቋምና ኑሮ ማሻሻያ ፕሮጀክት ለልማት ተነሺ አርሶ አደሮች የእንስሳት መጠለያ በራሳቸው የሰሩ በቁጥር 61 ለሚሆኑ ሰዎች የተከፈለ ጠቅላላ ብር ድምር 2,296,173.30 (ሁለት ሚሊዮን ሁለት መቶ ዘጠና ስድስት ሺ አንድ መቶ ሰላሳ ከ30/100 ብር) ሲሆን የተሰራው መጠለያ በዲዛይኑ መሰረት እና ደረጃውን በጠበቀ መልኩ አለመሰራቱ የኦዲት ቡድኑ በመስክ ምልከታ ያረጋገጠ መሆኑ፣







ዲዛይኑ እና በአርሶ አደሮች የተሰራ የእንስሳት መጠለያ ስዕላዊ መገለጫ ።

- ❖ በመልሶ ማቋቋም ጥናት መሰረት በኮልባ-ጎዴ ቀበሌ የኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ የልማት ድጋፍ ስራ የተሰራ ቢሆንም ነገር ግን ለ129 ነዋሪ ግለሰቦች ብር 439,293.86 (አራት መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ሺ ሁለት መቶ ዘጠና ሶስት ከ86/100 ብር) የመብራት ቆጣሪ ክፍያ ከመመሪያ ውጭ የተከፈለ መሆኑ፣

በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ የሰነድ ማስረጃዎች እና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፍዎች ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች ለማወቅ ተችሏል።

101. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የኢትዮጵያ የባሕር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት የሥራ ኃላፊዎች እና የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ባለሙያ በኦዲት ቡድኑ በቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ፡-

☞ ድርጅታችን የተገመተውን የካሳ ክፍያ ከላከ በኃላ አርሶ አደሮች በጎረቤት ቀበሌ

የአንድ ካሬ መሬት ካሳ 33ብር ሂሳብ የተከፈለ መሆኑን በመግለጽ ክርክር አነሱ። ወረዳው ከጥር ወር በፊት ካሣ የገመተላቸው በካሬ 269 ብር ሂሳብ ነበር። አርሶ አደሮች የተላከላቸውን ካሣ ቀርበው ለመውሰድ ፍቃደኛ ስላልነበሩ በተደጋጋሚ በኛ እና በወረዳ አመራሮች ውይይት ተደረገ። አርሶ አደሮች በዝምታ በመጽናታቸው በመጨረሻ በከፍተኛ አመራር ደረጀ በተደጋጋሚ ተሞከረ። መሬቱ በቶሎ መለቀቅ ስለነበረበት የድርጅቱ ከፍተኛ አመራር ለመጨረሻ ጊዜ ከአርሶ አደሩ ጋር ውይይት አድርጎ በካሬ 50 ብር ተጨምሮላቸዋል። የተጠቀሰው የተጨማሪ ካሣ ክፍያ ይህ ነው።

☞ በ1ኛ ዙር የመልሶ መቋቋም ሥራ በእንስሳት እርባታ ለተሰማሩ አርሶ አደሮች የአማካሪ የጥናት ሠነድ በሚያዘው መሰረት የእንስሳት መጠለያ ተሰርቶላቸዋል የመጠለያው ዲዛይን ከሎሜ ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት የተወሰደና ሥራውም በስኬት የተጠናቀቀ ነበር። ነገር ግን በ2ኛ ዙር የመልሶ ማቋቋም በተመሳሳይ መልኩ የእንስሳት መጠለያ እንዲሰራላቸው ኮንትራክተር ተቀጥሮ ሥራ ተጀምሮ ነበር። ነገር ግን ሥራው በተቋራጩና የእንስሳት መጠለያ በሚሰራላቸው አርሶ አደሮች መካከል በተፈጠረ አለመግባባት ምክንያት ሥራ ተቋራጩ ሥራውን አቋርጦ በመውጣቱ አርሶ አደሮች እንስሳት እንዳይጎዱ በሚል በራሳቸው መጠለያ በመስራት ያወጡት ወጭ እንዲመለስላቸው በጠየቁት ጥያቄ መሰረት የግብርና እና የመሃንዲስ ባለሙያዎችን ያካተተ ኮሚቴ ተቋቋሞ መጠለያ በራሳቸው ስለመስራታቸው አረጋግጠው እንዲያቀርቡ በማድረግ በቀረበው መረጃ መሰረት በወሰዱት እንስሳት መጠን፣ በሠሩት መጠለያ መሠረት ያወጡት ወጪ እንዲተካላቸው ተደርጓል።

☞ የኤሌክትሪክ ቆጣሪ ክፍያን በተመለከተ ድርጅታችን ለቀበሌ ከሰራው የልማት ድጋፍ ውስጥ አንዱ የኤሌክትሪክ መስመር መዘርጋታ ነው። መስመሩ ከተዘረጋ በኃላ 129 ነዋሪዎች የተጠየቁትን ብር 439,293.86 የመብራት ቆጣሪ መክፈል የማይችሉ መሆናቸውን በተደጋጋሚ በመግለጻቸው፣ ድርጅቱ በተጠቃሚዎቹ ስም ለመብራት ኃይል ክፍያውን ፈጽሟል በማለት በሰጡት ምላሽ ላይ ገልጸዋል።

102. የባለስልጣኑ የሥራ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ በኮልባ ጎዴ ቀበሌ ካሰራው የልማት ስራዎች ውስጥ ለተገነባው የአስተዳደር ቢሮ የኤሌክትሪክ መስመር መዘርጋት አንዱ ሆኖ ሳለ ለያንዳንዱ የቀበሌ ነዋሪዎች የቆጣሪ ክፍያ ክፈሉ የሚል የህግ አግባብም ሆነ መመሪያ ለኦዲቱ ያልቀረበ በመሆኑ መልሱ በኦዲቱ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም።

103. የግንባታ ፕሮጀክቱ ስራ ከመጀመሩ በፊት በአዋጁ እና በደንቡ መሰረት በወቅቱ ክፍያ

አለመፈጸሙ የተለያዩ ቅሬታዎችን በማስነሳት የሎጀስቲክ ግንባታ ሥራውን ከማጓተቱ በተጨማሪ በየጊዜው ተጨማሪ ወጪ ከመመሪያ ውጭ እንዲከፈል አድርጓል፡፡

## ክፍል ሶስት

## የኦዲቱ መደምደሚያ ሃሳቦች (audit conclusion)

104. ከላይ በኦዲት ግኝቶቹ ላይ እንደተመለከተው በማሪታይም ባለስልጣን የንግድ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክት ጽ/ቤት የሞጆ አረንጓዴ ሎጂስቲክስ ማዕከል ፕሮጀክት ግንባታ አፈፃፀም ውጤታማነትን በተመለከተ የሎጅስቲክስ ማዕከል ፕሮጀክት ውጤታማ መሆኑ ሲገመገም የሚከተሉት ዋና ዋና መደምደሚያ ሃሳቦች ላይ ተደርሷል፡፡

- (በሴሌሆርን-ኤችፒሲ ጄ.ቪ) Sellehorn-HPC JV የተሰራ የሎጂስቲክስ መሰረተ ልማት የምህንድስና ዝርዝር ዲዛይን፣ የግንባታ ቁጥጥር እና የውል አስተዳደር አገልግሎቶችን ያሟላ አለመሆኑ እንዲሁም በፕሮጀክቱ ውሉ መሠረት የተሟላ ዲዛይን ሰርቶ ማስረከብ አለመቻሉ፣የተፈጥሮ እና የሰው ሰራሽ ገፅታዎች የወንዝ ጅረት እና ጉድጓዶች የመሳሰሉትን በማስተር ፕላኑ ላይ ያላካተተ መሆኑ፤ ይህንኑ ተከትሎ ዲዛይኑን እንዲሰሩ በመ/ቤቱ በኩል የተወከሉ ባለሙያዎች የሰሩት ዲዛይን ኮንትራክተሩ ሥራውን ለመስራት ወደ ሳይት በገባበት ወቅት ሊያሰራው ያልቻለ መሆኑ ታውቋል፡፡
- ስራ ተቋራጩ የተወሰኑ ለመሬት ጥናት የሚያገለግሉ መሳሪያዎችን ያቀረበ ቢሆንም በስምምነቱ እንደሚያስፈልገው መጠን ሙሉ አለማቅረቡ እንዲሁም ስራ ተቋራጩ ለግንባታ የሚያስፈልግ ሲሚንቶ በማቅረብ ሥራውን በዕቅዱ መስራት አልቻለም፡፡
- በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ቀድም ሲል ተግባራዊ የሆነው የፕሮጀክት አስተዳደር ማኑዋል/Project Administrative Manual/ ያለው ቢሆንም ከ6 አመት በላይ የቆየ እና በእ.ኤ.አ መጋቢት 2021 ተሻሽሎ የቀረበውም ቢሆን ለሚመለከተው አካል ቀርቦ አልጸደቀም፡፡
- ስራ ተቋራጩ ሊያቀርብ የሚገው ማንዋል American Society for Testing Materials (ASTM) Standards, Deutsches Institut for Normung e.V. (DIN) Standards, British Standard (BS), American Concrete Institute(ACI) Standards, ባለመቅረቡ ቴክኒካል ስራዎችን አዛምዶ ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- ፕሮጀክቱ ከተጀመረበት ጀምሮ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ የፕሮጀክቱ የፋይናንስ አፈፃፀሙ ዝቅተኛ መሆኑ ታውቋል፡፡
- የሞጆ አረንጓዴ ሎጂስቲክስ ማዕከል ግንባታ ማስፋፍያ ለሲቪል ሥራ በተቀመጠው ውል Bill of Quantity በ Item 01500.5 a,b ላይ እንደተቀመጠው 4ታይፕ A እና 7 ታይፕ B መኪናዎች በድምሩ 11 መኪናዎች መገዛት እንዳለበት እና ከተገዙት 4ታይፕ A ሁለት ለአሰሪው ተቋም ሁለት ለአማካሪው መሆን እንዳለበት በውሉ

የተመላከተ ቢሆንም ነገር ግን 4ታይፕ A መኪናዎችን ሁሉንም አሰሪው መ/ቤት የወሰደ መሆኑ፣ በተጨማሪ ታይፕ B 2 አዲስ ፒክአፕ መኪናዎችን አሰሪው ተቋም በመውሰድ አማካሪው ሁለቱን መኪናዎችን በኪራይ መልክ እንዲጠቀም ተደርጓል፡፡

- ፕሮጀክቱ እ.ኤ.አ ሐምሌ 2017 ተጀምሮ ሐምሌ 2023 ይጠናቀቃል ተብሎ የታቀደ ቢሆንም በይፋ ስራ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ እስከ 2016 ዓ.ም. ሩብ በጀት ዓመት ድረስ ወይም እ.ኤ.አ (2024) ጠቅላላ የፕሮጀክቱ አፈጻጸም 61.51% ብቻ በመሆኑ ከዕቅድ አንፃር ሲታይ ፕሮጀክቱ የዘገየ መሆኑ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡
- የTOS-GOS ስራው እንዲሰጠው ከተደረገው JV CCECC, with Huadong Electron and CSI እ. አ .አ ጁላይ(ሐምሌ) 5 2023 የውል ስምምነት የተደረገ ቢሆንም ውሉ ተፈርሞ አምስት ወር ያለፈው ሲሆን ስራው ግን በአግባቡና በውሉ መሰረት እየተከናወነ አለመሆኑ እና ችግሩን ለመፍታት ጊዜ የወሰደ በመሆኑ አፈፃፀሙ ዝቅተኛ እንዲሆን አድርጓል፡፡
- የፕሮጀክቱን ግዥዎች ለማከናወን የተቀመጡ የግዥ ሂደቶች የሚወስዱት ጊዜ ከታሰበው በላይ የፕሮጀክቱን የትግበራ ጊዜ ማራዘሙ እና የግዥ ሂደቱ ሊወስድ የሚችለው ጊዜ ግንዛቤ ውስጥ አለመግባቱ በፕሮጀክቱ አፈፃፀም ላይ ተፅዕኖ የፈጠረ መሆኑ እንዲሁም የሎጂስቲክስ መሰረተ ልማት ግንባታ ፕሮጀክቶችን በውላቸው መሰረት ማጠናቀቅ አለመቻሉ በአስር አመቱ መሪ እቅድ እንደ ድክመት የተቀመጠ መሆኑ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡
- ፕሮጀክቱ ሲቀረፅ በፕሮጀክት ጥናት ጀምሮ በፕሮጀክት ትግበራና አፈፃፀም ወቅት በእያንዳንዱ የሥራ ሂደት ሴቶች እና ድጋፍ የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎችን አካትቶ ተግባራዊ ለማድረግ በዕቅድ ያላከተተ መሆኑ እና በአፈፃፀሙ ወቅትም ከዚህ አንፃር የማይገመግሙ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡
- ፕሮጀክቱ በሚተገበርበት ቦታ በህዳር 16/2016 በስራ ተቋራጩ ያሉ አጠቃላይ የሰው ሀይል ሰራተኞች ቁጥር 764 ሲሆን አንድ ኪ-እስታፍ የአካል ጉዳተኛ እንዲሁም በቁጥር 33 የሴት ሰራተኞች ያሉ ቢሆንም በተፈለገዉ መጠን የሴቶችን እና የአካል ጉዳተኞች ተሳትፎ ከወንዶች ጋር ሲነፃፀር 4.3% እና 0.1% ሲሆን ቁጥራቸዉ ዝቅተኛ ነው፡፡
- የፕሮጀክት ስትሪንግ ኮሚቴ የፕሮጀክቱን እንቅስቃሴ በእቅድ መሰረት በመስክ ላይ በመገኘት የፕሮጀክቱ ተግባራት ያሉበትን ደረጃ ገምግሞ አቅጣጫዎችን የማስቀመጠና የውሳኔ ሃሳብ መስጠት ላይ ክፍተት መኖሩን ተገንዝበናል፡፡
- ስትሪንግ ኮሚቴው ለፕሮጀክቱ ጠቀሜታ ሲባል በቋሚነት ከተለያዩ አካላት ጋር

የትብብር ግንኙነቶች እንዲኖር ያላደረገ መሆኑ እና የፕሮጀክቱ ስራዎች በጊዜው እንዲከናወኑ የፖሊሲ አቅጣጫዎችን ያላስቀመጠ እንዲሁም የፕሮጀክቱን ባለድረሻ አካላት/stakeholders/ በተፈለገው ጊዜ በአንድ ላይ መገኘት አለመቻልና ፕሮጀክቱ ላይ ባጋጠሙ ችግሮችና መፍትዎቻቸው ዙሪያ በጋራ መወያየት ላይ ክፍተቶች አሉበት፡፡

- የፕሮጀክት አስተባባሪ ኮሚቴው (PSC) የፕሮጀክቱን ስራዎች በበላይ ሆኖ ለመገምገም፣ ቁጥጥር እና ክትትል ለማድረግ እንዲሁም የዓመታዊ የሥራ ዕቅዶችን እና በጀትን ለማፅደቅ በመደበኛነት መሰብሰብ ላይ ክፍተት መኖሩን ታይቷል፡፡
- በባለስልጣን መ/ቤቱ እና ኮንትራክተሩ የጋራ የሆነ ያለመግባባትን የሚፈታ /የዳኝነት ቦርድ ውሉ በተፈረመ በ42 ቀን ውስጥ መቋቋም ቢኖርበትም (Dispute Avoidance/Adjudication Board) አልተቋቋመም፡፡
- የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሰው ሃይል ያልተሟላ መሆኑ፤ ለማሳያ ከተፈቀደው 26 የሰው ሃይል እስከ ሕዳር 15/2016ዓ.ም መጨረሻ ድረስ 13 የሰው ሃይል በስራ ላይ የሌለ ሲሆን ለፕሮጀክት ጽ/ቤቱ አስፈላጊ የሆኑ የሰው ሃይሎች ማለትም የአካባቢያዊ ባለሙያ፤የስርአተ-ጾታ ባለሙያ፤የአይቲ ድጋፍ ቴክኒሻን፤ የውስጥ ኦዲተር፤ የሎጂስቲክስ ባለሙያ፤የኤሌክትሮ ሜካኒካል ኢንጂነር ሰራተኞችን ለመቅጠር በየአመቱ እቅድ የሚታቀድ ቢሆንም ኦዲቱ እስከተከናወነበት ጊዜ ድረስ ተፈጻሚ አልሆነም፡፡
- ለፕሮጀክቱ አስፈላጊ የሆኑ ባለሙያዎች የሚቀጠሩበት መንገድ ሁሉንም ብቁ ተወዳዳሪዎችን አካታች ባደረገ መልኩ እና በውድድር አለመሆኑ፣ ለማሳያ የፕሮጀክት ኢንጂነር ቅጥር የገበያ አማራጩን (Market Approach Limited) ውስን በማድረግ ቅጥር መፈፀሙ አሰራሩ ትክክል አለመሆኑ እንዲሁም በበፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በየአመቱ የሚታቀድ ያልተሟላ ብዙ ክፍተት ያለበት የሰው ሀይል እያለ በፕሮጀክቱ በጀት ለባለስልጣን መ/ቤቱ የህግ ባለሙያ (Lawyer) መቀጠሩ በጀቱ ለታለመለት አላማ እየዋለ እንዳልሆነ የሚያሳይ መሆኑን ለመገንዘብ ችለናል፡፡
- የግንባታ ፕሮጀክቱን ዝግጅት እና አተገባበርን በተመለከተ በብሮሸር፣ፍላየር(በበራሪ-ወረቀት)ወ.ዘ.ተ በመሳሰሉ የማስተዋወቅያ ዘዴዎችን በመጠቀም በስፋት ፕሮጀክቱን የማስተዋወቅ ስራ አለመስራቱ እንዲሁም ዘመናዊ የመረጃ ቴክኖሎጂ በመጠቀም መረጃን በሚገባው መጠን ተደራሽ አልተደረገም፡፡
- ከሞጆ ወደብና ተርሚናል ፕሮጀክት ጋር በተያያዘ ለልማት ተነሺዎች ወደቡ በአካባቢው ማህበረሰብ እና በአርሶ አደሮች ዘንድ መልካም ስም እንዲኖረው እና የህብረተሰቡ አጋር እንደሆነ እንዲገነዘቡ በማለት በሞጆ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ እና ኢኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤት በኩል ተጨማሪ 9,632,750.00 (ዘጠኝ ሚሊዮን ስድስት

መቶ ሰላሳ ሁለት ሺ ሰባት መቶ ሀምሳ ብር) ክፍያ ተፈፅሟል፡፡

- ለልማት ተነሽዎች ምትክ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ የመስጠቱ እና የካሳ ክፍያ ስራዎች መዘግየታቸው እንዲሁም የመኪና ማቆሚያ ቦታ የባለቤትነት ይዞታ አለመጠናቀቁ በማሪታይም ባለስልጣን የንግድ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክት ጽ/ቤት በ2013 እና በ2014 በጀት ዓመት ዓመታዊ ሪፖርት የተመላከተ መሆኑ ተመልክተናል፡፡
- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ከህግ ውጭ ክፍያ (ጥቅም) የሚፈልጉ የተለያዩ ግለሰቦች በተመረጡ አፈር ማምረቻ(Borrow Site)፣ በማይጠቅም አፈር መድፍያ(Waste Disposal area) ቦታዎች ላይ በተደጋጋሚ የሚፈጠረውን የስራ ማወክ ድርጊት በጋራ ለማስቆም በቂ ክትትል ማድረግ ላይ ክፍተት መኖሩን ተመልክተናል፡፡
- በሞጆ ወደብ ማስፋፍያ ፕሮጀክት የመልሶ ማቋቋምና ኑሮ ማሻሻያ ፕሮጀክት ለልማት ተነሺ አርሶ አደሮች የእንሰሳት መጠለያ በራሳቸው የሰሩ በቁጥር 61 ለሚሆኑ ሰዎች የተከፈለ ጠቅላላ ብር ድምር 2,296,173.30 (ሁለት ሚሊዮን ሁለት መቶ ዘጠና ስድስት ሺ አንድ መቶ ሰላሳ ከ30/100 ብር) ሲሆን የተሰራው መጠለያ በዲዛይኑ መሰረት እና ደረጃውን በጠበቀ መልኩ አለመሰራቱ የኦዲት ቡድኑ በመስክ ምልከታ አረጋግጧል፡፡
- በመልሶ ማቋቋም ጥናት መሰረት በኮልባ-ጎዴ ቀበሌ የኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ የልማት ድጋፍ ስራ የተሰራ ቢሆንም ነገር ግን ለ129 ነዋሪ ግለሰቦች የመብራት ቆጣሪ ክፍያ ከመመርያ ውጭ የተከፈለ መሆኑ ታይታል፡፡

105. ስለሆነም ከላይ የተጠቀሱትን ድክመቶች እና ችግሮች በብቃት፣ ኢኮኖሚያዊና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማስተካከል ይረዳሉ ተብለው የታመነባቸው የማሻሻያ ሀሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል አቅርበናል፡፡

# ክፍል አራት
# የማሻሻያ ሃሳቦች

106. በማሪታይም ባለስልጣን የንግድ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክት ጽ/ቤት የሞጆ አረንጓዴ ሎጂስቲክስ ማዕከል ፕሮጀክት ግንባታ አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማከናወን ያስችላሉ ተብለው የታመነባቸው የማሻሻያ ሃሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- የኢትዮጵያ ማሪታይም ባለስልጣን የሞጆ ሎጂስቲክስ ማዕከል ፕሮጀክትን ሲተገብር የቅድመ አዋጭነት እና የአዋጭነት ጥናት በማስጠናት፣ የፕሮጀክት ግምገማ ሰነድ እና የፕሮጅክት ትግበራዎች በቅድም ተከተል በማከናወን በጥልቅ በተጠና ዲዛይን ሥራውን መስራት በሀገር ውስጥ ለሚተገበሩ ማናቸውም የግንባታ ፕሮጀክቶች ውጤታማ እንዲሆኑ ሲለሚያስችል፣ የሞጆ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክትም ሆነ ወደ ፊት በብድር እና በመንግስት ፋይናንስ የሚሰሩ ትላልቅ ሀገራዊ ፕሮጀክቶች በጥናት ላይ የተመሰረተ የዲዛይንና የግንባታ ኮንትራት አስተዳደር ስርዓት ሊኖራቸው ይገባል፡፡
- የግንባታ ፕሮጀክቶች ስራን ለመተግበር የተሟላ የዲዛይን ንድፍ መንደፍ ወጪን ለመቀነስ፣ በጊዜ ለመጨረስ፣ አጠቃላይ ጥራትን ለማሻሻል እና የግንባታው ሂደቱን የበለጠ ውጤታማ መሆኑን ለማረጋገጥ እንዲሁም ሥራ ተቋራጭ እና አማካሪ ተቋም ስራቸውን በብቃት እንዲሰሩና የግንባታ ፕሮጀክቱ እንዴት እንደሚሠራ በቀላሉ እንዲረዱ የሚያግዝ በመሆኑ የሞጆ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክትም ሆነ ወደ ፊት በብድር እና በመንግስት ፋይናንስ የሚሰሩ ትላልቅ ሀገራዊ ፕሮጀክቶች ሲቀርፅ የፕሮጀክቱን ገፅታ በተገቢው መንገድ የሚሳይ ግልጽ እና የተሟላ ዲዛይን መነደፍ ይኖርበታል፡፡
- የግንባታ ፕሮጀክት በተሳካ ሁኔታ እንዲጠናቀቅ ልምድ ያላው ሥራ ተቋራጭ እና አማካሪ ተቋም አስፈላጊ መሆኑ ይታመናል፡፡ ስለሆነም አሰሪው ተቋም የስራ ተቋራጭ እና የአማካሪ መረጣውን ሲያከናውን በቴክኒካል እና ፋይናንሻል ያላቸው ልምድ እና አፈፃፀም እንድሁም በአለም ባንኩ ተለይቶ የተቀመጡ እና የሀገር ውስጥ የግዥ መመርያን መሰረት በማድረግ መከናወን አለበት፡፡ በተጨማሪም ባለስልጣን መ/ቤቱ የሞጆ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክትም ሆነ ወደ ፊት በብድር እና በመንግስት ፋይናንስ የሚሰሩ ትላልቅ ሀገራዊ ፕሮጀክቶች ግዥ በሚፈፅምበት ወቅት ያነሰ ዋጋ ያቀረበ ብቻ ከመምረጡ በፊት ያለውን ቁልፍ የሰው ኃይል፣ የግንባታ ማቴሪያል የፋይናንስ አቅም እና በፊት በግንባታ ላይ ያላቸውን አፈፃፀም ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል፡፡
- ኘሮጀክቱን በተሳካ ሁኔታ ለማጠናቀቅ ቅድመ-ብቃት /Pre-qualification/ ምዘናን በእቅድ ውስጥ በማካተት እንደ አማራጭ በመጠቀም መስራት ከፍተኛ ጥራት ያለው

ሥራ ለማቅረብ፣ አስፈላጊ ክህሎት፣ ልምድ እና ግብዓት ያላቸውን ብቁ ተጫራቾች ለመለየት እንዲሁም ኮንትራቱ የፕሮጀክቱን መስፈርቶች ሟሟላት ለሚችል ተጫራች መሰጠቱን ለማረጋገጥ ይረዳል፡፡ በተጨማሪም ኮንትራክተሩ ወደ ሥራ ከመሰማራቱ በፊት ያለውን አደጋ ለመቀነስ እና ትላልቅ እና ውስብስብ ስራዎችን ለማከናወን የሚረዳ ሂደት በመሆኑ ባለስልጣን መ/ቤቱ የሞጆ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክትም ሆነ ወደ ፊት በብድር እና በመንግስት ፋይናንስ የሚሰሩ ትላልቅ ሀገራዊ ፕሮጀክቶችን ሲቀርፅ በጨረታ ተወዳዳሪዎች ላይ ቅድመ-ብቃት /Pre-qualification/ ምዘናን እንደ አንዱ የዕቅዱ አካል አድርጎ በማካተት መስራት ይኖርበታል፡፡

- ጨረታውን አሸንፎ የሚገቡ ስራ ተቋራጮች በገቡት ውል መሰረት ለግንባታ ፕሮጀክቱ የሚያስፈልገውን ግብአት ማቅረብ ሲችሉ ስራው በተገቢው መንገድ እንዲከናወን አስተዋጾ ያደርጋል፡፡ በተጨማሪ ስራ ተቋራጩ የራሱ አማራጭ የገበያ ሰንሰለቶችን በመጠቀም ሲሚንቶም ሆነ ሌሎች ለግንባታው የሚያስፈልጉ ግብአቶችን በማቅረብ ግዴታውን መወጣት ስላለበት ባለስልጠን መ/ቤቱ የሞጆ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክትም ሆነ ወደ ፊት በብድር እና በመንግስት ፋይናንስ የሚሰሩ ትላልቅ ሀገራዊ ፕሮጀክቶችን ሲቀርፅ በጨረታ ያሸነፉ ሥራ ተቋራጬች ለግንባታ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች ማቅረብ የሚችሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡
- የፕሮጀክት አስተዳደር መመሪያ /Project Administrative Manual/ የኘሮጀክቶችን ሥራ በየደረጃው ለማከናወን፣ ለመከታተል፣ ለመገምገምና ለመቆጣጠር እንዲሁም የፕሮጀክቶች ትግበራን ለማቀላጠፍ እና ለግንባታ ፕሮጀክቶች የአስተዳደር ሂደቶችን፣ አሰራሮችን እና ኃላፊነቶችን ለመለየት እንዲሁም የኘሮጀክት ሥራዎች በቅድሚያ በተነደፈላቸው ስልት ወይም ዘዴ መሰረት እንዲከናወኑ፣ በተያዘላቸው እቅድ መሠረት እንዲጠናቀቁ እና የተቀረፁበትን ዓላማ እንዲያሳኩ አመቺ ሁኔታን የሚፈጥር በመሆኑ ባለስልጣን መ/ቤቱ የሞጆ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክትም ሆነ ወደ ፊት በብድር እና በመንግስት ፋይናንስ የሚሰሩ ትላልቅ ሀገራዊ ፕሮጀክቶችን ሲቀርፅ የፕሮጀክት አስተዳደር ማኑዋሉን በየግዜው ወቅታዊ በማድረግ እና በሚመለከተው አካል በማፀደቅ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- አንድ የግንባታ ፕሮጀክት ውጤታማ ነው ለመባል በተያዘለት የጊዜ እቅድ እና በተመደበለት በጀት ማለቅ ሲችል በመሆኑ ይህ ትልቅ ሀገራዊ ፕሮጀክት ከአለም ባንክ በተገኘ ብድር የሚሰራ ፕሮጀክት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ፕሮጀክቱ በተያዘለት በጀት ስራዎችን በተገቢው መንገድ ሊከናወኑ ይገባል፡፡ እንዲሁም የፕሮጀክቱ ስራዎች ሲከናወኑ ውጤታማ፣ ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ ሲተገበሩ አመርቂ ውጤት

ስለሚያስገኝ ባለስልጠን መ/ቤቱ የሞጆ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክትም ሆነ ወደ ፊት በብድር እና በመንግስት ፋይናንስ የሚሰሩ ትላልቅ ሀገራዊ ፕሮጀክቶችን ሲቀርፅ ፕሮጀክቶች በተገባው የኮንትራት ውል መሰረት በታቀደው የጊዜ ሰሌዳ እና ዋጋ (በጀት) እንዲጠናቀቁ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- የግንባታ ፕሮጀክቶች ሲከናወኑ የሴቶችን፣የአካል ጉዳተኞችን እና ድጋፍ የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎችን ባሳተፈ መልኩ መከናወኑ መንግስት በቀጣይ የልማት ዕቅድ (SDG) የያዘውን የሴቶች፣ አካል ጉዳተኞች እና ድጋፍ የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎችን ተሳትፎ ከማሳካት እና ተጠቃሚነታቸውን ከማረጋገጥ አንፃር የጎላ ሚና/አስተዋፆ/ ያለው በመሆኑ ባለስልጣን መ/ቤቱ የሞጆ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክትም ሆነ ወደ ፊት በብድር እና በመንግስት ፋይናንስ የሚሰሩ ትላልቅ ሀገራዊ ፕሮጀክቶችን ሲቀርፅ የሴቶች፣ የአካል ጉዳተኞችን እና ድጋፍ የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎችን ተሳትፎ የሚያሳድጉ ውሎችና አሰራሮችን ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡፡
- የፕሮጀክት ስትሪንግ ኮሚቴ የፕሮጀክት ጽ/ቤቱን ስራዎች በበላይነት ለመምራት በመደበኛነት በመሰብሰብ የፕሮጀክቱን ሥራዎች መከታተል፣ በመደገፍ፣ ምክር እና መመሪያ መስጠት፣ ጥራትን መቆጣጠር፣ አቅጣጫዎችን እና የውሳኔ ሃሳብ ማስተላለፍ ኃላፊነቱን መወጣት ይኖርበታል፡፡
- የሞጆ ሎጅስቲክስ ማዕከል ግንባታ ፕሮጀክትን ለመገንባት ሲታቀድ በሎጅስቲክስ ግንባታው ሂደት በባለስልጣን መ/ቤቱ እና ስራ ተቋራጭ በሚጠበቅባቸው መብት እና ግዴታዎች ላይ ያሳለፉትን ውሳኔ እንዳይጥሱ እንዲሁም ለሚፈጠሩ አለመግባባቶች መፍትሄ የሚያስቀምጥ ከማንኛው ወገንተኝነት ነፃ እና ገለልተኛ አካል የሆነ የግልግል ዳኝነት (Dispute Avoidance/Adjudication Board) ውሉ መሰረት ሊያቋቋሙ ይገባል፡፡
- ባለስልጣን መ/ቤቱ የሞጆ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክትም ሆነ ወደ ፊት በብድር እና በመንግስት ፋይናንስ የሚሰሩ ትላልቅ ሀገራዊ ፕሮጀክቶችን ሲቀርፅ ተቋራጭ እና አማካሪ የጨረታውን አሸንፈው ሥራውን ለመጀመር ውል በገቡበት ቀናት ውስጥ ሥራው መጀመሩን ሊከታተል ይገባል፡፡
- ባለስልጣን መ/ቤቱ የሞጆ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክትም ሆነ ወደ ፊት በብድር እና በመንግስት ፋይናንስ የሚሰሩ ትላልቅ ሀገራዊ ፕሮጀክቶችን ሲቀርፅ ስራዎች በጊዜ መስተካከል እንዲችሉ ተነባቢና የተዋረድ ተልዕኮ የሚያሳይ የክትትል፣ ድጋፍ እና ግብረ-መልስ ቼክ ሊስት በማዘጋጀትና ከመሰረተ ልማት ማስፋፍያ እና ከአይሲቲ ስራዎች በተጨማሪ አስተዳደራዊ እና የአቅም ግንባታ ስራዎች ዝግጅት የክትትል፣

ግምገማና ግብረ-መልስ ሥርዓት በመዘርጋት በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የሚገኙ የስራ ክፍሎች፣ ጽ/ቤት፣ አማካሪ ተቋምና ሥራ ተቋራጭ ጋር ያለው መስተጋብር የበለጠ መጠናከር ይኖርበታል፡፡

- ባለስልጣን መ/ቤቱ የሞጆ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክትም ሆነ ወደ ፊት በብድር እና በመንግስት ፋይናንስ የሚሰሩ ትላልቅ ሀገራዊ ፕሮጀክቶችን ሲቀርፅ የፕሮጀክት ዝግጅት እና አተገባበርን በተመለከተ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ ማጠናቀር፣ መተንተን እና ማሰራጨት ይጠበቅበታል፡፡ እንዲሁም የሞጆ አረንጓዴ ሎጂስቲክስ ማዕከል ግንባታ ፕሮጀክት ዝግጅት እና አተገባበርን በዲጂታልና በአናሎግ አደራጅቶ በመያዝ፣ ለሚፈልገው አካል ተደራሽ የሚደረግበት የመረጃ መረብ ሊዘረጋና በየጊዜው ወቅታዊ መደረግ ይኖርበታል፡፡
- ባለስልጣን መ/ቤቱ የሞጆ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክትም ሆነ ወደ ፊት በብድር እና በመንግስት ፋይናንስ የሚሰሩ ትላልቅ ሀገራዊ ፕሮጀክቶችን ሲቀርፅ የካሳ እና መልሶ ማቋቋም ወጪ ሽፍኖ መሬት እንዲለቀቅለት ሲጠይቅ የከተማ ወይም የወረዳው አስተዳደር የወጪውን መጠን ካሳወቀበት ቀን ጀምሮ በአዋጁ እና በደንቡ መሰረት ገንዘቡን ገቢ ማድረግ እንዲሁም ኮንትራክተሩ ለመንገድ ግንባታ ግብአት የተጠቀመባቸውን ቦታዎች /ማቴሪያሎች/ ከጨረሰ በኃላ መሬቱን የተፈጥሮ ይዘታቸውን በጠበቀ መልኩ ቀደሞ ወደ ነበረበት ይዞታ መመለሱን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

107. በመጨረሻም የባለስልጣን መ/ቤቱ እና የፕሮጀክት ጽ/ቤት የስራ ኃላፊዎች፣ የሥራ ተቋራጭ፣ አማካሪውም ተቋም፣የሞጆ ደረቅ ወደብ፣ የልማት ተነሽ አርሶአደሮች፣ ካሳ ገማች ኮሚቴ እና ባለድርሻ አካላት በኦዲቱ ወቅት በኦዲት ቡድኑ የተጠየቁትን ማስረጃዎች በማቅረብና ለቀረቡ ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ፤ አስተያየት በመስጠት ስላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

# አባሪ 1

## ኦዲት ተደራጊው መ/ቤት:- የኢትዮጵያ ማሪታይም ባለሥልጣን

**የኦዲት አካባቢ:-** የሞጆ ሎጅስቲክስ ማዕከል ፕሮጀክት አፈጻጸም ፣ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና እና ውጤታማ በሆኑ መልኩ መከናወኑን ማረጋገጥ፡፡

| **የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫ** (Audit Issues) | **የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች** (Evaluative Criteria ) | **የኦዲት ተደራጊ መ/ቤት አስተያየት** (Auditee Comments) |
|---|---|---|
| I. **በማሪታይም ባለስልጣን የንግድ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ሞጆ አረንጓዴ ሎጂስቲክስ ማዕከል ግንባታ ፕሮጀክቶች በዓለም ባንክ እና በፌዴራል መንግስት ፕሮጀክቶች አዘገጃጀት መመሪያ መሰረት የተከተለ መሆኑን ማረጋገጥ፡፡** | 1. የሞጆ አረንጓዴ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክት በጥናት ላይ የተመሰረተ የዲዛይንና የግንባታ ኮንትራት አስተዳደር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ **(ምንጭ:- የማሪታይም እና ሎጂስቲክስ ዘርፍ የአምስት ዓመት ስትራቴጅክ ዕቅድ፣**(2013-2017 *ገፅ* 8) | |
| | 2. ባለስልጣን መ/ቤቱ የሞጆ አረንጓዴ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክትን ሲቀርጽ የፕሮጀክቱን ገፅታ በተገቢው መንገድ የሚሳይ ግልጽ እና የተሟላ ዲዛይን በመንደፍ ስራዎችን ሊያከናውን ይገባል፡፡ **(ምንጭ:-** Ethiopian Maritime Authority modjo Dry Port Upgrading and Expansion of hub facilities project progress report no 05 page 9,22 $ 37) | |
| | 3. በባለስልጣን መ/ቤቱ የሥራ ተቋራጮች እና አማካሪ ድርጅቶችን በሚያወዳድርበት ወቅት የተጫራቾችን የቴክኒካል እና ፋይናንሻል ብቃት /Qualification/ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ **(ምንጭ:- የዓለም ባንክ የጨረታ ህጎች መመሪያ አንቀፅ** 1.7 **ገፅ** 9 **እና** Selections of Consultant Request for Proposal | |

| | | |
|---|---|---|
| | (RFP) developing Ethiopian port community system Instructions to consultant's data sheet ) | |
| | 4. የኢትጵያ ማሪታይም ባለስልጣን የተቋራጮች እና አማካሪዎች ግዢ በሚፈፀምበት ወቅት በግዥ ህግ መሰረት ሊያከናውን ይገባል፡፡<br>**ምንጭ፡- የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001** | |
| | 5. ባለስልጣን መ/ቤቱ በጨረታ ተወዳዳሪዎች ላይ ቅድመ-ብቃት /Pre-qualification/ ምዘና ማድረግ ይኖርበታል፡፡<br>**(ምንጭ፡- የዓለም ባንክ የጨረታ ህጎች መመሪያ አንቀፅ 2.9 ገፅ 16 እ.ኤ.አ ግንቦት1/2010)** | |
| | 6. ባለስልጣን መ/ቤቱ በጨረታ ያሸነፈው ተቋራጭ ለግንባታ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች መፈብረኪያ አቅርቦት ባለቤት መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡<br>**(ምንጭ፡- የዓለም ባንክ የጨረታ ህጎች መመሪያ አንቀፅ 2.9 ገፅ 16 እ.ኤ.አ ግንቦት1/2010)** | |
| | 7. ባለስልጣን መ/ቤቱ ጨረታ ያሸነፉ ተጫራቾች በሎጂስቲክስ ፕሮጀክት ግንባታ የሥራ ልምድ እና መልካም የስራ አፈጻጸም ያላቸው መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡<br>**(ምንጭ፡- የዓለም ባንክ የጨረታ ህጎች መመሪያ አንቀፅ 2.9 ገፅ 16 እ.ኤ.አ ግንቦት1/2010** | |
| | 8. ባለስልጣን መ/ቤቱ የፕሮጀክት አስተዳደር | |

| | | |
|---|---|---|
| | ማኑዋል/Project Administrative Manual/ በማዘጋጀት እና በሚመለከተው አካል በማፀደቅ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>**(ምንጭ፡- በማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን የንግድ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክት ጽ/ቤት (ሞጆ ሎጂስቲክስ ማዕከል) የ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ ገፅ 25)** | |
| **II. የኢትዮጵያ ማሪታይም ባለሥልጣን በሞጆ አረንጓዴ ሎጂስቲክስ ማዕከል ግንባታ ፕሮጀክት ለልማት ተነሽዎች በወቅቱ የካሳ ክፍያ መከፈሉን ማረጋገጥ፡፡** | 9. ባለስልጣን መ/ቤቱ ለልማት ተነሽዎች በወቅቱ የካሳ ክፍያ በመክፈል የግንባታ ቦታውን ለስራ ዝግጁ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>**ምንጭ፡- የካሳ ክፍያ አዋጅ ቁጥር 1161/2011 እና የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 472/2012** | |
| | 10.ባለስልጠን መ/ቤቱ ግንባታ ከመጀመሩ በፊት ካሳ የተከፈለበት መሬት ወሰን መከበሩን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡<br>**ምንጭ ለህዝብ ጥቅም ሲባል መሬት ሲለቀቅ ስለሚከፈል ካሳና የልማት ተነሽዎችን መልሶ ስለማቋቋም የወጣ የሚኒስተሮች ም/ ቤት ደንብ ቁጥር 472/2012 ገፅ 12465** | |
| | 11.ባለስልጣን መ/ቤቱ ካሳ እንዲከፈለው የሚጠይቅ ማንኛውም አካል የሚለቀቀው መሬት ህጋዊ ባለይዞታና ካሳ የሚከፈልበት ንብረት ባለቤት መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረቡን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡<br>**ምንጭ፡- የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ 472/2012 አንቀፅ 20)** | |
| **III.በማሪታይም ባለስልጣን የንግድ ሎጂስቲክስ** | 12.የሞጆ አረንጓዴ ሎጂስቲክስ ማዕከል ግንባታ ፕሮጀክቶት በተገባው የኮንትራት | |

| | | |
|---|---|---|
| **ፕሮጀክት ጽ/ቤት ሞጆ አረንጓዴ ሎጂስቲክስ ማዕከል ግንባታ ፕሮጀክቶች በታቀደለት ጊዜና በጀት እንዲሁም በአካባቢ እና የማህበራዊ ደህንነት ተፅዕኖ ግምገማ መሰረት እየተከናወነ መሆኑን መገምገም::** | ውል መሰርት በዕቅድ በተያዘለት ዋጋ(በጀት) ሊጠናቀቅ ይገባል፡፡ **(ምንጭ፡**-Contract Agreement between( EMAA and CCECC) on Modjo Dry Port Expansion and upgrading the hub facilities Sub-Clause 4.2.1 Contractors obligation **ገፅ** 23፣ **የኢትዮጵያ የኮንስትራክሽን ህግ ገፅ** 27, 32) | |
| | 13.የሞጆ አረንጓዴ ሎጂስቲክስ ማዕከል ግንባታ ፕሮጀክቶት በተገባው የኮንትራት ውል መሰርት በዕቅድ በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ ና ጥራት መሰረት ሊጠናቀቅ ይገባል፡፡ **(ምንጭ፡**-Contract Agreement between( EMAA and CCECC) on Modjo Dry Port Expansion and upgrading the hub facilities Sub-Clause 4.2.1 Contractors obligation **ገፅ** 23፣ **እና የኢትዮጵያ የኮንስትራክሽን ህግ ገፅ** 32) | |
| | 14.ስራ ተቋራጩ ለያንዳንዱ ግንባታ የአቅርቦት እቅድ ሊኖረው ይገባል፡፡ **(ምንጭ፡**-Contract Agreement EMMA and CCECC) On constriction of modjo dry port expansion and upgrading hub facilities | |
| | 15.ስራ ተቋራጩ የተሟላ /Equipment/ መሳሪያዎች እና ዕቃዎች የያዘ የጥራት መፈተሻ ላቦራቶሪ ሊያቋቁም ይገባል፡፡ **(ምንጭ፡**- Ethiopian Maritime Authority modjo Dry Port Upgrading and Expansion of hub facilities project | |

| | | |
|---|---|---|
| | progress report no 05 page 6,) | |
| | 16.ስራ ተቋራጩ የማህበራዊ እና አካባብያዊ አስተዳደር እቅድ ሊኖረውና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>**(ምንጭ፡-** Contract Agreement EMMA and CCECC) On constriction of modjo dry port expansion and upgrading hub facilities Addis Ababa, Ethiopia June 2021 **ገፅ** 22 | |
| | 17.ስራ ተቋራጩ የማህበራዊ እና አካባብያዊ አስተዳደር ዕቅድን ስድስት ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ሊገመግም ይገባል፡፡<br>**(ምንጭ፡-** Contract Agreement EMMA and CCECC) On constriction of modjo dry port expansion and upgrading hub facilities Addis Ababa, Ethiopia June 2021 **ገፅ** 22 | |
| | 18.ስራ ተቋራጩ የሞጆ ሎጂስቲክስ ግንባታ ፕሮጀክት ሂደት ወቅት ሴቶች እና አካል ጉዳተኞችን አካታች ባደረገ መልኩ ሊተገብር ይገባል፡፡<br>**(ምንጭ፡-**Contract Agreement between ( EMAA and CCECC) on Modjo Dry Port Expansion and upgrading the hub facilities Sub-Clause 6.25 contractors personnel **ገፅ** 32) | |
| IV.**ባለስልጣን መ/ቤቱ ተቋራጭም ሆነ አማካሪ ድርጅት በገቡት የኮንትራት ውል እና ውሉን መሰረት አድርጎ በተዘጋጀው ቴክኒካዊ** | 19.ባለስልጠን መ/ቤቱ የፕሮጀክቱን በበላይነት የሚመራ፣ የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላትን ያካተተ ስትሪንግ ኮሚቴ ሊቋቋም ይገባል፡፡<br>**ምንጭ፡-በማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን የንግድ** | |

| | | |
|---|---|---|
| **የሥራ ዝርዝር ውል መሰረት ግዴታቸውን መወጣታቸውን በቅድመ-ትግበራ፣ በሥራ ሂደት ትግበራ እና ድህረ ትግበራ ወቅት ውጤታማ ክትትልና ቁጥጥር ማድረጉን በተመለከተ፡፡** | **ሎጂስቲክስ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ሞጆ ሎጂስቲክስ ማዕከል የ2013 ዓ.ም በጀት ዓመት ዕቅድ ገፅ 9)** | |
| | 20.የፕሮጀክት ስትሪንግ ኮሚቴው የፕሮጀክቱን አፈፃፀም በበላይ ሆኖ ሊከታተል እና ሊገመግም ይገባል፡፡ **(ምንጭ፡- በማሪታይም ባለስልጣን የንግድ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክት ጽ/ቤት (ሞጆ አረንጓዴ ሎጂስቲክስ ማዕከል) የ2014 በጀት ዓመት ዓመታዊ ሪፖርት ሰኔ 2014 ዓ.ም ገፅ 10)** | |
| | 21.ስትሪንግ ኮሚቴው ለፕሮጀክቱ አፈፃፀም የሚረዱ የፖሊሲ አቅጣጫዎችን ሊያመላክት ይገባል፡፡ **(ምንጭ፡- በማሪታይም ባለስልጣን የንግድ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክት ጽ/ቤት (ሞጆ አረንጓዴ ሎጂስቲክስ ማዕከል) የ2014 በጀት ዓመት ዓመታዊ ሪፖርት ሰኔ 2014 ዓ.ም ገፅ 10)** | |
| | 22.የፕሮጀክት ስትሪንግ ኮሚቴው ሪፖርቶችን፣ እቅዶችንና በጀትን ገምግሞ ሊያፀድቅ ይገባል፡፡ **(ምንጭ፡- በማሪታይም ባለስልጣን የንግድ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክት ጽ/ቤት (ሞጆ አረንጓዴ ሎጂስቲክስ ማዕከል) የ2014 በጀት ዓመት ዓመታዊ ሪፖርት ሰኔ 2014 ዓ.ም ገፅ 10)** | |
| | 23.በባለስልጣን መ/ቤቱ እና ኮንትራክተሩ የጋራ የሆነ ያለመግባባትን የሚፈታ /የዳኝነት ቦርድ (Dispute Avoidance/Adjudication Board) ሊያቋቁሙ ይገባል፡፡ **(ምንጭ፡-** Contract Agreement between ( EMAA and CCECC) on Modjo Dry Port | |

| | | |
|---|---|---|
| | Expansion and upgrading the hub facilities General conditions of Dispute Avoidance/Adjudication Agreement Page 15 and 41) | |
| | 24. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ተቋራጭ እና አማካሪ ተቋም በውሉ መሰረት ስራቸውን በግዜው መጀመራቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል። (**ምንጭ**፡-Contract Agreement between( EMAA and CCECC) on Modjo Dry Port Expansion and upgrading the hub facilities Contractors & consultant obligation *ገፅ* 23) | |
| | 25. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ፕሮጀክቱ ወደፊት ሊያጋጥሙት የሚችሉ ችግሮችን ለመቅረፍ የሚያስችል የፕሮጀክት ስጋት ማቅለያ ዕቅድ/Project Risk Mitigation Plan/ ሊያዘጋጅ እና ሊተገብር ይገባል። **(ምንጭ፡- በማሪታይም ባለስልጣን የንግድ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክት ጽ/ቤት (ሞጆ አረንጓዴ ሎጂስቲክስ ማዕከል) የ2014 በጀት ዓመት ዓመታዊ ሪፖርት ሰኔ 2014 ዓ.ም ገፅ 12)** | |
| | 26. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ኮንትራክተሩ/ተቋራጭ ለግንባታ ሥራ ወደ መስክ /ሳይት/ ያሰማራቸው የግንባታ ማሽነሪዎች፣ መሳሪያዎች እና ዕቃዎች የሎጂስቲክስ ግንባታውን ለማከናወን በሚያስችል ሁኔታ ብቁ መሆናቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል። (**ምንጭ**፡-Contract Agreement EMMA and CCECC) On constriction of modjo dry port expansion and upgrading hub facilities special provisions sub- | |

| | | |
|---|---|---|
| | clause4.1 | |
| | 27.ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በሳምንት፣በየወር እና በየሩብ አመቱ፣ ከአማካሪ ድርጅቱ የሚላኩ የፕሮጀክቱን አፈጻጸም የሚያስረዱ ሪፖርቶችን መሰረት በማድረግ የጽሁፍ ግብረ መልስ ሊያቀርብ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡-በማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን የንግድ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ሞጆ ሎጂስቲክስ ማዕከል የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ ገፅ 23 እና በማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን የንግድ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክት ጽ/ቤት የ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ**) | |
| | 28.ባለስልጣን መ/ቤቱ የሞጆ ሎጂስቲክስ ግንባታ ፕሮጀክት በሚተገበርበት ወቅት ማህበራዊ አካባብያዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ወይም ለማሳዳግ ሴቶች እና አካል ጉዳተኞችን አካታች ባደረገ መልኩ እየተተገበረ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡ (**ምንጭ፡**-Contract Agreement between ( EMAA and CCECC) on Modjo Dry Port Expansion and upgrading the hub facilities Sub-Clause 6.25 contractors personnel **ገፅ** 32) | |
| | 29.ባለስልጣን መ/ቤቱ የፕሮጀክት አስተዳደር አቅምን ለማሳደግ የክትትል፣ ቁጥጥርና የማብቃት ስራዎችን ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ **(ምንጭ፡- የማሪታይም እና ሎጂስቲክስ ዘርፍ የአምስት ዓመት ስትራቴጅክ ዕቅድ፣**(2013-2017) **ገፅ**26) | |

| | | |
|---|---|---|
| | 30.ስራ ተቋራጩ የሞጆ አረንጓዴ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክት ስራዎችን በተመለከተ ለሰራተኞች እና ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የተለያዩ ስልጠናዎች፣ ሙያዊ ወርክሾፖችን አዘጋጅቶ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡<br>(**ምንጭ፡-** Contract Agreement between ( EMAA and CCECC) on Modjo Dry Port Expansion and upgrading the hub facilities Sub-Clause 6.27 contractors personnel *ገፅ* 33)<br>31.ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ከግዥው ጋር የተያያዙ ሰነዶችን በአግባቡ መያዝና በሚመለከታቸው አካላት ሲጠየቅ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡<br>**ምንጭ፡- የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001** | |
| | 32.ባለስልጠን መ/ቤቱ የሞጆ አረንጓዴ ሎጂስቲክስ ማዕከል ግንባታ ፕሮጀክት ዝግጅት እና አተገባበርን በተመለከተ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ ማጠናቀር፣ መተንተን እና ማሰራጨት ይኖርበታል፡፡<br>**ምንጭ፡-መልካም ተሞክሮ** | |
| | 33.ባለስልጠን መ/ቤቱ፣ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ፣ አማካርው ተቋም እና ስራ ተቋራጩ የሞጆ አረንጓዴ ሎጂስቲክስ ማዕከል ግንባታ ፕሮጀክትን በተመለከተ መረጃ/ሰነድ በአግባቡ መያዝና በሚመለከታቸው አካላት ሲጠየቅ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡<br>**ምንጭ፡-መልካሚ ተሞክሮ** | |


# አባሪ 2

የተከለሱ ማስረጃዎች  ዋና ዋና ሰነዶች

1. የኢትዮጵያ ማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን የፕሮጀክቱ ፕሮግረስ ሪፖርቶች
2. በማሪታይም ባለስልጣን የንግድ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክት ጽ/ቤት (ሞጆ አረንጓዴ ሎጂስቲክስ ማዕከል) በጀት ዓመት ዓመታዊ ሪፖርቶች
3. የተልዕኮ ግምገማም ሰነዶች (IMS)
4. በጨረታ ገምጋሚ ኮሚቴ የተገመገሙ የጨረታ ሰነዶች
5. በአማካሪዎች የተጠኑ የዲዛይን እና የፍላጎት ትንተና ሰነዶች
6. የአስር(10) አመት መሪ እቅድ እና የአምስት (5) አመት ስትራቴጂክ እቅድ
7. በፕሮጀክቱ  ስራ የሚደረጉ የውይይት ቃለ-ጉባዔዎች
8. የፕሮጀክቱ ሂደት ላይ የሚደረጉ ውይይቶች እና ወርክሾፖችን የሚያሳዩ መረጃዎች
9. በስራ ተቋራጩ እና በአማካሪ ምህንዲስ የተደረጉ የላብራቶሪ ውጤት የሚያሳዩ ሰነዶችን
10. በሞጆ ሎጂስቲክስ ማዕከል ፕሮጀክት ለልማት ተነሺዎች የተከፈለ የካሳ ክፍያ ሰነዶችን
11. ባለስልጣን መ/ቤቱ ከስራ ተቋራጩ እንዲሁም ከአማካሪው ጋር ያደረጓቸው የውል ስምምነት ሰነዶች

# አባሪ 3

## የማሪታይም ባለስልጣን ድርጅታዊ መዋቅር



## አባሪ 4

Form IVB. Adjustments–Currency Conversion–Evaluated Prices

| Consultants' Names | Proposals' prices | | Adjustments | Evaluated price(s) | Conversion to currency of evaluation | | Financial scores |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | Currency | Amounts (1) | (2) | (3) = (1) + (2) | Exchange rate(s) (4) | Proposals' prices (5) = (3)(4) | (6) |
| EPTISA SERVICIOS DE INGENIERIA, S.L. in association with PAN AFRICA GEO INFORMATION SERVICES PLC (Sub consultant) | USD | 1,062,800 | - | 1,062,800 | 40.9756 | 43,548,867.68 | |
| | ETB | 40,463,000 | | 40,463,000 | 1.0000 | 40,463,000.00 | |
| | | | | | | 84,011,867.68 | 97.17 |
| PROSPECTIVA SA | EUR | 1,671,160 | - | 1,671,160 | 48.8470 | 81,631,152.52 | 100.00 |
| JV SYSTRA SA and KHATIB & ALAMI (K&A) | USD | 1,160,078 | - | 1,160,078 | 40.9756 | 47,534,892.10 | |
| | ETB | 44,895,722 | | 44,895,722 | 1.0000 | 44,895,722.00 | |
| | | | | | | 92,430,614.10 | 88.32 |

**Form IVC. QCBS–Combined Technical/Financial Evaluation–Award Recommendation**

| | Technical Evaluation | | | Financial Evaluation | | Combined Evaluation | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| Consultants' names | Technical scores[a] S(t) | Weighted scores $S(t) \times T^b$ | Technical rank | Financial scores[c] S(f) | Weighted scores $S(f) \times F^d$ | Scores S(t) T + S(f) F | Rank |
| EPTISA SERVICIOS DE INGENIERIA, S.L. in association with PAN AFRICA GEO INFORMATION SERVICES PLC (Sub consultant) | 89.35 | 44.68 | 2 | 97.17 | 48.59 | 93.27 | 2 |
| PROSPECTIVA SA | 88.36 | 44.18 | 3 | 100.00 | 50.00 | 94.18 | 1 |
| JV SYSTRA SA and KHATIB & ALAMI (K&A) | 91.98 | 45.99 | 1 | 88.32 | 44.16 | 90.15 | 3 |
| Award recommendation | To highest combined technical/financial score. Consultant's name: PROSPECTIVA S.A. | | | | | | |

a. See Form IIB.
b. T = As per RFP.
c. See Form IVB.
d. F = as per RFP.

# አባሪ-5

## ሰንጠረዥ 1፡ የ2015 በጀት ዓመት የፊዚካል ስራዎች እቅድ አፈፃፀም

| ተ.ቁ. | ዘርፍ | እስከ 2014 በጀት ዓመት መጨረሻ ድረስ የተደረሰበት | የ2015 በጀት ዓመት | | | እስከ 2015 በጀት ዓመት መጨረሻ ድረስ የተደረሰበት አጠቃላይ ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዓመታዊ ዕቅድ | ዓመታዊ ክንውን | የበጀት ዓመቱ ክንውን በ% | |
| | በፕሮጀክት ደረጃ | 36.49 | 28.51 | 15.39 | 54.0 | 51.88 |
| **I** | **በሞጆ ደረቅ ወደብ የሚከናወነው የመሰረተልማት ማስፋፊያ ስራ** | **33.23** | **30.06** | **17.53** | **58.3** | **50.76** |
| 1.1 | የስራ ቁጥጥርና የኮንትራት አስተዳደር (የክትትል ስራው) | 29.17 | 50 | 37.83 | 75.7 | 67.00 |
| 1.2 | የግንባታ ስራ | 2.5 | 33.72 | 23.80 | 70.6 | 26.30 |
| | የሁለተኛው መዕራፍ ማሽነሪዎች የምርት ሂደት | | 79.49 | 72.86 | 91.7 | 72.86 |
| | RTG/የ13 ወራት ኮንትራት | | 92.3 | 84.62 | 91.7 | 84.62 |
| | RMG/ የ18 ወራት ኮንትራት | | 66.67 | 61.11 | 91.7 | 61.11 |
| **II** | **የ IT ስራዎችን በማስፋፋት ቀንጅታዊ አሰራርን የማሳደግ ስራ** | **42.04** | **23.24** | **2.09** | **9.0** | **44.13** |
| | የፖርት ኮሚዩኒቲ ሲስተም(PCS) | 14.6 | 25.4 | 21.19 | 83.4 | 35.79 |
| | የToS እና Electronic gate pass system | 53.8 | 26.6 | 0.00 | 0.0 | 50.00 |
| **III** | **የአስተዳደራዊና ተቋማዊ (አቅም ግንባታ) ድጋፍ ስራ** | **57.12** | **21.24** | **16.99** | 80.0 | **74.11** |

| | | | | የ2015 በጀት ዓመት | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | ዋና ዋና ተግባራት(ኮምፖነንቶች) | ጠቅላላ የተመደበ | እስከ 2014 በጀት ዓመት ድረስ የተደረሰበት | ዕቅድ | | ክንውን | | | እቅድ አፈፃፀም በመቶኛ | |
| | | | | ዓመታዊ | 4ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት | እስከ 4ኛ ሩብ ዓመት | ፕሮጀክቱ ከተጀመረ ጀምሮ | ከዓመቱ | ፕሮጀክቱ ከተጀመረ ጀምሮ |
| I | በሞጆያለውንመሰረተ-ልማትማሻሻል (Improvement of infrastructure at Modjo) | 120,000,000.0 | 43,626,348.00 | 59,008,602.83 | 16,430,114.69 | 4,058,944.73 | 15,495,455.73 | 59,121,803.73 | 26.26 | 49.27 |
| | ጥናትና ዲዛይን | | 953,675.19 | | 0.00 | | - | 953,675.19 | | |
| | አማካሪ | 2,357,833.63 | 903,237.41 | 943,133.45 | 235,783.36 | 292,538.78 | 831,081.55 | 1,734,318.96 | 88.12 | 73.56 |
| | ግንባታ | 88,125,000.00 | 20,383,698.04 | 48,440,000.00 | 11,694,666.67 | 3,766,405.95 | 13,753,523.18 | 34,137,221.22 | 28.39 | 38.74 |
| | ፖርት ማሽነሪ | | 21,385,737.36 | 9,625,469.38 | | - | 910,851.00 | 22,296,588.36 | 9.46 | |
| | ፖርት ማሽነሪ 1 | | 19,969,525.36 | | | | - | 19,969,525.36 | | |
| | ፖርት ማሽነሪ 2 | | 1,416,212.00 | | 4,499,664.66 | | 910,851.00 | 2,327,063.00 | | |
| II | የኢንፎርሜሽንቴክኖሎጂስርዓቶችንበማጠንከርየተቀናጀአሰራርእንዲኖርማድረግ | 15,000,000.00 | 307,732.00 | 6,140,137.89 | 5,143,723.55 | 51,134.00 | 51,955.35 | 359,687.35 | 0.85 | 2.40 |
| | EPCS | | | 890,000.00 | 600,000.00 | 51,134.00 | 51,955.35 | 51,955.35 | 5.84 | |
| | TOS-GOS | | 307,732.00 | 5,250,137.89 | 4,543,723.55 | | - | 307,732.00 | - | |
| III | የአስተዳደራዊናተቋማዊ (አቅም ግንባታ) ድጋፍ (Regulatory and Institutional Capacity | 15,000,000.00 | 4,263,019.00 | 4,744,446.37 | 534,510.39 | 715,042.00 | 1,516,725.00 | 5,779,744.00 | 31.97 | 38.53 |

| | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | Buliding) | | | | | | | | | |
| | ድምር | 150,000,000.00 | 48,197,099.00 | 69,893,187.09 | 22,108,348.63 | 4,825,120.73 | 17,064,136.08 | 65,261,235.08 | 24.41 | 43.51 |

ሰንጠረዥ 2፡ እስከ 2015 በጀት ዓመት የፕሮጀክቱ የገንዘብ አጠቃቀም በአሜሪካ ዶላር

# አባሪ-6

**ሰንጠረዥ 3፡ እስከ 2016 በጀት ዓመት 6 ወር መጨረሻ ድረስ የፕሮጀክቱ የሰው ሃይል ዝርዝር**

| S.No | Professions | Approve | Available |
|---|---|---|---|
| | PIU level | 28 | 16 |
| 1 | Project Coordinator | 1 | 1 |
| 2 | Contract administration Specialist | 2 | 1 |
| 3 | Procurement Specialist | 2 | 1 |
| 4 | Financial Management Specialist | 2 | 2 |
| 5 | Project Engineer | 1 | 0 |
| 6 | Logistics Specialist | 2 | 0 |
| 7 | Social Safeguard Specialist | 1 | 1 |
| 8 | Environmental Safeguard Specialist | 1 | 0 |
| 9 | ICT Specialist | 2 | 1 |
| 10 | Monitoring and Evaluation Specialist | 1 | 1 |
| 11 | Electromechanical Engineer | 1 | 0 |
| 12 | Gender Specialist | 1 | 0 |
| 13 | Internal Auditor | 1 | 0 |
| 14 | Office Administrator | 1 | 0 |
| 15 | Office Assistant | 2 | 2 |
| 16 | Office Clerk | 1 | 1 |
| 17 | ICT Support Technician | 1 | 0 |
| 18 | Drivers | 3 | 3 |
| 19 | Liasson officer(EMA) | 1 | 1 |

## LOGISTICS TRANSFORMATION OFFICE STAFF

| S.N | Name of the staff | Position | Start Date |
|---|---|---|---|
| 1 | Mr.Temesegen Yihunie | Logistic Expert/Depty Director | 01/01/2019 |
| 2 | Dr.Mengist Hailmariam | Strategic Advisor | 04/04/2017 |
| 3 | Mr.Desalegn Gutu Disso | Logistic Expert | 01/01/2019 |
| 4 | Ms. Aneni Kejela | Maritime Lawyer | 04/12/2023 |
| 5 | Mr.Eyasu Yimam Ali | Senior Economist | 21/05/2020 |
| 6 | Mr.Nigussie Tisge Nigatu | M&E Specialist | 25/05/2020 |
| 7 | Mr.Gaim Yibrah Tesema | Senior Trade Facilitation | 08/06/2020 |
| 8 | Mr.Kalayu Tesema Bogale | Senior Shipping Expert | 26/10/2020 |
| 9 | Mrs. Hilina Tibebu | Office Admin | 06/02/2023 |
| 11 | Mr. Shimeles Teka | Driver | 12/09/2017 |

**አባሪ-7** ፡- Program Information (የፕሮግራም መረጃ)

| | |
|---|---|
| Project Name | Ethiopia Trade Logistics Project |
| Financers | The World Bank/IDA/ |
| Program Duration | 5 years |
| Project Effectiveness Date | July 5th, 2017 |
| Project Closing Date | July 7th, 2023 |
| Program Intervention areas | Modjo Dry Port |
| Development objective | to enhance the performance of the Ethio-Djibouti corridor through improvements in operational capacity, efficiency, and range of logistics services at the Modjo Dry Port. |
| Program Components | Improvement of Infrastructure at Modjo, Enhancing coordination through investments in IT systems, and Regulatory and institutional capacity support. |
| Program Direct Beneficiaries | private sector exporters, importers, manufacturers and farmers, those working for companies producing goods for export, government agencies involved in exporting and importing, and consumers |
| Program Budget | 150 Million USD |
| Budget for the program year | |
| Component based budget allocation | • Component 1: Improvement of infrastructure at Modjo: 120 Million USD<br>• Component 2: Enhancing coordination through investments in IT systems: 15 Million USD and<br>• Component 3: Regulatory and institutional capacity support: 15 Million USD |
| Reporting period | 2020 |

**አባሪ-8** ፡- በስራ ተቋራጩ ተገዝቶ ለአማካሪው እና ለአሰሪው ድርጅት የተላለፉ አጠቃላይ መኪናዎች ዝርዝር

## Dihong International FZE

P O Box 52216, Hamriyah Free Zone,Sharjah,UAE

+97142654058 , +971567650448

# Commercial Invoice

| | |
|---|---|
| CHINA CIVIL ENGINEERING CONSTRUCTION CORPORATION ETHIOPIA BRANCH (CONSTRUCTION OF MODJO DRY PORT EXPANSION AND UPGRADING OF HUB FACILITIES)<br>ADDRESS: WOREDA 03, NEFAS SILK-LAFTO<br>ADDIS ABABA, ETHIOPIA<br>CONTACT PERSON: MR.TIAN ZHIJIAN<br>TEL: +251-938836888<br>EMAIL: ccecc_logistics@163.com | Invoice No: DHL-22060 |
| Shipping way: Sea | DATE: 11-08-2022 |
| Port of Loading: Jebel Ali | Port of Discharge: Djibouti |

| NO. | Name of Goods | Chassis no. | Brand | Origin | HS code | Unit | Qty | Unit Price (USD) | Total Value (USD) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | Nissan Patrol LE Platinum 5.6L DOHC V8 Petrol, Automatic Transmission, Left Hand Drive, Black Color, Model-2022 | JN8AY2NYXN9447059 | NISSAN | JAPAN | 87032331 | Unit | 1 | 84500.00 | 84500.00 |
| 2 | TOYOTA, LAND CRUISER 300 Turbo GXR, 3.3L V6 Diesel, Automatic Transmission, Left Hand Drive, White Color, Model-2022 | JTMAABBJ4N4010629 | TOYOTA | JAPAN | 87032431 | Unit | 1 | 93500.00 | 93500.00 |
| 3 | TOYOTA, LAND CRUISER 300 Turbo GXR, 3.3L V6 Diesel, Automatic Transmission, Left Hand Drive, White Color, Model-2022 | JTMAABBJ3N4011822 | TOYOTA | JAPAN | 87032431 | Unit | 1 | 93500.00 | 93500.00 |
| EXW Dubai Total Amount USD | | | | | | | | | 271500.00 |
| Sea freight, port miscellaneous charges, local charges, loading and unloading charges, document charges, etc..in USD | | | | | | | | | 6500.00 |
| **CIF Djibouti Total Amount USD** | | | | | | | | | **278000.00** |

غرفة تجارة وصناعة الشارقة
Sharjah Chamber of Commerce & Industry
مرفقات شهادة المنشأ
Attachment of certificate of Origin

P.O.Box: 52216
Sharjah - U.A.E.
Dihong International - FZE

# Dihong International FZE

P O Box 52216, Hamriyah Free Zone,Sharjah,UAE

+97142654058 , +971567650448

## Commercial Invoice

CHINA CIVIL ENGINEERING CONSTRUCTION CORPORATION ETHIOPIA BRANCH (CONSTRUCTION OF MODJO DRY PORT EXPANSION AND UPGRADING OF HUB FACILITIES)
ADDRESS: WOREDA 03, NEFAS SILK-LAFTO
ADDIS ABABA, ETHIOPIA
CONTACT PERSON: MR.TIAN ZHIJIAN
TEL: +251-938836888
EMAIL: ccecc_logistics@163.com

Invoice No: DHL-22060-2

Shipping way: Sea

DATE: 27-09-2022

Port of Loading: Jebel Ali

Port of Discharge: Djibouti

| NO. | Name of Goods | Chassis no/ Engine no | Brand | Origin | HS code | Unit | Qty | Unit Price (USD) | Total Value (USD) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | Chevrolet Suburban LT, 5.3L ECOTEC3 V8 provides 355 horse power and 519 Nm of torque, 10-speed automatic transmission 4WD, Petrol, Combined 16 MPG, 8 seater, Left Hand Drive<br>Black Color- Model-2022 | Chassis no: 1GNSK9KD9NR309225<br>Engine no: L84ANR309225 | Chevrolet | USA | 87032331 | Unit | 1 | 82900.00 | 82900.00 |
| EXW Dubai Total Amount USD | | | | | | | | | 82900.00 |
| Sea freight, port miscellaneous charges, local charges, loading and unloading charges, document charges, etc..in USD | | | | | | | | | 2000.00 |
| **CIF Djibouti Total Amount USD** | | | | | | | | | **84900.00** |

P.O.Box: 52216
Sharjah - U.A.E.
Dihong International - FZE